# ሦስት አይነት አማኞች

ራሶቻችን ዝቅ እናድርግ። ራሳችንንና፡ ልባችንን አዘንብለን፡ በጸሎት እንድናስታውሳቸው የሚፈልጉ ሰንቶች እንደሆኑ ለማወቅ እወዳለሁ፡ እጃችሁን ብቻ ወደ ላይ በማንሳት፡ "ጌታ ሆይ፡ እባክህ አሰበኝ፡ ጌታዬ፡" በሉ። እዚህ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጡ፡ ብዙ የጸሎት ጥያቄዎችና መሃረቦች አሉ።

2 ውድ የሰማይ አባት ሆይ፡ ብዙ ጊዜ ከእኛ ጋር በተገናኘህበትና፡ ፍቅርህን በገለጽክልን በዚህ ጣሪያ ስር፡ ዛሬ ምሽትም እንደገና ተሰብሰበናል፥ ለእኛ ስላደረግከው ነገር፡ ባለን ትሁት መንገድ ፍቅራችንንና ምስጋናችንን ለአንተ ለመግለጽ እንሞክራለን። ዛሬ ማታም እንደገና መጥተናል፡ ጌታ ሆይ፡ እርዳታህን እንደምንሻ ህዝቦች ሆነን፡ ሁልጊዜ አንተን እንፈልጋለንና። በዚህ ምድር ላይ እስካለን ድረስም፡ ጩኸታችን ይህ እንደሚሆን እናውቃለን፡ በውጊያ ውስጥ ነንና። እኛም... ውጊያው ተፋፍሟል፡ ጠላትም እንዴት እንደሚያገሳ አንበሳ እንደሚሆን ቃል ገብተህ ነግረኸናል። እርሱ በሰዎች መካከል ተለቋል፡ ሊውጠው የሚችለውን እንደሚፈልግ፡ እንደሚያገሳ አንበሳ በየቦታው እናየዋለን፡ ምክንያቱም ጊዜው አጭር መሆኑን ያውቃልና። ሆኖም እኛ—እኛ—ለታናናሾቹ የሚያስብ አባት አለን፡ ወደ አንተም ከነጥያቄዎቻችን እንሸሻለን፡ ዛሬ ማታ፡ ጌታ ሆይ። እነዚያንም ትሰጥ ዘንድ ይሁንልን ብለን እንጸልያለን።

3 አባት ሆይ፡ እዚህ የተቀመጡት እነዚህ መሃረቦች፡ በምድሪቱ ላይ የሆነ ቦታ የታመሙ ሰዎች እንዳሉ ያሳያል፡ ያም አንተን እየጠሩና እየፈለጉ ነው፡ በአንተም በማመን፡ እምነታቸውን ለመለማመድ እነዚህን መሃረቦች ወደዚህ ልከዋል። አምላክ ሆይ፡ እያንዳንዳቸው እንዲፈወሱ ይሁንልን።

4 ጌታ ሆይ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ በዚያ ክፍል ውስጥ ሆኖ ኃይልህን አይተናል፡ የማስታወስ ችሎታውን ላጣው ልጅ ፍጹም የሆነ ማስታወስን ስትመልስለት አየን። በሽታን በማስወገድ፡ የልብን ሚስጥር በመግለጥ፡ ለሰዎችም በማሳየትና፡ በቅደም ተከተል በማቀናጀት፡ ታላቅ ኃይልህን ደጋግመን እናያለን። እናመሰግንሃለን፡ ጌታ አምላክ ሆይ፡ ምክንያቱም ያ ከማንኛውም ሰው አቅም በላይ ነውና። ትክክለኛውን መንሰኤ እንዴት እንደምትገልጥ፡ ሰበቡ ምን እንደሆነ፡ እንዲሁም እንዴት እንደሆነ፡ ያ ከማንኛችንም እውቀት በላይ ነው። ያ አንተ ነህ፡ አባት ሆይ። ደግሞም እናውቃለን፡ ይህም፡ "ቃሉ ልብን ይመረምራል፡ የልብንም ሀሳብና ስሜት እንደሚለይ፡" ስለዚህም አንተን እናመሰግንሃለን።

5 አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ህዝቡ አሁን፡ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው፡ በእነዚህ ነገሮች ላይ እያሰቡ እንደሆነ እናምናለን፡ የሚናገራቸውም መንፈስ ቅዱስ ነው። የእያንዳንዳቸውም ጥያቄ እንዲመለስ ይሁንልን። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ መዳን የሚችሉትን አድን። የጠፉትም፡ ወደ ውስጥ ገብተው ይዳኑ።

6 ያንን ታላቅና ግዙፍ የራስ ልብስ ክምር፡ እዚያ በማየታችን፡ መቃብሩ እንደተከፈተ፥ እንዲሁም ለብዙዎቹ፡ የአሮጌው-ሰው ኃጢአት መቀበሩን በማወቃችን እጅግ እናመሰግናለን። አባት ሆይ፡ ለዚህም አመሰግንሃለሁ።

በቀሪው ዘመናቸውም፡ በአዲስ ሕይወት ይመላለሱ ዘንድ ይሁንልን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንጠይቃለን። ኣሜን።

7 ጌታ ይባርካችሁ፡ በልባችሁ የነበረው ጥያቄ ይመለስ ዘንድ ይሁን።

8 አሁን፡ ወንድም ዊለር ትንሽ ሕፃን እንዳለው ቢሊ የነገረኝ ይመስለኛል። ልክ ነው? ተሳስቻለሁ'ዴ፡ ለጌታ አደራ እንዲሰጥ፡ ወይስ ሌላ ነገር ነውን፡ ወይም አደራ መስጠት አይደል? [ወንድም ኔቪል፡ "ሦስት ወይም አራት ሕፃናት ያሉ ይመስለኛል" አለ።—አርታዒ።] እሺ። አሁን ወደ ፊት ልታመጧቸው ከፈለጋችሁ፡ ደስ ይለናል፥ ሽማግሌዎቹ ወደ ፊት መጥተው፡ አደራ የመስጠት አገልግሎት፡ በእነዚህ ታናናሾች ላይ እጃቸውን ቢጭኑ። አጠር ለማድረግ እንሞክራለን። ወደ ጌታ ኢየሱስ ለማምጣት፡ እነዚህ ታናናሾች፡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትንንሽ—ዕንቁዎቻቸውን ይዘው ሊመጡ የሚፈልጉትን እንሻለን። ነገ ምን እንደሚሆን አናውቅምና፡ ሁልጊዜም ለእነርሱ መንገድ ለመክፈት እንሞክራለን።

9 እናቴ፡ "ዛሬ ሊደረግ የሚችለውን፡ ለነገ አታስተላልፍ፡" ትለኝ ነበር። ልክ ነው፡ ምክንያቱም ነገ ምን እንዳዘለ አታውቁም፡ ነገን ማን እንደያዘው ግን እናውቃለን። ዋናው ነገሩ ያ ነው። ነገን ማን እንደያዘው እናውቃለን።

10 ወንድም ዊለር፡ ጌታ አምላክ ይባርክህ። ይህቺ ደግሞ እህት ዊለር ናት። ከእናንተ ጋር በመገናኘቴ በእርግጥ ደስተኛ ነኝ። እስከማውቀው ድረስ፡ ከእናንተ ጋር ሰገናኝ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ይመስለኛል፡ ይህም ለእኔ... ታላቅ መታደል ነው። ይህችም ልጃችሁ ናት። ስሟ ማን ነው? [እህት ዊለር፡ "ካርሊና ሬቤካ" አለች።—አርታዒ።] ካርሊና ሬቤካ። መልካም፡ ምንኛ ግሩም ልጅ ናት፡ እጅግ በጣም ቆንጆ ናት። ይኸው፡ ትንሿ ካርሊና ሬቤካ ዊለር።

11 ወንድም ዊለር እዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ዲያቆኖቻችን አንዱ ነው፡ እግዚአብሔርም በትዳራቸው ላይ፡ ይህችን ታናሽ ልጅ በመስጠት ባርኮአቸዋል። ወደ ሁለት ሌሎች ሴቶች ልጆች አሉህ ብዬ አምናለሁ፡ አይደል? [ወንድም ዊለር፡ "ሦስት" አለ።—አርታዒ።] ሦስት ሌሎች ሴቶች ልጆች። እነርሱ በእርግጥም ጥሩ ልጃገረዶች ናቸው፡ እኔ እንደምረዳው፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ሬቤካንም ልክ እንደ እነርሱ እንዲያደርጋት እጸልያለሁ። አያችሁ? ከዚያም ያ ለሁላችሁም እርካታ ይሆንላችኋል፡ አይደል? ልክ ነው፡ ምክንያቱም በጣም ተወዳጅ ልጆች ናቸውና።

12 እንዳቅፋት ትፈቅድልኝ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ አላውቅም፡ ነገር ግን፡ እሷ ባትፈቅድልኝ እንኳን፡ እጃችንን እንጭንባታለን። ሬቤካ፡ ወደዚህ ወደ እኔ መምጣት ትፈልጊያለሽ? እንድይዝሽ ትፈልጊያለሽ? በጣም ጥሩ ነው። እንዴት ያለች ቆንጆ ልጅ ናት!

አሁን ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

13 ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት፡ በዚህ ዲያቆን ፊት ቆመን ሳለ፥ በእውነትም አገልግሎቱ ግሩም ነው፡ ዲያቆን ነቀፋ የሌለበት ይሆን ዘንድ ይገባልና፡ የአንዲት ሚስት ባል፡ ቤተሰቡን በጥሩ ሁኔታ የሚያስተዳድር መሆን አለበትና። ምክንያቱም፡ የራሱን ቤት ማስተዳደር ካላወቀ፡ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት መጠበቅ ይችላል? ይህ ወንድም እነዚህን መስፈርቶች ስላሟላ እናመሰግንሃለን፡ በውስጡም የእግዚአብሔርን መንፈስ አግኝተናል።

14 እነሆ ሕፃን ሴት ልጁን አደራ ለመስጠት፡ ይዞ መጣ። ያሳድጓትም ዘንድ በክንዳቸው ውስጥ አስቀምጠሃታል። አምላክ ሆይ፡ ምኞታቸው እርሷም እንደ ሌሎቹ እህቶቿ እንድትሆን ነው፡ ብለን ለመናገር መቻላችን፡ ምንኛ እናምስግንሃለን። አባት ሆይ፡ ይህ እንዲሆን፡ ይሁንልን። ሕፃኗም በሕይወት ትኑርና—ለአንተም ታላቅ አገልግሎት ትሁን፡ አባት ሆይ። አሁንም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይህች ሕፃን ለአገልግሎት ሕይወት ለአንተ እንሰጣለን። ጤነኛና፡ ጠንካራ አድርጋት፥ ከተቻለም፡ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ፡ ረጅም ዕድሜ ትኑር። ከዚያም፡ አባት ሆይ፡ በክርስቶስ ምክርና ተግሣጽ እንደምታድግ እናምናለን። ለአገልግሎት ሕይወትም፡ ሕይወቷን ለአንተ እንሰጣለን። አሜን።

15 እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ርብቃ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ወንድም ዊለርና እህት ዊለር። ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን።

16 እንዴት ነሽ? አሁን እዚህ ፊቷ ላይ ፈገግታ የተሞላች ሌላ ትንሽ ልጅ አለች። ስሟ ማን ነው? [እናቲቱ፡ "ሮንዳ ረኔ ኮትስ" አለች።—አርታዒ።] ሮንዳ ረኔ ኮትስ፡ ልክ ነው? ከእነ ጄሲ፡ ከጄሲ ኮትስ ጋር ዝምድና አላችሁ? ["የለንም።"] እኔ እንደሚመስለኝ... እዚህ ከተማ ውስጥ አንዳንድ የኮትስ ወገኖችን አውቃቸዋለሁ። እነርሱን በደንብ አውቃቸዋለሁ፡ ደግሞም ለ—ለረጅም ጊዜ ጓ—ጓደኞቼ ሆነው ቆይተዋል።

17 ሮንዳ፡ ሮንዳ ረኔ። ሮንዳ፡ ወደ እኔ ትመጪያለሽ? ልክ ለጌታ ኢየሱስ እንደሰጠንሽ፡ ወዲያውኑ ለእናትሽ እ—እመልስሻለሁ። እንደው፡ እንዴት ያለች ጣፋጭ ናት!

አሁን ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

18 የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት እኔና ሽማግሌህ በወንጌል ተስማምተንና፡ በአንድነት አብረን ስንቆም፡ ይህቺ እናት ይህችን ትንሽ ሮንዳ ረኔን አደራ ለመስጠት ወደ አንተ አመጣች። ያሳድጓት ዘንድ፡ እነሆ በእቅፋቸው ስር ሰጥተሃቸዋልና፡ ከሁሉ በፊት ቀድማ ማድረግ የፈለገችው ለአንተ አደራ መስጠትን ነው። የጥንቱ እዮብ፡ ጌታ ነገሮችን ይሰጣል እንዳለው ነው። እግዚአብሔር ሆይ፡ እስከምትወስዳት ሰዓት ድረስ፡ በሰላም እንድትጠብቃት እንጸልያለን። እንዲሁም፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ስታድግ እውነተኛ የክርስቲያን ሕይወት ትኑር፡ ለሌሎች ምሳሌ ትሁን። ቤቷን ባርክ፡ በቅን ልብም፡ ስለ ሙሉ አገልግሎት፡ ለአንተ የተሰጠች ይሁን። አሁንም፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ህጻን ሮንዳ ረኔ ኮትስን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለአገልግሎት ሕይወት ለአንተ እንሰጣለን። አሜን።

በጣም ጥፋጭ! እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ።

19 እንዴት ነሽ! [እህቲቱ፡ "ሮበርት ፖል ሻሜል" አለች።—አርታዒ።] ሮበርት ፖል ሺን? ["ሻሜል።"] ሻሜል።

20 ታዲያስ፡ እስኪ... ገና ለጋም ነህ፡ በዚህ ላይ ብዙ ሁከት ልታስነሳ የምትችል አትመስለኝም። እንደዚያ'ማ አትሳቅብኝ። የምትስቅበት ነገር ከፈለግህ፡ እዚህ ተመልከት። ሮበርት ፖል፡ እንዴት ያለ የሚያምር ስም ነው!

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

21 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህቺ ወጣት ሴት ወደዚህ ስትመጣ፥ ለእኛም፡ ገና፡ ልጅ ናት። እግዚአብሔር ሆይ፡ እነሆ ይህንን ታናሽ ልጇን፡ ለአገልግሎት ሕይወት ለአንተ ትሰጣለች። እርሱም በትዳራቸው የተገኘ ፍሬና ውጤት ነው። እግዚአብሔር ሆይ፡ እኔና ሽማግሌህ በዚህ ታናሽ ልጅ ላይ እጃችንን ስንጭን፡ ሕይወቱ ለአንተ የተቀደሰ እንዲሆን፡ እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ ነገ ካለ፡ ወ—ወላጆቹ የሚሰሙትን ይህ መልእክት የሚሸከም፡ ይሁንልን፡ እግዚአብሔር ሆይ። ይሁንልን። በቤታቸውም ላይ በረከትህን እንድታፈስና፡ ሕፃኑም በእግዚአብሔር ምክርና ተግሣጽ እንዲያድግ፡ የ—የአንተ ተወዳጅ ደቀ መዝሙር እንዲሆን እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለአንተ እንሰጠዋለን። አሜን።

22 ታዲያስ፡ በጣም ግሩም ልጅ ነ—ነው። በቃ። አዎን፡ ጌታዬ። ከዚህ የበለጠ ተወዳጅ ነገር ልትጠይቁ አትችሉም፡ አይደል? ከዚህ ታናሽ ልጅ የበለጠ፡ በዚህ ዓለም ላይ ምንም ተወዳጅ ነገር የለም፡ በትክክል። ሁሉም ፈገግታ ነው! እንዴት ያለ ጣፋጭ ነው?

23 እነዚህን ሕፃናት መያዝ፡ ባለቤቴ የምትቀናበት አንዱ ነገር ነው። እነርሱን ማቀፍ ትወዳለች። እኔም እንዲሁ፡ እወዳለሁ፡ ነገር ግን ሁልጊዜ የምሰብራቸው ይመስለኛና እፈራለሁ። እነርሱ በጣም፡ ታውቃላችሁ፡ በጣም ቆንጆዎችና በቀላሉ የሚጎዱ-መሳይ ናቸው፡ ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ በእርግጥ ከእኛ ይልቅ ጠንካራ ና—ናቸው።

24 አሁን፡ እንደምወጣ ነግሬአችሁ ነበር… ደህና፡ ሰላሳ አምስት-ደቂቃ ብቻ ነው ያለኝ። መቸኮል አለብኝ፡ አይደል? እስኪ እንየው። እ—እ—እኔ ማንንም በተሳሳተ መንገድ ለመፍረድ፡ ወይም የተሳሳተ ነገር ለመናገር ፈልጌ አይደለም፡ ነገር ግን በጣም እሞክራለሁ፡ ምክንያቱም… ታውቃላችሁ፡ በጉዞው ላይ ወደ ፊት በጣም ከተጓዝን በኋላ፡ እንደ ቀድሞው ንቁ ሆነን አንቀጥልም፡ ታውቃላችሁ። ርቀቱ አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ ይሆናል፡ በተለይ በቀን ሁለት ወይም ሦስት አገልግሎቶች ሲኖሩ፡ እንዴ… ”

25 ዋናውን ክፍል የሚይዘው ደግሞ፡ እነዚያ ራእዮች ናቸው። መሰበክ እኔን አይጎዳኝም። ኦህ፡ ቀኑን ሙሉ እዚህ መቆየት እችላለሁ፡ ምንም አልሆንም፡ ነገር ግን እ… ብቻ ግን እነዚያ ራእዮች፡ ሰዎች ቃለ መጠይቆች ሲደረጉ፡ ማግኘት ያለባቸው ያ ስለሆነ። አያችሁ? እዚህ የሚመጡት ለዚያ ነው። እጅ በመጫን ብቻ ሊፈታ የሚችል ነገር አይደለም። ሥሩን፡ መጀመሪያውን፡ መንስኤው ምን እንደሆነ፡ ምን እንዳስነሣው፡ ከዚያም ከዚያ ለመውጣት ምን መደረግ እንዳለበት ማወቅ ያስፈልጋል። እዚህ የመጡት ለዚያ ነው።

26 አሁን፡ ስብሰባው የሚጀምረው፡ ከነገ ወዲያ ምሽት ላይ ነው… ወይም፡ አይደለም፡ ይቅርታ አርጉልኝ፡ እሮብ ማታ፡ በሽሬቭፖርት፡ ሉዊዚያና ነው። ከእናንተም መካከል በዚያ አካባቢ ወዳጆች ያሏችሁ ካሉ፡ ከሆነ፡ እንዲመጡ ንገሯቸው። ያንን ማግኘት ችለው፡ አዳራሹን ካላስፋት በስተቀር፡ የ—የሚጀምረው፡ ላይፍ ተበርናክል ውስጥ፡ ይመስለኛል፡ ይህም ተጨማሪ የመቀመጫ ቦታ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ዳሩ ግን ፎቅ ላይ ሰገነት አላቸው፡ ትልቅ ዋና ወለልም አላቸው፡ ከዚያም በታች ሌላ ወለል አለ። ስለዚህ፡ ምን ያህል ሰዎችን ማስተናገድ እንደሚችሉ በእርግጠኝነት አላውቅም፡ ነገር ግን…

ነገሩ በጣም አስቸጋሪ ከሆነ፡ ምናልባት ልክ ማዶ ያለውን አዳራሽ ልናገኝ እንችላለን፡ እርሱም... ምን ያህል ሰው እንደሚይዝ፡ እኔም አላውቅም። በዚያ አገልግሎቶች አድርጌ አውቃለሁ፡ ነገር ግን አላስታውስም። ይህ—አመታዊ ጉባኤ ነው።

27 ከሦስት ዓመት በፊት በዚያ ነበርኩ፡ በጌታም ስም፡ ሪቫይቫል ጀመርን፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮም፡ አላበቃም። በቋሚነት ብቻ ይቀጥላል፡ በቋሚነትም፥ በየቀኑ፡ ሰዎች ይመጣሉ፡ ይድናሉ፡ ይጠመቃሉ፡ እንዲሁም በዚያ መንገድ ከጌታ ጋር ይቀጥላሉ፡ አገልጋዮችና ሁሉም ነገር በቀጥታ እየገቡ ነው። እኛም... ልክ እንደዚሁ እስከቀጠለ ድረስ፡ እዚህም ለመቆየት ከቻልኩ፡ ሁልጊዜም ለመጎብኘትና፡ ጥቂት ቃላቶቼን ለመናገርና—ለመቀጠል እፈልጋለሁ።

28 አሁን፡ ያ ረቡዕ ይጀምራል፡ እሁድም ያበቃል። የክርስቲያን ቢዝነስ ሜን ቁርስ... የዚያን ሆቴል ስም... ረሳሁት... ይመስለኛል... ስሙም... በዚያ ስትደርሱ፡ ይነግሯችኋል። የነጋዴዎቹ ቁርስ ነው።

29 ባለፈው ጊዜ፡ በዚያ ለነበራችሁት ነጋዴዎች፡ ግሩም ጊዜ አሳልፈናል። ጌታ ከአንደኛው ከተማ፡ አንድ—መምህር አድኗል። ደግሞም፡ ኦህ፡ ምን እንደተፈጸመ አላውቅም። ስለ ደም ኪዳን በመስበክ፡ በዚያ፡ በጌታ ዘንድ ታላቅ ጊዜ ነበር። ስለዚህ እኛ... አይሁዶች የሚያውቁት ያንን ነው፥ እርሱም ደም ነው። “ያለ ደም መፍሰስ፡ ስርየት የለም፡” አያችሁ።

30 አሁን በቀጥታ ወደ ቃሉ እንሂድ፡ የገባሁትንም ቃል ለመጠበቅ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ።

31 አሁንም፡ የጌታ ፈቃድ ቢሆን አሁን፡ ከገና በኋላ ባለው እሁድ፡ በበዓላት እረፍታችሁ ላይ ሆናችሁ ወዲያ ወዲህ የምትሉ ከሆነና፡ መንገዱ የማያንሸራትት ከሆነ፡ እንዲሁም፡ እናንተ—እዚህ አካባቢ ቅርብ ከሆናችሁ፡ እባካችሁ፡ ጎራ በሉ። እኛም ከ—ከ—ከገና በኋላ ባለው እሁድ፡ እሁድ ጠዋት እዚህ አገልግሎት ለማድረግ አስበናል። ያን ጊዜ ቀኑ ምንድነው? [አንድ ሰው፡ “ሃያ-ዘጠኝ” አለ።—አርታዒ።] ሃያ-ዘጠኝ፡ ሃያ-ዘጠነኛው ቀን፡ እርሱም ከገና በኋላ ያለው እሁድ፡ ሃያ-ዘጠነኛው ቀን ነው። አሁን፡ እኛ እዚህ መሆን እንዳንችል፡ የሚያደርግ፡ ነገር፡ ከተከሰተ... ስለ ወደፊቱ ጊዜ አናውቅም፡ ታውቃላችሁ። ነገር ግን አንድ ነገር ቢከሰት፡ ከከተማ ውጭ የምትኖሩ፡ ወደዚህም የምትመጡት፡ እንደ እነዚያ፡ ከሜምፊስ እንደሚመጡት ወገኖች...

32 ወንድም አንግሬን **ሃው ግሬት ዛው አርት** ሲዘምር ለመስማት ፈልጌ ነበር። ደግሞም አላውቅም... ዛሬ ምሽት እዚህ አለ?

33 ስለዚህም፡ ሁልጊዜም፡ በጣም ብዙ ነገሮች አሉብኝ፡ ሁሉንም ማጠናቀቅ አልችልም፡ ሁሉንም ማጠናቀቅ አልችልም። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ እናንተን ወገኖች።

34 አሁን ለጥቂት—ለጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ አሁን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ። በዚያም፡ ቃላቶቹ ቢከሽፉ እንኳን፡ ይህ አይከሽፍም። በዚያም እግዚአብሔር ስለመቆየታችሁ፡ ዝም ብሎ ቃሉን ስለማዳመጣችሁ ብቻ ይባርካችኋል። “እምነት ከመስማት ነው፡ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት።” ልክ ነው? አሁንም እያሰብኩ ሳለ... እናንተም፡ ወደ ቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 6፡

ከቁጥር 60 ጀምሮ፡ እስከ ቁጥር 71 ድረስ፡ ያለውን አውጡ። ቅዱስ ዮሐንስ 6፥60።

35 አሁን ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ በመስኮት ወደ ውጭ እመለከት በነበረበት ጊዜ እያሰብኩ፡ ጀምበር ስትጠልቅም እያየሁና መላው ተፈጥሮ እንዴት ሕግ እንዳለው እየተመለከትኩ ነበር። የክረምቱ ወቅት ሲመጣም፡ የተፈጥሮው ሕግ፡ በራሱ መንገድ፡ የዛፉን ፈሳሽ፡ ወደ ዛፉ ሥሮች ያወርደዋል። ይቀበራል።

36 እዮብ እንደተናገረው፡ “ኦህ፡ በመቃብር ውስጥ በሰወርኸኝ፡ ቁጣህም እስኪያልፍ ድረስ በሰውር ስፍራ በጠበቅኸኝ።” አሁንም፡ ነገሩ ያ ነው፡ “በሰወርኸኝ!” አያችሁ፡ እርሱ—ተፈጥሮው፡ የዛፉ፡ ሕይወቱ ወደ ሥሩ ሲወርድ ተመልክቷል፥ ወንድም ዌይ። “ቁጣውም እስኪያልፍ ድረስ በዚያ በቆየሁ፡ ከዚያም በጠራኸኝና ጊዜ በቆረጥክልኝ።” አያችሁ?

37 ተፈጥሮ ሕግ አለው። የተፈጥሮ ሕግ አለ፥ ከዚያ የሚያመልጡበት ምንም መንገድ የለም። እርሱ የተፈጥሮ ሕግ ነው። ከዚያም የመንፈስ ሕግ አለ፥ እንዲሁም፡ ከእርሱም፡ የሚያመልጡበት ምንም መንገድ የለም።

38 ዛሬ ከሰዓት በኋላ ለአንድ ባልና ሚስት፡ ማንኛውንም ነገር፡ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት እንደማይቻል እየተናገርኩ ነበር። የሰው ልጆች ማጥፋት አይችሉም። ማፍረስ ይችላሉ፡ ማጥፋት ግን አይችሉም። አንድ ሰውም፡ “ታዲያ፡ አንድ ወረቀት ወስዶ ማቃጠልስ፡ ያ ያጠፋዋልን” አለ? አይደለም፡ ጌታዬ። የእሳቱ ሙቀት፡ ኬሚካሎቹን ብቻ ነው የሚለያየው። በመጀመሪያ ወደ ነበረበት ጋዝ፡ በቀጥታ ይመለሳል። ማጥፋት አይቻልም። ዓለምም ረዘም ላለ ጊዜ ቢቆይ፡ በዚያ ወረቀት ውስጥ የነበሩት ያው ጋዞች፡ ያ—ኬሚካሎቹም ተመልሰው፡ እንደገና ወረቀት ሊሆኑ ይችላሉ። በትክክል። ማጥፋት አትችሉም። በትክክል።

39 ታዲያ፡ አምላክ። ለሁሉም ነገር ትንሳኤ ካለው፡ ወደ ቀድሞው መመለስ ካለው፡ እንዲሁም መጥፋት ከሌለ፡ እንግዲያውስ የጻድቃንም ትንሳኤ ይኖራል፡ አዎን፡ እኛም እንመለሳለን። ነገሩ ይህ ብቻ ነው። ሌላ ምንም አማራጭ የለም። ብትቃጠሉም፡ ብትሰምጡም፡ ምንም ቢከሰት፡ ሊያጠፉት አይችሉም።

40 እግዚአብሔር ዓለምን ይሁን በማለት ወደ መኖር ሲያመጣው፡ እያንዳንዱ የእናንተ ክፍል እዚህ እንደነበረ አስታውሱ። የእናንተን አካል እዚህ አስቀመጠው ያኔ ነው። ከእግዚአብሔር በቀር ሊወስደው የሚችል ምንም ነገር የለም። ይህ ሁሉ እንደገና ወደ እጆቹ ይመለሳል። አያችሁ? እናም እርሱ ነው፡ እርሱ፡ ፈጣሪ፡ ቃል የገባው እርሱ ነው፡ ስለዚህ የዘላለም ሕይወት እንዳለ እርግጠኞች ነን። አሁንም በውስጣችን የማይሞት የዘላለም ሕይወት፡ ዘለአለማዊ የሆነ፡ ለዘላለም የሚኖር የማይጠፋ ሕይወት አሁን እንዳለን፡ በልባችን ውስጥ ማረጋገጫ አለን። እሺ።

41 ቅዱስ ዮሐንስ 6። አሁን ደግሞ በቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 6 እንጀምር፡ ከ 60 ኛው ቁጥር ጀምሮ።

**ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች፡ ይህንን በሰሙ ጊዜ፡ ሰምተውም፡ ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፥ ማን ሊሰማው ይችላል፡ አሉ?**

**ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ነገር እንደሚያንጎራጉሩ፥ በራሱ አውቆ... እንዲህ አላቸው፡** ይህ **ያሰናክላች**ኋልን?

**ታዲያ... የሰው ልጅ ቀድሞ ወደነበረበት** ሲወጣ **ብታዩ ምን ትላላችሁ?**

ያ—ያ... **ህይወት የሚሰጥ መንፈስ ነው እንጂ፥ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፥ ለእናንተ የነገርኳችሁ ቃል፡ መንፈስ ነው** (እርሱ ያ ነው)፡ **ሕይወትም ናቸው።** (ምን አለ? "እውነትና፡ ሕይወት እኔ ነኝ።")... **መንፈስ ናቸው፡... ሕይወት ናቸው።**

**ነገር ግን ከእናንተ መካከል የማያምኑ አሉ። ኢየሱስ የማያምኑት እነማን እንደሆኑ፡ አሳልፎ የሚሰጠውም ማን እንደሆነ ከመጀመሪያ ያውቅ ነበርና።**

**እርሱም፡ ስለዚህ** አልኳችሁ፡ **ከአባቴ ዘንድ ካልተሰጠው በቀር፡** ወደ **እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አላቸው።**

ከዚያም **ጊዜ ጀምሮ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፡ ከዚያም በኋላ ከእርሱ ጋር አልሄዱም።** ("የሚያስጨንቅ ንግግር፡" እያችሁ፡ ሊቀበለው አልቻለም።)

**ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ አላቸው፡** "እናንተ **ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?**

**ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡ ጌታ ሆይ፡ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል** አለህ **ብሎ መለሰለት።**

**እኛም አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ** እንደሆንክ **አምነናል አውቀናልም።** (ማይ!)

**ኢየሱስም መለሰለት፡ እኔ አሥራ ሁለታችሁን እኔ የመረጥኳችሁ፡ ከእናንተስ አንዱ ዲያብሎስ አይደለምን?**

**ይህንን ስለ ስምዖን ልጅ ስለ ይሁዳ አስቆሮታዊ ተናገረ፥ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ሆኖ፡ አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ ያለው እርሱ ነበርና።**

42 አሁን፡ ይህንን የዛሬ ምሽት ርዕስ ብሰጠው፡ ግማሿን ሰዓት ጠቃሚ ለማድረግ የምችለውን ያህል ብጥር፡ **ሦስት አይነት አማኞች፥** በሚል ርዕስ ላይ ለመናገር እፈልጋለሁ።

43 ይህንን አገላለጽ ደጋግሜ ተናግሬዋለሁ። በአሳቤም፡ "ታዲያ፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ አንድ ጊዜ በእርሱ ላይ እንደምሰብክ አምናለሁ።" ብዬ አሰብኩ።

44 የመጀመሪያዎቹ አማኞች፡ አስመሳይ-አማኞች፡ እንዲሁም የማያምኑት ናቸው። አሁን፡ ይህ በጣም ትልቅ ር—ር—ርዕስ ነው። ነገር ግን፡ እኛ ዛሬ ምሽት እዚህ እንደተቀመጥን ሁሉ፡ ያ ወገን ሁልጊዜም በአንድ ላይ ይሰበሰባል። ሰዎች በሚሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ፡ ይህንን ወገን እናገኘዋለን፡ ሁልጊዜም አሉ፡ ምናልባትም እስከ ጌታ መምጣት ድረስ ሁልጊዜም ከእኛ ጋር ይኖራሉ። ስለነዚህ ሦስት ወገኖች ስናገር፡ ዛሬ ምሽት፡ ራሳችንን እንድንመለከትና፡ በየትኛው ወገን ውስጥ እንዳለን እንድናይ፡ እፈልጋለሁ።

45 አሁን አስታውሱ፡ እዚህ ምናልባት ስናገር... ዛሬ ምሽት በዙሪያዋ፡ በግድግዳዎቿ እና በኮሪደሮቹ ላይ፡ እንደገና ለተሞላችው፡ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን ለዓለምም ጭምር እየተናገርኩ ነው። እያችሁ? በሁሉም የተለያዩ የዓለም ክፍሎች፡ በቴፖች አገልግሎት አማካኝነት፡ እነዚህ ቴፖች ይሰራጫሉ።

46 አሁንም ስለ ሦስቱ ልዩ ልዩ አማኞች ዓይነት መናገር እፈልጋለሁ። አሁን አስታውሱ፡ **አማኞች** ሆይ፡ የንግግሬ ርዕስ ስለ **አማኞች** ነው። ከእነርሱ መካከል አንደኛው እውነተኛ አማኝ ነው፡ ቀጣዩም አስመሣይ-አማኝ ነው፡ ቀጣዩ ደግሞ የማያምን ነው። እያችሁ?

47 አሁን፡ በመጀመሪያ ልንናገርበት የምንፈልገው ወገን፡ አማኙን ነው። ምክንያቱም፡ ቀዳሚ መሆን ያለበት እሱ ይመስለኛል፡ ምክንያቱም እርሱ በእውነት የሚያምን ነውና፡ እንግዲህ፡ እምነቱ ልክ እንደ ደቀ መዛሙርት እምነት ነው። ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ለምሳሌ እንጠቀማለን። አሁን፡ መጀመሪያ አማኞች ናቸው፡ እውነተኛ አማኞች። “እምነትም ከመስማት ነው፡ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡” የእግዚአብሔር ቃል፡ እርሱም ክርስቶስ። እያችሁ፡ አማኞች!

48 አሁን፡ ይህ ታላቅ አማኝ የተናገረው ይህን ታላቅ አባባል አስተውላችኋል? አሁን፡ አማኝ በዓለም ላይ ብልህ ለመሆን ብልጣ ብልጥ ሰው መሆን የለበትም። እነዚህ ሰዎች እንዲህ ልትሆኑ ይገባችኋል እ—እንደሚሉት ዓይነት ምሁር መሆን አይጠበቅበትም፥ ሆኖም አይደላችሁም። እ... ይህንን ንግግር የተናገረውን ሰው፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ራሱ “አላዋቂ” እና “ያልተማረ” እንደነበረ ይናገራል። ጴጥሮስ፡ በርግጥም እንደ ምሁር ሰው አልተቆጠረም።

49 በኢሳይያስ 35 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ “እውራ ጐዳናና፡ መንገድ ይሆናል፡ እርሱም፡ ‘የቅድስና መንገድ’ ይባላል። እርኩስትን የሚሰሩ አይለፉበትም።”

50 ዛሬ ከሰዓት በኋላ ከአንደኛው ዲያቆናት ጋር እየተነጋገርኩ ነበር፡ ስላለፉት ድልድዮችና፡ ስላለው አዲሱም ስናወራ ነበርን። እንዲህም አልኩት፡ “ዛሬ በውኃማ አካላትና በረግረጋማ ቦታዎች ላይ የሚዘረጉ፡ በርካታ ድልድዮች አሉ።” አክዬም፡ “ነገር ግን ከምድር እስከ ክብር የሚዘልቅ አንድ ታላቅ ድልድይ አለ፡ እርሱም፡ ‘የንጉሥ ጎዳና’ ይባላል። ርኩሰም የሆነ አያልፍበትም።” ልክ ነው። እርሱ በጌታችን በክርስቶስ የተገነባ መንገድ ነ—ነው፡ ከዚህች ምድር ወደ ሌላ አገር የተዘረጋ ድልድይ ነው፡ ርኩሰም የሆነ አያልፍበትም።

51 ይህ ያልተማረ ሰው፡ ጴጥሮስ፡ በ... አቅራቢያው ቆሞ፡ በዚያ ዘመን እግዚአብሔር፡ በመካከላቸው ነቢይ የሆነ አንድ ሰው እንደሚያስነሳ ቃል የገባላትን—ያንን በዚያ ዘመን ሙሉ በሙሉ የጸናውን ቃል አየ። በርካታ የዚያ አስመሳይነቶች ስለነበሩ፡ ሰምዖን ለማመን ተቸግሮ ነበር። ነገር ግን የዚያን ዘመን እውነተኛና፡ የተገለጠውን ቃል ባየ ጊዜ፡ እንዲሁም እርሱ በትክክል እንደተቆጠረ በሰማ ጊዜ፡ እ—እርሱ ማን እንደሆነ በእርግጠኝነት አመነ። ሲጠየቅም፡ “ጌታ ሆይ፡ ወደ ማን እንሄዳለን? ” ያለው፡ እርሱ ነበር።

52 ሕዝቡ በአማኞች፡ በማያምኑ፡ እና በአስመሳይ-አማኞች መካከል ሲ—ሲከፋፈሉ፡ በእነዚያ በአንድ ወገን ሰዎች መካከል ሦስቱም ዓይነቶች እዚያው

ቆመው ነበር፥ አማኞች፡ አስመሳይ-አማኞች፡ እና የማያምኑ፡ ልክ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ናቸው። ኢየሱስም ቃሉን በዚያ መንገድ በመናገሩ ምክንያት፡ ጉባኤውን ከፈለው። ነገር ግን ይህ መሆን ነበረበት።

53 በሽተኞችን እስከፈወሰ ድረስ ታላቅ ሰው ነበር፡ ሆኖም ነገሩ ወደ ትምህርቱና ወደ ትንቢቱ ሲመጣ፡ ገለባውን ከ—ከሰንዴው የለየው ያ ነበር። አያችሁ? ገለባው ሰንዴውን ብቻ ይሸፍነዋል። እርሱ ሰንዴው አይደለም። ሊጠቅም አይችልም። በውስጡ ምንም ነገር የለም። በውስጡ ሕይወት የለም። እርሱ ቅርፊቱ ነው፡ ከሰንዴውም ጋር ሊቆይ አይችልም። ከሰንዴውም ጋር ሊወርስ አይችልም። ስለዚህም... እኛ እየተናገርን ያለነው ስለ ፍሬው ብቻ ነው፡ ስለ ሰንዴው ፍሬ ልብ።

54 አሁን ልብ በሉ፡ ጴጥሮስ ያ መሲሁ እንደነበረ እርግጠኛ ሆኖ ነበር። ስለዚህ፡ ሌሎቹ ምንም ቢናገሩ ምንም ለውጥ አያመጣም። ካህናቱ ቢናገሩ ምንም ለውጥ አያመጣም። ቤተ ክርስቲያኑ የምትናገረው ለስምዖን ጴጥሮስ ግድ አልነበረውም። እርሱ ራሱ፡ እርግጠኛ ሆኖ ነበር።

55 በአንድ ሰፍራ፡ ኢየሱስ፡ እንዲህ አለው "ሰዎች ማን ይሉኛል" ብሎ በጠየቀው ጊዜ?

56 "አንዳንዶች 'ነቢይ ነው' ይሉሃል፡ አንዳንዶችም 'ቀድሞ ከተነሱት ከነቢያት አንዱ ነው' ይሉሃል፡ እንዲሁም—እንዲሁም 'ሙሴ፡' ወይም 'ኤልያስ፡' ወይም ከእነርሱ አንዱ ነህ።"

እርሱም፡ "**እናንተን** እጠይቃችኋለሁ። ምን ይመስላችኋል? "

57 ጴጥሮስም፡ "አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" አለ።

58 እርሱም እንዲህ አለው፥ "የዮና ልጅ፡ ስምዖን ሆይ፡ የዮና ልጅ፡ ብፁዕ ነህ፥ ሥጋና ደም ይህንን አልገለጠልህምና። ይህንን ከማንኛውም መጽሐፍ፡ ወይም ከየሐይማኖት መግለጫ፡ ወይም ከካቴኪዝም አልተማርከውም። አንተ... በሰማይ ያለው፡ አባቴ፡ ይህንን ገልጦልሃል።" እውነተኛ አማኝ ማለት ይህ ነው፥ የቃሉ መንፈሳዊ መገለጥ። አያችሁ? እንዲሁም-... "አንተ ስምዖን ነህ፡ ማንነቴን በተረዳህበት፡ በዚህ መገለጥ ዓለት ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም።" አያችሁ?

ስምዖን እንዲህ ማለቱ እውነት ነበር፡ "ወደ ማን እንሄዳለን? "

ኢየሱስም ዞር ብሎ እንዲህ አላቸው፡ "እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? "

59 እነርሱም አሉ፡ "ጌታ ሆይ፡ እና ወደ ማን፡ ወደ ማን እንሄዳለን? የሕይወት ቃል ያለህ፡ አንተ ብቻ ነህና። ብቸኛው አንተ ነህ።"

60 ምክንያቱም፡ የሕይወት ቃል በእርሱ ዘንድ ነበረ ብቻ ሳይሆን፡ እርሱ የሕይወት ቃል ነበር። አያችሁ፡ እርሱ የሕይወት ቃል ነበር፡ ስምዖንም ይህንን ሙሉ በሙሉ ተረድቶት ነበር። ይህንን በተረዳ ጊዜም፡ የሙጥኝ ብሎ እንዲይዝ ያደረገው ያ ነበር፡ ምክንያቱም እርሱ ያ ሕያው ቃል እንደነበረ ተገልጦለት ነበርና።

61 አሁን፡ በሌላ ሰው፡ ወይም በሌላ ነገር የተረታ ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን፡ ያ እውነተኛ አማኝ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ራሱ

ሲገልጥልህ፡ ቃሉም ግልጽ ሆኖ ሲታይህና፡ በማስረጃ ሲረጋገጥልህ፥ ያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ መጥቶ በዚያ ዘመን ውስጥ ይገባል፡ ለዚያ ዘመን ለሆነው ቃልም በመሆን፡ ግልጽ አድርጎ ያሳየዋል።

62 አንድ ሰው ይህንን ቢያውቅ ኖሮ ሉተርን ከማመን እንዴት ሊታቀብ ይችል ነበር? ሉተር ተሐድሶ አራማጅ ነበር። የሰውየው-መንፈስ ለተሐድሶው ወጣ። ዌስሊም፡ በተመሳሳይ መንገድ። ማመን ነበረባቸው። አያችሁ፡ ያ—ለቤተ ክርስቲያን ዘመን የተላከው መልእክት ነበር። በትክክልም የሆነው ያ ነበር። ሊሆን የነበረው ነገር ያ ነው። ማመን አለባችሁ።

63 እነሆ አሁን ደግሞ፡ ወደ ሎዶቅያ ዘመን ደርሰናል። በሎዶቅያም ዘመን፡ ክርስቶስ፡ ከቤተ ክርስቲያኑ እንደተወገደ ተምረናል፥ እንደውም ተመልሶ ለመግባት እየሞከረ፡ ደጁ ላይ እያንኳኳ ነው። ስለዚህ ይህ ሲሆን ስናይ፡ በየትኛው ዘመን ውስጥ እየኖርን እንደሆነ እናውቃለን።

64 እንዲሁ፡ ደግሞም፡ በዓለም ታሪክ ማብቂያ ላይ እንገኛለን። መጽሐፉ አሁን እየተጠናቀቀ ነው። እነሆ ከዕለታት አንድ ቀን የመጨረሻው መስመር ይጻፍባታልና፡ እርሷም ትዘጋለች፡ ከዚያም ጊዜ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም።

65 ታላቅ ትዕይንትም እየተዘጋጀ ነው። መላእክትም በሰማያት ላይ ቆመው፡ እየተመለከቱ ነው። ትዕይንት ምን እንደሆነ ታውቁታላችሁ። ተዋናዮቹ ዝግጁ ሆነዋል። ትወናቸውም ታዩታላችሁ።

66 ያ ክፉው ሲተውን ማየት ትችላላችሁ። የተውኔቱን ተንኮለኛ፡ ለማታለል በተንኮለኝነቱ እንዴት መድረኩ ላይ እንደመጣ፡ ታያላችሁ።

67 ነገር ግን የምትነጠቀው ቤተ ክርስቲያንም ራሷን ስታዘጋጅ ታያላችሁ። እጅግ ታላቅ ትዕይንት ነው። እዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስቀድሞ የተነገረውን ታላቅ ድራማ የእግዚአብሔር ህልውና እያጸና፡ ራሱን በትወና ሲያወጣ ታያላችሁ። እንዴት ያለ ጊዜ ነው የምንኖረው፡ ከሁሉ ይልቅ የከበረ ጊዜ! በየዘመናቱ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ይህንን ጊዜ ለማየት ናፍቀዋል። የቀድሞ ነቢያት ይህንን ሰዓት ለማየት ተመኙ፡ ዳሩ ግን አልታደሉም።

68 አሁን፡ ያ እማኝ ነበር። ምክንያቱም፡ አይቶታል። አምኖታልም። “አንተ ክርስቶስ፡ መሲሕ፡ የዘመናችን የእግዚአብሔር ቃል እንደሆንክ ሙሉ በሙሉ አምነናል፡ ያንን እናምናለን።” አያችሁ፡ እውነተኛ እማኝ ነበር ።

69 ወደ ቀጣዩ ባህሪ ከመሄዳችን በፊት፡ በጥቂቱ ጥቂት ተጨማሪ እማኞችን፡ በፍጥነት እንመልከት። ነቢዩን፡ ኖህን እንውሰድ። በዚያ ዘመን፡ ምናልባት፡ እርሻ አራሽ፡ ምናልባትም ገበሬ ነበረ። ነገር ግን የዚያ ዘመን ዘባቾችና ሃይማኖተኞች... ቤተ ክርስቲያኗ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ደርሳ በነበረበት ወቅት፡ እግዚአብሔርም ለኖህን፡ መርከብንም እንዲሠራ ነገረው። ኖህ በዚህ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ፈጽሞ አልተከራከረም። እርሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ፡ አመነ፡ ነገሮችንም ለማዘጋጀት በፍጥነት ወደ ሥራ ገባ።

70 እውነተኛ እማኝ እንዲህ ነው። በነገሩ ላይ አይከራከርም። ሙሉ በሙሉ ሰታምኑ፡ ነገሩ ያው ነው። ልክ እንደ ማንኛውም ሰው፡ እንደ ማንኛውም እምነት፡ እንደ ማናቸውም መንገድ። “እምነት ከመስማት ነው።” ዶክተሩ ምንም ይበል፡ ምንም ቢል በዚህ መጽናት ብቻ ከቻልክ! ይህም፡ ሰውዬው

የበሽታውን ምርመራ አድርጎልሃል፡ በመሣሪያዎቹና በእውቀቱ መጠን፡ ስለ ምን እንደሚናገር ምናልባት በትክክል ያውቃል፡ ነገር ግን ከመሞት በስተቀር የቀረህ ነገር የለም ይላል። ሆኖም፡ አንተ ትጸልያለህ፡ ወደፊትም ቆመህ ጤነኛ ወንድ ወይም ሴት ቆሞ ይታይሃል። አዎ፡ ነገሩ ያ ነው። ልክም እንደዚያው ነው። ስለምታምንበትም፡ ልክ እንደ ማናቸውም ነገር በእርግጠኝነት ወደዚያ ትሻገራለህ። እግዚአብሔር ተናግሮታል። እውነት እንደሆነ ታውቃለህ።

71 ልክ ያቺን ካንሰሩን ስላስመለሰችው ትንሽ ሴት አሰቡ፡ አያችሁ። ያ እንደሚሆን፡ በልቧ ውስጥ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አልነበራትም። ካንሰሩ ሞቶ ስለነበር፡ ተላቆ፡ ጠፋ። አያችሁ? ነገሩ ያው ነው። እናንተም እመኑት።

72 ልክ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ያ አባት፡ ትንሹን ልጁን ወደዚያ ክፍል እንዳመጣው ሁሉ። እርሱም አሁን በዚህ አዳራሽ ውስጥ የሆነ ቦታ ይገኛል። ትንሹ ልጅ ወድቆ፡ የማስታወስ ችሎታው አጥቶ። ምንም ነገር ማስታወስ አይችልም ነበር። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፡ ከፀሎት በኋላ፡ ስሙን ጠየቅኩት። ስሙንና፡ እድሜውን ነገረኝ፡ ልክ እንደማንኛውም ልጅ ሙሉ በሙሉ ጤነኛ ሆነ። አያችሁ? አነርሱ አመኑ። እግዚአብሔርም አንድ ነገር ሲናገር፡ ልክ እንደዚያ መሆኑ አይቀሬ ነው።

ኖኅም እግዚአብሔርን አመነ፡ ኖኅም እንደ አማኝ ተቈጠረ።

73 ዳንኤልም፡ ቤተ ክርስቲያን በባቢሎን በምርኮ በነበረችበት ጊዜ፡ እግዚአብሔርን አመነ። ምንም እንኳን እነርሱ እንዲህ ቢሉም፡ "አዋጅ እናወጣለን። እዚያ ካለው ቅዱስ ተብሎ ከተሰየመው ምስል በስተቀር፡ ወደ ሌላ አምላክ አይጸልዩም፡" ቅዱስ ሰው ይሁን፡ ወይም ማንም ይሁን። ዳንኤል ለዚያ ምንም ትኩረት አልሰጠም። እርሱ ነቢይ ስለነበረ፡ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ ነበር፡ ቃሉም ወደ እርሱ መጥቶ ነበርና። የቤተ መቅደሱ የመክፈቻ ስነ ስርዓት በተደረገ ዘመን፡ እንዲህ ተብሎ ነበርና፡ "ማንኛውም ሰው፡ በማንኛውም አገር ውስጥ በጭንቅ ላይ ቢሆን፡ ወደዚህ ቅዱስ ስፍራ ፊቱን አዙሮ ቢጸልይ፡ ከሰማይ ሰማው።" ዳንኤልም እግዚአብሔርን አመነ። እርሱ እውነተኛ አማኝ በመሆኑ፡ አንበሶች እንኳ ሊበሉት አልቻሉም። ይህ እውነት ነው፡ አያችሁ፡ እርሱ አማኝ ነበር። እውነተኛና ትክክለኛ ነገር በውስጡ ነበረው። እርሱ አማኝ ነበር።

ዳዊትም ቢሆን፡ የተናቀ ትንሽ ልጅ ቢሆንም፡ እርሱ ሌላኛው አማኝ ነበር።

74 ዳንኤል ከዘመኑ ቤተ ክርስቲያን ጋር አልተባበረም፡ ኖህም ቢሆን ከዘመኑ ቤተ ክርስቲያን ጋር አልተባበረም። በጭራሽ። እነርሱ እግዚአብሔር እውነት ነው ባለው ቃል ላይ የቆሙ አማኞች ነበሩ። ዘመናዊው ዓለም ምንም ቢል፡ እግዚአብሔር የተናገረው እውነት እንደሆነ ያምኑ ነበር። እውነተኛ አማኞች ማለት እነዚህ ናቸው።

75 ልክ ጴጥሮስና ሐዋርያት፡ እንዳደረጉት፡ እነርሱም የሕይወት ቃል በእርሱ ዘንድ እንዳለና እርሱ ራሱ የሕይወት ቃል እንደነበረ አመኑ። ዛሬም ቢሆን ያንኑ እውነት እምናለሁ። ከዚህ ውጪ ያለውና፡ ይህንን የሚጻረር ነገር ሁሉ ግን፡ ተቃራኒና የሞት መንገድ ነው። **ይህ** ብቻውን የሕይወት ቃል ነው፡ ክርስቶስም ራሱ ቃሉ ነው።

76 አሁንም፡ ዳዊት፡ ቀይና መልከ መልካም ወጣት ነበረ። በመጀመሪያ ደረጃ፡ ትንሽ በመሆኑ፡ ምክንያት ምናልባት በወንድሞቹ ይናቅ ነበር። የጦር ዕቃ ለመሸከም የሚያስችል ብቃት አልነበረውም። ወደ ጦርነት መሄድም አይችልም ነበር፡ ደግሞም በጣም ትንሽና ከሲታ ነበረ። ሆኖም፡ ግን፡ እንደ አማኝ፡ በዚያ ተገኘ።

77 በዚያም ምድረ በዳ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ (አንበሶች—ድቦችና ተኩላዎች ባሉበት አገር፡ አባቱ ይጠብቃቸው ዘንድ የሰጠውን፡ ጥቂት በጎች፡ በወንጭፍ እየጠበቀ ወዘተ)፡ ዳዊት ጥላማውን አረንጓዴ መስክ መመልከት ጀመረ፡ ለበግ በዚያ ጥላ ሥር መጠለልና፡ በፀሐይ ትኩሳት ወቅት መተኛት፥ ምን ያህል መልካም እንደሆነ ያውቃል፡ ጥሩና ቀዝቃዛ ውኃ መጠጣት ምን ማለት እንደሆነ ያውቅ ነበር፡ እርሱም፡ “ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደምትናፍቅ፡ አቤቱ አምላኬ፡ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች” አለ። አያችሁ? ጮኸ፡ ጸለየ።

78 አንድ ቀንም ድንገተ ነገር ተፈጠረ፡ አንበሳ ከበጎቹ አንዱን ነጥቆ፡ ሮጠ። እርሱም፡ “የፈጠረኝ አምላክ ከአንበሳው ይበልጣል” ብሎ አሰበ! አያችሁ? ወንጭፉንም አንስቶ፡ በትንሽ ድንጋይ አንበሳውን መትቶ ጣለው። አሁን፡ የአፍሪካ አንበሶች ያየ፡ ማንኛውም ሰው ካለ፡ እነዚያ በፍልስጥኤምና በእስያ ያሉትን ባለ-ጋማ ታላላቅ ፍጥረታት፡ ምን ዓይነት እንደሆኑ ያውቃል። ታላቁ ባለ ሶስት መቶ ማግነም ጥይት እንኳ ሊጥለው የማይችለውን፡ እርሱ ግን በድንጋይ ጣለው። አንበሳውም በተነሳበት ጊዜ፡ ጺሙን ይዞ ገደለው። እሱ የሚናገረውን የሚያውቅ ሰው መሆኑ ምክንያት ይህ ነው፥ የግል ልምምድ ነበረው። በቃሉ ላይ፡ እግዚአብሔርን ፈትኖት ነበርና።

79 እ—እርሱም ጎልያድን አልፈራውም፡ ምክንያቱም፡ ያልተገረዘ ነበረና። እርሱ፡ ፈጽሞ አማኝ አልነበረም፥ ጎልያድም በወጣ ጊዜ በአማልክቱ ሰም ረገመው።

80 ጎልያድም፡ ከእርሱ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ፥ አሥራ አራት-ኢንች ርዝመት ያላቸው ጣቶች ያሉት፡ ታላቅ ግዙፍ ሰው ነበር። እንግዲህ፡ ጣቶቹ ያን **ያህል** ረጃጅም ነበሩ፡ አያችሁ፡ አሥራ አራት-ኢንች ጣቶች ያሉት፡ ተዋጊ። የለበሰውም የሰንሰለት ጥበብ ጥሩር፡ ምናልባት ሦስት መቶ ፓውንድ፡ ወይም ከዚያ በላይ፡ ይመዝን ነበር፡ አያችሁ። የራስ ቁር፡ እና ታላቅ... ምናልባትም የአንድ-ኢንች-እና-ተኩል ውፍረት ያለው ብረት ነበረው። እንደዚያ ያለ ይህ ታላቅ ግዙፍ ሰው፡ ወደ ሃያ ጫማ ገደማ እንደሚረዝም የሚነገርለትን የሸማኔ—መጠቅለያ የሚመስል ነበረው። ባለ ሃያ-ጫማ ጦር በእጁ ይዞ ይራመድ ነበር። አሁን ማንኛውም ሰው እንዴት... እንደዚያ ያለ ሰው፡ ቆሞ የመጡበትን አስራ ሁለት ሰዎች በየተራ እያነሳ፡ **እንደዚያ** ሊወረውራቸው ይችላል። እንዴት ያለ ታላቅ ተግዳሮት!

81 እዚያ ቆሞ፡ ራሱን እያመጻደቀ፡ ሲፎክር፡ እዚያም ነበር። የ... ዕድሉ ዝቅ ያለ በሚመሰልበት ጊዜ፡ አያችሁ፡ እርሱ፡ “ይሁን... ምንም ደም አይፍሰስ” አለ። “አንድ—አንድ ሰው መጥቶ ይዋጋኝ፡ ከዚያም እኔ ካሸነፍኩ፡ እናንተ ሁላችሁም፡ ለእኔ ትገዛላችሁ፥ ከዚያም እናንተ—እናንተ—እናንተ ካሸነፋችሁ፡ እኛ እንገዛላችኋለን” አለ። አያችሁ፡ ዲያብሎስ በእናንተ ላይ ብልጫ እንዳገኘ ሲያስብ፡ አያችሁ፡ መፎከር የሚወደው ያኔ ነው። ዳሩ ግን የተሳሳተውን ሰው

አገኘ። በሀገሪቱ ውስጥ ካለው እጅግ ትንሹን ሰው፡ ትንሽ፡ ትከሻው-የጎበጠ፡ ቀይ-መሳይ ሰው አገኘ።

82 እርሱም፡ “ምን ለማለት ፈልጋችሁ ነው፡ ይህ ያልተገረዘ ፍ—ፍልስጥኤማዊ፡ የሕያው እግዚአብሔር ሰራዊትን እንዲህ ሲገዳደር ዝም ብላችሁ እዚህ እንቆማለን ልትሉኝ ነውን? ” በቃ፡ እጅግ ተገረመ! ለምን? ለምን? እርሱ አማኝ ስለነበር። ሌሎቹ ደግሞ አስመሣይ-አማኞች ነበሩ። እያችሁ? እያችሁ፡ እርሱ እውነተኛ አማኝ ነበር። እርሱም፡ “እናንተ ከፈራችሁ፡ ሄጄ እገጥመዋለሁ” አለ። እያችሁ? እንደዚያ ላለ ትንሽ ልጅ እንዴት ያለ ትልቅ ተግዳሮት ነው! ስለዚህም እርሱ አማኝ በመሆኑ፡ እግዚአብሔር እንደሚያደርጋት የሚያውቃትን ነገር በትክክል አደረገ። እርሱ...

83 ይህ ያልተገረዘ ፍልስጤማዊ በአማልክቱ ስም፡ እንዲህ በማለት ተራገመው፡ “እንዲህ ልትገጥመኝ ስትመጣ፥ እኔ ውሻ ነኝን? ይኸውልህ፡” አለው፡ “በጦሬ ጫፍ ላይ አንስቼ፡ በዛፉ ላይ እሰቅልሃለሁ የሰማይ ወፎችም ሥጋህን እንዲበሉ አደርጋለሁ።” ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ እንዴት ያለ አስፈሪ ሰው ነበረ!

84 ዳዊትም፡ “አንተ በሰይፍና በጦር፡ በጥሩርም ትገጥመኛለህ። በፍልስጤማዊ ስምም ትመጣብኛለህ። ዳሩ ግን፡ እኔ ያለ ሰይፍና ያለ ጦር፡ ያለ ጥሩር፡ ነገር ግን በእስራኤል አምላክ በጌታ በእግዚአብሔር ስም እገጥምሃለሁ” አለው።

85 ይኸው ነው። አማኝ ማለት ይህ ነው። ምሽጉ ያ ነው። ጋሻው ነው። መከላከያው ነው። አሜን! የቤተ ክርስቲያን ጋሻም ይህ ሊሆን ይገባል። የማንኛውም አማኝ፡ ጋሻው ይህ ነው። ምንም ነገር ቢከሰት፡ ዓለም ምንም ቢል፡ ሌላም ቢሆን፡ ጋሻችሁ የእስራኤል አምላክ ጌታ እግዚአብሔር ነው። አለቀ። “የኢየሱስ ክርስቶስ ስም የጸና ግንብ ነው፡ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ያመልጥበታል።” ጋሻችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

86 ልብ በሉ፡ ነገሩ በሆነ ጊዜ፡ ምን እንደተፈጠረ እናውቃለን። ያ ግዙፍ ሰው የ—የ—የፊቱን ራስ ቁር ዝቅ ባደረገበት ጊዜ፡ ዳዊት እርሱን የሚመታበት አንድ ጠባብ ቀዳዳ ብቻ ነበረው። እርሱ ሊመታ የፈለጋት ቦታ ግንባሩ ላይ ብቻ ነበርና። ወደ—ግዙፉ ሰው ከመቅረቡ በፊት፡ እግዚአብሔር የመግደያው ምልክት አስቀድሞ አሳየው፡ እርሱም ግዙፉን ገደለው። እያችሁ? ያደረገው እግዚአብሔር ነው። አሁን፡ እርሱ አማኝ እንደነበረ አይተናል።

87 አሁን፡ ሌላኛው አማኝ ደግሞ አብርሃም ነበረ፡ እርሱም ከ... ከለዳውያን የኡር ከተማ ሰው ነበረ። በአካላዊ ሁኔታ፡ ፈጽሞ የማይቻልን ነገር... እንዲያደርግና እንዲያምን ተጠርቶ ነበር። ሮሜ 4 እንደሚለው፡ “በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ላይ አልተጠራጠረም፡” “ነገር ግን እግዚአብሔርን እያመሰገነ፡ በእምነቱ በረታ።”

88 አብርሃም ሰባ-አምስት ዓመት ሲሆነው፡ ሚስቱ ደግሞ ስልሳ-አምስት ዓመት ስትሆን፡ ገና ከወጣትነታቸው ጀምሮ አብረው ይኖሩ ነበር። ግማሽ-እህቱ ነበረች፥ ወጣት ወንድ እና ወጣት ሴት ነበረች። ያም ሆኖ፡ ምንም ልጅ ሳይወልዱ፡ አብረው ኖሩ። እግዚአብሔርም አብርሃምን፡ “ከማያምኑት ተለይተህ ውጣ” አለው። እግዚአብሔር ሁልጊዜ፡ መለየትን ይጠይቃል።

“ከማያምኑት ተለይተህ ተከተለኝ፡ የብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁ። ይህንን አስቀድሜ አድርጌዋለሁ።”

89 አብርሃምም አመነ። አማኝ ማለት ያ ነው። “ጌታ ሆይ፡ ይህንን እንዴት ታደርገዋለህ? ” ብሎ ፈጽሞ አልጠየቀም። እግዚአብሔር እንደሚያደርገው ተናገረ፡ ያም ድምዳሜው ሆነ።

90 የመጀመሪያው ወር ባለፈ ጊዜ፡ ሳራ አሁንም... የወር አበባዋ ቆሞ ነበር። “የተለየ ነገር አለ? ”

“ምንም ነገር የለም።”

91 አብርሃም ግን አሁንም አመነ። ከሃያ-አምስት ዓመታት በኋላም፡ አሁንም ምንም ለውጥ አልነበረም፡ ዳሩ ግን አብርሃም አሁንም ያምን ነበር። አማኝ ማለት ያ ነው። አስመሳይ-አማኝ አይደለም። አማኝ ያ ነው። ከሃያ-አምስት ዓመታት በኋላ፡ አብርሃም ከፊት ይልቅ በረታ። “እግዚአብሔርን አመነ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።” ምክንያቱም እርሱ-... እውነተኛ አማኝ ማለት ያ ነው።

92 አሁን፡ ከአፍታ በኋላ በየትኛው ክፍል ውስጥ እንዳላችሁ ራሳችሁን እንድትመረምሩና እንድታዩ አደርጋለሁ።

93 አብርሃም ምን አደረገ? የማይቻለውን ነገር እያለ፡ “በእግዚአብሔር ተስፋ አልተጠራጠረም።”

94 ዕድሜው፡ ሰባ-አምስት ዓመት የሆነው ሰው፡ ሰልሳ-አምስት-ዓመት-ከሆናት ሚስቱ ጋር፡ ወደ ሐኪም ሄደው፡ “በሆስፒታል፡ ዝግጅት ማድረግ እንፈልጋለን። ልጅ ልንወልድ ነው” ቢሉ ምን ያደርግ ነበር? ከዚያም፡ ከሃያ-አምስት ዓመታት በኋላ፡ መጥተው፡ “ዶክተር ሆይ፡ አሁንም ሆስፒታሉን ስራ ላይ ነውን” ቢሉትስ? እያችሁ? እያችሁ?

95 ይህ ቂል እንድትሆኑ ያደርጋል። ውሳኔዎቻችሁ ለዓለም፡ እንግዳ ይሆናሉ። ነገር ግን ምንም ያህል እንግዳ ቢመስልም፡ አማኝ ነው። ይህም፡ “እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ነገር ሊፈጽም እንዲችል ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነበር፡” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ።

96 ይህ ዛሬ ከሰዓት በኋላ የእያንዳንዱ አማኝ ሰኬት ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር ያደርገዋለሁ ያለውን ቃሉን ሁሉ ሊፈጽም የሚችል ነው። የሐይማኖት ተቋማት ምን እንደሚሉ ግድ አይሰጠኝም፡ ቃላቸው፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል፡ ይህ ሁሉ አእምሮን ማንበብና፡ ሟርተኝነት ነው። እ... ” የሚሉትን ቃላት ግድ አይሰጠኝም። አሁንም እምናለሁ። ጠመንጃው ኢላማ ላይ ካነጣጠረ፡ ኢላማውን ይመታል። አማኝም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከተስማማም፡ ያንኑ ኢላማ እንደሚመታ እምናለሁ። ከእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ ቃል የተገባ ከሆነ፡ በድጋሚ ያደርገዋል። በዚህ ላይ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ። ማለትም፡ በዚህ ዘመን መሆን ያለበትን ነገር ሰናይ፡ በዚሁ ዘመን መሆን አለበት። እነዚህ ነገሮች መፈጸም አለባቸው።

97 ያቺ ሙሽራ ተጠርታና ተመርጣ፡ በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ስትጻፍ፡ ከሰማይ ዘንድ ድምፅ እንደሚመጣ የማምነውም በዚሁ ምክንያት ነው ያም ድምፅ ያቺን ሙሽራ ከምድር የሚወስዳትን የቅዱስ መንፈስ ጥምቀት፡

በንጥቀት ጸጋ ያጐናጽፋታል። እግዚአብሔር ቃል ገብቶታል። ሰንት ሳይንቲስቶችና፡ ሰንት ጠፈርተኞች ቢከተሉት፡ ወይም ሌላው ነገር ምንም ይሁን፡ ምን ያህል ሚሊዮን ማይሎች ማየት ቢችሉም፥ ግድ አይሰጠኝም። ሰማይ አለ፡ በዚያም ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ራሱ ለመውሰድ በአካላዊ መልክ የሚመጣ እውነተኛው ኢየሱስ ክርስቶስ አለ። ታሪኩ ምንም ያህል ያረጀ ቢመስልም፡ አሁንም እውነት ነው። እግዚአብሔር ተናግሮታል። አማኞች የሚያምኑት ይ—ይህንን ነው።

98 እግዚአብሔርም፡ "ደዌሽን ሁሉ የምፈውሰ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። እኔ እግዚአብሔር ነኝ አልለወጥምም" ብሏል። አሜን! እግዚአብሔርም ቃል ነው። እግዚአብሔር የማይለወጥ ከሆነ፡ ቃሉ እንዴት ሊለወጥ ነው? አያችሁ? "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ አልለወጥምም።" ቅዱሳት መጻሕፍትም ይመሰክራሉ። እግዚአብሔር ራሱ፡ ተናግሯል። እሱ የማይለወጥ ከሆነ፡ እርሱ ቃል ነው። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" የማይቀየር ቃል! "ቃልም ሥጋ ሆነ፡ በመካከላችንም አደረ።" አሜን! አዎን፡ ወዳጄ።

99 እግዚአብሔር በየዘመናቱ፡ ግለሰቦችን አስነስቷል፥ ቃሉ በጊዜያዊነት የመጣባቸው ሙሴ፡ ሕዝቅኤል፡ ኤርምያስ፡ ኢሳይያስና፡ ኤልያስ፡ ሁሉ፡ አልፈዋል። ሙሉውን ቃል ግን በዚህ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጠ። እርሱም፡ በመለኮት ሙላት ሁሉ በሥጋ እግዚአብሔር—እግዚአብሔር ነበረ። በዚያ ሥጋ ሆነ። ያንን ቃል በቃል፡ አምናለሁ።

ኢዮብ፡ ሌላኛው አማኝ ነበረ።

100 አንዳንድ ጊዜ፡ አማኞች ይፈተናሉ። አንዳንድ ጊዜ ብቻ አይደለም፥ ሁልጊዜም ጭምር ነው! "ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ ልጅ ሁሉ መገሰጽ፡ መፈተንና-መታረም፡ አለበትና።" አስታውሱ፡ ፈተናዎቹ፡ አቧራማ መንገዶችና፡ የሰደቱን ትኩሳት፡ ነገር ግን የልባችሁ ታማኝነት ያንን ቁስ እስኪዘጋጅ ድረስ ይቀጠቅጣል። የእግዚአብሔር ልጆች በቃሉ ላይ በትክክል የተገነቡ ናቸው፡ ምክንያቱም ሕያው ምሳሌዎች ናቸውና፡ የእግዚአብሔርም ቃል በእነርሱ ውስጥ ይኖራል። አያችሁ? ፈተናው የሚመጣው እናንተን ለማናወጥ፡ እስከ ታችኛው ክፍል ድረስ፡ ለመፈተንና በየትኛው ቦታ ላይ እንደምትቆሙ ለማየት ነው። ወደ እግዚአብሔር የሚመጣውን ልጅ ሁሉ ይፈትኑታል፡ ይሞክሩታል።

101 ኢዮብ በፈተናዎችና በመከራዎች ውስጥ አልፏል። ልጆቹ ተወሰዱ፤ ሌላው ነገር ሁሉ ተወሰደ። የቤተ ክርስቲያን አባላት መጥተው፡ ሰዉር ኃጢአተኛ እንደነበረ ከሰሱት፡ በእርሱም ላይ የሚቻለውን ሁሉ ለመናገር ሞከሩ፡ ነገር ግን እርሱ ለምንም ነገር አልሰማቸውም ነበር። የእግዚአብሔርን መሰፈርት እንዳሟላ ያውቅ ነበር። ሰይጣን ሊፈትነው መሞከር እንደማያስፈልገው ያውቅ ነበር። እርሱ ዲያብሎስ እንደነበረ ያውቅ ነበር። ሰይጣንም በሽታውን ያመጣበት እግዚአብሔር እንደሆነ እንዲያምን እስካደረገው ድረስ፡ ኢዮብን ማሸነፍ ይችል ነበር። ነገር ግን ኢዮብ ያንን መገለጥ በተረዳ ጊዜ፡ ያደረገው እግዚአብሔር እንዳልነበረ አወቀ! እርሱን የተሻለ ለማድረግ በፈተና ውስጥ እንዲያልፍ ብቻ አድርጎታል። ያደረገው እግዚአብሔር አልነበረም። ያደረገው ሰይጣን ነበረ።

102 ዛሬም እንዲሁ ነው። እርሱ እነዚህ ፈተናዎችና ነገሮች አምላክህ ሊቀጣህ ፈልጎ የሚያመጣብህ እንደሆኑ ሊነግርህ ይሞክራል። እንደዚያ ግን አይደለም። አይ፡ ጌታዬ። ያንን እያደረገ ያለው ሰይጣን ነው፡ እግዚአብሔርም አንተን ለማጠንከር፡ ይፈቅድለታል፥ በዚህ ምድር ነገሮች መ—መታሰርህን፡ ወይም መዝገብህ በሰማይ መሆኑን፡ ለማየት እንዲረዳህ ነው። “መዝገብህ ባለበት ስፍራ፡ ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።” ትክክል። ልብህ ያለው መዝገብህ ባለበት ስፍራ ነው።

103 ኢዮብም፡ ተፈትኖ ሳለ፡ ሆኖም፡ “የሚበዠኝ ሕያው እንደሆነ፥ በመጨረሻውም ዘመን በምድር ላይ እንደሚቆም አውቃለሁ። ምንም እንኳን የቆዳዬ ትሎች ሰውነቴን ካጠፋ በኋላ… ”

104 አስተውላችኋል? የቆዳ ትሎች አስቀድመው በውስጡ እንደነበሩ። የእናንተም የቆዳ ትሎች በውስጣችሁ አሉ። ምንም አየር በማይገባበት ወይም በማንኛውም ሁኔታ፡ በታሸገ-ሳጥን ውስጥ ብትገቡም እንኳ፡ የቆዳ ትሎች ቀድሞውኑ አሉ። እዚያው በውስጣችሁ አሉ፡ በማንኛውም ጊዜም ወደ ሥራ ለመሰማራት ዝግጁ ናቸው። ቄሳርን አስታውሱ፡ እርሱ በጎዳና ላይ እያለ ነበር የተላው። በዚያው በጎዳና ላይ ትሎች በሉት፡ የራሱ የቆዳ ትሎች። እነርሱ ዝግጁ ሆነው፡ በዚያ አሉ።

105 “የቆዳዬ ትሎች ሰውነቴን ካጠፉት በኋላ፡ በሥጋዬ ግን እግዚአብሔርን እያለሁ” አለ። አሜን! ልታጠፉት አትችሉም። ምንም እንኳ የቆዳ ትሎች ቢበሉትም፡ አሁንም ተመልሶ ይመጣል። “እነሆ እኔ ራሴ አየዋለሁ። ዓይኖቼም ይመለከቱታል፡ የሌላም አይደለም።” ይህንን ተናግሯል፡ ኢዮብ። ለምን? እርሱ አማኝ ነበርና። በመከራ ጊዜ አማኝ ነበር። ሰደት ውስጥ፡ አማኝ ነበር። እውነተኛ አማኝ ነበር።

106 ዮሴፍም፡ ሌላኛው አማኝ፡ የሆነው ከመሆን በቀር ሌላ ሊሆን አይቻለውም። እርሱ ነቢይ ነበርና። እግዚአብሔር ነቢይ አደረገው። ከወንድሞቹ የተለየ መሆን አልፈለገም፡ ሆኖም የተለየ ነበር። የሆነውን እንዲሆን ያደረገው እግዚአብሔር ነው። የእርሱን ስፍራ ሊተካ የሚችል ሌላ አልነበረም።

107 ማንም ሰው ስፍራችሁን ሊተካ አይችልም፡ ምንም ያህል ታናሽ ነኝ። ብትሉም፡ “እኔ የቤት እመቤት ነኝ” ብትሉም። ማንም ሰው ስፍራችሁን ሊተካ አይችልም። ማንም የእናንተን ስፍራ ሊወስድ እስከማይችል ድረስ፡ እግዚአብሔር፡ በታላቅ አሠራሩ፡ የክርስቶስን አካል፡ በሥርዓት፡ አስቀምጦታል። የእኛ የአገልጋዮች፡ እኔ የቢሊ ግርሃምን ስፍራ መተካት በቻልኩ ብለን እንመኛለን፡ ይህንን ማድረግ ግን አንችልም፥ ነገር ግን፡ ቢሊም ቢሆን የእኛን ስፍራ መውሰድ እንደማይችል፡ አስታውሱ። አያችሁ፡ ሁላችንም የራሳችን ስፍራ አለን፡ አንዳንዶቻችን ወንጌላውያን ነን፡ አንዳንዶቻችን ነቢያት፡ አንዳንዶቻችን አስተማሪዎች፡ አንዳንዶቻችን ፓስተሮች ነን፡ ምንም ብንሆን፥ አንዳንዶቻችን የቤት እመቤቶች፡ አንዳንዶቻችን መካኒኮች፡ አንዳንዶቻችን ገበሬዎች፡ ምንም ቢሆን፡ እግዚአብሔር በስፍራችሁ አስቀምጧችኋል። አያችሁ?

108 ዮሴፍ ነቢይ ነበር። ሕልሞችን መተርጎም ስለሚችል ዝም ማለት አልቻለም ነበር። ራእዮችን ስለሚያይ ዝም ማለት አልቻለም። ምን ያህል ታማኝ እንደነበረ ተመልከቱ። ከወንድሞቹ ጋር ያለውን ኅብረት ቢያሳጣውም እንኳ፡ እርሱ ታማኝ ነበር፡ ምክንያቱም እነዚያን ሕልሞች ያምን ነበርና። እነዚያ ነዶዎች ሁሉ፡ ለእርሱ እንደሚሰግዱለት፡ ያየውን ሕልም፡ አመነ። ስለ አመነበትም ነገሩ ተፈጸመ። እርሱ እውነተኛ አማኝ ነበር። እንዴት…

109 አምስት ደቂቃዎች፡ እና አሰር ገጾች አሉኝ፥ አሁን ልብ በሉ፡ ልብ በሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እዚህ ተጽፏል። ያቺ ሴት…

110 ናትናኤልም፡ አማኝ ነበር። ልክ ነው? ናትናኤል፡ የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ፥ በእርሱም ላይ በሠራ ጊዜ፡ ኢየሱስ ማንነቱን በነገረው ጊዜ፡ እ—— እርሱ "በእውነት የእስራኤል ሰው" እንደሆነና፡ "ተንኮልም" እንዳልነበረበት፡ ከዕለታት በፊት የት እንደነበረ፡ "ከዛፍ ሥር ሲጸልይ" እንደነበረ በነገረው ጊዜ። ፊልጶስ ሲጠራው——አየው። አማኝ ነበር።

111 በዚያ ቆመው የነበሩ ብዙዎች፡ "ይህ የጋኔን መንፈስ ነው። ሰይጣንም መለኮታዊ ፈውስ ያደርጋል፡" አሉ። ያ ያለፈበት ሰይጣን ዛሬም ቢሆን አልሞተም። እነርሱ ሰይጣን መለኮታዊ ፈውስ ያደርጋል ብለው ያምናሉና።

112 ኢየሱስ፡ "ሰይጣን ሰይጣንን ሊያወጣው ከቻለ፡ መንግሥቱ ተከፋፍላለች፡ መንግሥትም ልትቆም አትችልም" አለ። አያችሁ? ሰይጣን፡ እ… አያደርገውም። ስለዚህ፡ ሰይጣን ሰይጣንን ሊያወጣ አይችልም።

113 ስለዚህ ናትናኤል አማኝ ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆኖ ሲያይ፡ እርሱ አማኝ መሆኑን ሰላረጋገጠለት፡ እንዲህ አለ፡ "አንተ… መምህር ሆይ፡ አንተ ክርስቶስ ነህ። አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ።" አመነ።

114 በውኃ ጉድጓድ አጠገብ የነበረችው ሴት ያንን ባየች ጊዜ፡ አመነች። አማኝ ነች።

ዕውሩ በርጠሜዎስም… አንዲት ሴት በአጠገቡ ባለፈች ጊዜ…

115 ሁሉም ሰው ይጮኽ፡ ይንጫጫም ነበር። አንዳንዶቹ፡ "ሁሉም በየፊናው… ሙታንን እንደምታስነሳ ሰምቻለሁ። እዚህ ላይ በሙታን የተሞላ መቃብር አለ፥ ናና አስነሳቸው። ሰታደርገው እንይህ" ይሉ ነበር። አያችሁ፡ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፡ እነዚህ ድንጋዮች ዳቦ እንዲሆኑ እዘዝ" ያለው፡ ያው ሰይጣን ነው። ፊቱን በጨርቅ ሸፍኖ፡ ራሱን እየመታ፡ አንዱ ለአንዱ፡ በትሩን እያቀበለ… እንዲህ ያለው ያው አካል፡ "አሁን፡ ማን እንደመታህ ብትነግረን፡ እናምንሃለን፡" ያለው። እነዚያ ወታደሮች፡ አያችሁ፡ ያፌዙበት ነበር። ዕጣው ፈንታው፡ ፈጽሞ ያበቃለት ይመስል ነበር።

116 ነገር ግን አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜም በሰፍራው አለ። አያችሁ? እርሱ በማንኛውም ጊዜ፡ በዚያ ዝግጁ ነው።

117 አሁንም ኢየሱስ፡ "አባቴን ልለምነው እርሱም ወዲያውኑ አሥራ ሁለት ክፍለ ጦር መላእክት ይልክልኛ ይችል ነበር" አለ። አቤት፡ አንዱ መልአክ ምን ሊያደርግ ይችል ይሆን? አያችሁ? ነገር ግን፡ ተመልከቱ፡ ነገር ግን በትእዛዙ ብቻ አሥራ ሁለት ክፍለ ጦር መላእክት ሊልክ ይችል ነበር። ነገር

ግን የሚሠራው ሥራ ነበረው። የሚያደርገው ነገር ነበረው። በዚያ ውስጥ ማለፍ ነበረበት።

118 እናንተም የምታደርጉት ነገር አላችሁ። እግዚአብሔር እናንተ የምታደርጉት ነገር አዘጋጅቶላችኋል። ምናልባት የልብ ስብራትና ችግሮች ይኖሩባችሁ ይሆናል፡ ምናልባትም አንዳንድ ብስጭቶች ያጋጥሟችሁ ይሆናል፡ ነገር ግን እነርሱን ለማምለጥ እንጸልያለንን? የለም። "ጌታ ሆይ፡ ምንም ቢሆኑም፡ በእነዚያ መካከል አሳልፈኝ። ምንም ይሁን ምን፡ ከእነሱ እንድሸሽ አታድርገኝ። ለእኔ የተዘጋጁ ከሆኑ፡ በውስጣቸው እንዳልፍ ጸጋህን ብቻ ስጠኝ። አለቀ።"

119 አሁንም ልብ በሉ፡ ዕውሩ በርጠሜዎስ፡ እርሱ፡ እንደሚያውቀው "ይህ የገሊላው ነቢይ ነው። እርሱ የዳዊት ልጅ ነው። እናምናለን" ተብሎ፡ እንደተነገራቸው ያውቅ ነበር። ከአማኞቹ አንዳንዶቹ ይህንን ነግረውት መሆን አለበት። "እኛ አማኞች እርሱ ያ... ያ የዳዊት ልጅ እንደሆነ እናውቃለን።"

120 እርሱም፡ እንዲሁ ከሆነም፡ ቃሉ እንደነበረ ያውቅ ነበር። ቃሉ እንደነበረም ካወቀም፡ የልብን አሳብ መመርመር እንደሚችልም ያውቅ ነበር፡ ስለዚህም፡ "የዳዊት ልጅ ሆይ፡ ማረኝ" ብሎ ጮኸ። የማያምኑትም **ይህንን፡** እና **ያንን** እያሉ ይጮኹ ነበር፡ እነዚያ የቤተ ክርስቲያን አባላት። ይህ ዕውሩን በርጠሜዎስን በጭራሽ አላቆመውም። እርሱም፡ "ኢየሱስ ሆይ፡ የዳዊት ልጅ ሆይ፡ ማረኝ" አለ!

121 በርግጥ ላይሰማው ይችል ነበር። እንደሚጮኽ ግን ያውቅ ነበር፡ ቆሞም ዞወር አለ። እነሆ አማኙ ነበረ። "እምነትህ ድኖሃል፡" አለው። አሜን።

122 ለዚያችም ደም ይፈስሳት ለነበረችው ሴት፡ እንዲሁ አላት፡ "እምነትሽ።"

123 ምክንያቱም፡ በልቧ፡ "ልብሱን ብቻ ብነካ፡ እድናለሁ" ብላ ነበርና።

"እምነትሽ አድኖሻል።" አያችሁ፡ እርሷ አማኝ ነበረች።

124 ባለፈው ቀን፡ በዚያ ተቀምጦ ለነበረውና፡ ሙሉ በሙሉ የልብ ድካምና የልብ ሕመም ለነበረበት፡ ዕድሜው ዘጠና-አንድ ዓመት ለሆነው፡ ለዊልያም ዳውች መዳን ምክንያት የሆነው፡ ያው ተመሳሳይ ነገር ነው። "እምነትህ ድኖሃል።" ለምን? አማኝ ነዋ።

125 እዚህ ያለው ረቨረንድ ቶም ኪድ፡ አሁን ዕድሜው ወደ... ወደ፡ ዘጠና ዓመታት፡ ገደማ፡ የሆናቸው አረጋዊ፡ ወደዚያ የተጠጋ ነው። ዕድሜው ሰባ-ዘጠኝ ዓመት በነበረ ጊዜም፡ በፕሮስቴት ካንሰር ምክንያት ወደ ሆስፒታል ወሰዱት። ሐኪሙም፡ "ምንም ተስፋ የለውም" አለ።

126 በዚያች በማለዳው በሄድን ጊዜ፡ ያ የእምነት አርበኛ አባት በትከሻው ላይ ኩታ ደርቦ፡ በዚያ ተቀምጦ፡ ትንሿን ምርኩዙን ይዞ እየደበደበ፡ ከራሱ ጋር አልነበረም። በዚያ ተቀምጣ ለነበረችው ለአንዲት አሮጊት፡ ለብዙ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን አባላቱ ከነበሩት አንዷ ስለነበረች፥ ያውቃት ነበር፡ እያቴ ብሎ ጠራት። ከአእምሮው ጋር ስላልነበረ፡ "እንደ በረዶ ነጭ መሰለኝ፡" አላት።

127 ሆኖም፡ የእግዚአብሔር ኃይል ክፍሉን ሞላው፡ እነሆም ዛሬ ምሽት በህይወት አለ። ይህ ከአራት ዓመታት በፊት ነው። ወደ ሰማንያ ዓመት ገደማ የሆነው ሰውዬ፡ ዛሬ ምሽት ከካንሰሩ፡ ሙሉ በሙሉ ድኖና ጤነኛ ሆኖ፡

እዚህ ተቀምጧል። አያችሁ፡ አሰመሣይ-አማኝ ሳይሆን፥ አማኝ! አለቀ፡ እመኑ! እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ ያዘው።

128 ልክ እንደ ዓይነ ሰውር በርጤሜዎስ ነበር። ዕውር ነበር፡ ሆኖም ግን የኢየሱስ ክርስቶስን ትኩረት መሳብ ከቻለ፡ የሚፈልገውን እንደሚያገኝ፡ አውቆ ነበር።

129 ያቺም ሴት ልብሱን መንካት ከቻለች፡ የፈለገችውን እንደምታገኝ፡ ታ—ታውቅ ነበር።

130 ቶም ያውቅ ነበር። እኔ ብጸልይለት፡ የሚፈልገውን እንደሚያገኝ፡ እምነት ነበረው።

131 ማርታ እንዲህ ያለችበት እምነትስ ያው አይደለምን፡ "ጌታ ሆይ፡ አሁንም ቢሆን፡ ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ፡ እግዚአብሔር እንዲያደርግልህ አውቃለሁ፥ ወንድሜ በዚያ አራት ቀን፡ ሙት ሆኖ፡ በመቃብር ውስጥ ተጋድሟል፥ አንተ ግን እግዚአብሔርን ብቻ ለምን፡ እግዚአብሔርም ያደርግልሃል"?

እርሱም፡ "ወንድምሽ ይነሣል" አላት።

132 እርሷም፡ "አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ በትንሣኤ ይነሳል። ጥሩ ልጅ ነበር፡" አለች።

እርሱም፡ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ!"

"አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ እኔም፡ አምናለሁ።"

"የት ነው የቀበራችሁት? " በቃ። አለቀ። አዎን፡ ወዳጄ።

133 የደቡብ ንግሥት በዚያ በማያምኑት ትውልድ መካከል መጣች፡ ያ እውነት ነው፡ በዚያም ቆማ ያየችው ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ አመነች። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "በመጨረሻው ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነስታ፡ ትፈርድበታለች፡ የሰለሞንን ጥበብ ለመሰማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና" ይላል።

134 ሙሴ አማኝ ነበረ። ምንም እንኳ በአእምሮው አስተሳሰብ ቢሞክርም፡ የቻለውን ዘዴ ሁሉ ቢሞክርም፡ ነገር ግን ሊሳካለት አልቻለም። እሰራኤልን ለማውጣት ሞክሮ ነበር፡ ይህንን ለማድረግ እንደተጠራ ያውቅ ነበርና። በሒሳባዊ መንገድ ሞከረ። በወታደራዊ መንገድ ሞከረ። በትምህርታዊ መንገድ ሞከረ። በሁሉም ዓይነት መንገድ ሞከረ፡ ነገር ግን አልሰራም። ከዚያም የእግዚአብሔርን መንገድ ተከተለ።

135 ምን ተፈጠረ? አንድ ቀን፡ በዚያ ቁጥቋጦ ላይ፡ የማይጠፋ እሳት ነበረ። ከዚያም ቃሉ ተናገረው፡ "እኔ ነኝ" አለው። "እኔ የነበርኩ፡" ወይም፡ "እኔ እሆናለሁ፡" አላለውም። "እኔ ነኝ፡" አለው። አሁንም እርሱ "እኔ ነኝ" ነው። እርሱ ቃሉ ነው፡ ዘላለማዊውና፡ የማይለወጠው ቃል።

136 ሙሴ አልተጠራጠረም። አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢቃወሙትም፡ ተፈጥሮ ሁሉ ተቃወመው፡ ነገር ሁሉ ተቃወመው። ዳሩ ግን፡ ጠማማ በትር በእጁ ይዞ፡ ወርዶ መላውን ሕዝብ ተረከበ፡ በዚያ ባለው በሞተው ባሕር ውስጥ አስጠማቸው፡

እስራኤልንም ወደ ተስፋይቱ ምድር መራቸው። ለምን? እግዚአብሔርን አመነ። ልክ ነው። እርሱ...

137 አማኝ ማለት ያ ነው። እዚህ መቆየት እንችል ነበር... አሁን ስለ አማኞች የተናገርኩት ግማሽ-ሰዓት ሞላኝ።

138 ሁለት ተጨማሪ ክፍሎች አሉን። ታዲያ አስፈላጊ ስላልሆኑ፡ እንዲሁ፡ በፍጥነት እናልፋቸዋለን። አይ።

139 ስለዚህም፡ ሁለተኛው ደረጃ፡ የሚመጡት የማያምኑ ናቸው። በመቀጠል ስለማያምኑቱ እንነጋገር። የማያምን ምን ያደርጋል?

140 አማኙ (ምን? ) ቃሉን ሲቀበል አይተነዋል፥ ከኖህ ጀምሮ፡ እስከ ላይኛው ድረስ ያለው፡ እያንዳንዱ ዘር፡ እያንዳንዱ ትውልድ። በዚያው ላይ ብቻ ገጸ ባህሪያቱን እያነሳን፡ ለስድስት ወራት ያህል ሪቫይቫል ልናደርግ እንችል ነበር። እነርሱ ያምናሉ። አማኙ ጥያቄ አይጠይቅም። ምንም ያህል የማይቻል፡ ቢመስልም ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው፡ ስለ እርሱ ምንም ቢናገር አማኙ ያምነዋል።

141 አማኙ፡ ያምናል (ምን? ) ቃሉን። ቃሉን እንጂ፥ የሃይማኖት መግለጫ አይደለም! የሐይማኖት ተቋምን አይደለም፥ ቃሉን ነው! ሌላ ሰው የሚናገረውን አይደለም፥ ቃሉ እንጂ! አሁን፡ አስታውሱ፡ ያ አማኝ ነው። አማኙ ጥያቄ አይጠይቅም። አማኙ፡ "እንዴት ሊሆን ይችላል? አስቀድሞ ቢብራራልኝ ኖሮ" አይልም! ያኛውማ የማያን ነው። ኧ-ህ። አማኝ የሆነውማ፡ ምንም ቢሆን፡ "ቃሉ ከሆነ፡ ቃሉ ነው! ያ እውነት ነው፡" ይላል። አማኝ ማለት ያ ነው።

142 አሁን ደግሞ የማያምኑ። አሁን ምን እንደሚሆን እናያለን... የማያምኑ እንውሰድ። ጀርባቸው መታ መታ ሲደረግና ደቀ መዛሙርት ተብለው እስከተጠሩ ድረስ መልካም የሚያደርጉ እንደሆኑ እናውቃለን። ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ (ለእነርሱ) እስከተጓዘ ድረስ፡ እነርሱ ጥሩ ይሆኑ ነበሩ። ነገር ግን ይህ ነቢይ መሆኑን ባመኑ፡ እና ነቢይ መሆኑን ሲያውቁ፡ የታመሙትን ሊፈውስ እንደሚችል፡ ወዘተ ባወቁ ጊዜ፡ ምን አደረገ? እነርሱ ከሚያምኑት በተቃራኒ፡ ትክክለኛና እውነተኛ ተግሳጽ በመጣ ጊዜ፡ ቃሉን ለመቀበል አልቻሉም።

143 ተአምራቱን ተቀብለዋቸዋል፡ እነርሱም ፈጽመዋቸዋል። ወጥተው አጋንንትን አሰወጥተው፡ ቃሉን ሰበኩ፡ አሁንም የማያምኑ ናቸው። በማቴዎስ 10 ላይ፡ ሰባዎቹን፡ ሁለት በሁለት አድርጎ፡ ላካቸው፡ አጋንንትንም አወጡ፡ በዚያም ኢየሱስ ደስ ብሎት፡ "ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁት፡" አለ። እያችሁ፡ አጋንንትን አሰወጥተዋል፥ ይሁዳም ከእነርሱ ጋር አብሮ ነበረ። የማያምኑትም ይኸው ነው።

144 ኢየሱስ እርሱ እከሌ እንደሆነ መናገር እንደጀመረ ግን፡ ማለትም እርሱ "ትንሣኤ" እንደሆነ፡ "ሕይወት" እንደሆነ መናገር ጀመረ። "የሰው ልጅ ከነበረበት ሰፍራ ወደ ላይ ሲወጣ ብታዩስ ምን ትላላችሁ" አላቸው?

145 "አሁን፡ ይህ ሰው ከሰማይ እንደመጣ ለመናገር እየሞከረ ነው፡ ይህ ለእኛ በጣም ከባድ ነው። ልናምነው አንችልም።"

146 እርሱም፡ "ምንድነው? እናንተ የምትናገሩበት ሥጋ፡ ምንም አይጠቅምም። ሕያው የሚያደርግ መንፈስ ነው" አለ።

147 ይኸው ነው፡፡ መንፈስ ቃሉን ሕያው ያደርገዋል። መንፈሱ ነው እንጂ፡ የሃይማኖት መግለጫው አይደለም፡፡ የቅዱስ መንፈስ የሆነው፡ ያ መንፈስ፡ ቃሉን ለእናንተ ሕያው ያደርገዋል፡ እርሱም ሕያው ይሆናል፡ እነሆም፡ ታዩታላችሁ። በእምነት ታዩታላችሁ። ይህ እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ምክንያቱ ቃሉ ስለተናገረ መንፈስ ቃሉን ለእናንተ ሕያው ያደርጋል። ይኸው ነው፡፡

148 አሁንም እሱም አለ፡ "ምን ሊ... " ይህንም ባደረግን ጊዜ፡ ደርሰንበታል፡ የማያምኑት፡ ከማይስማሙበት ነገር አንድ ነገር ሰትናገሩ፡ ጥለዋችሁ ይወጣሉ። "አልስማማም!" ኦህ፡ ዛሬ በዓለም ላይ፡ ይህ በጣም እየጠነከረ መጥቷል። ጀምራችሁ አንድ ነገር ብቻ ስትናገሩ...

149 ይሰበሰባሉ። በሰብሰባዎች ላይ፡ ትላልቅ ህዝብ እንደሚሰበሰቡ አስተውያለሁ፡ እናንተም ትቆማላችሁ፡ መናገርም ትጀምራላችሁ። አሁንም፡ እስከ... ብቻ እዚያ ይቀመጣሉ፡ ይመለከታሉ፡ ይጠብቃሉ። በዚያን ጊዜም እንዲህ ሰትሉ፡ "አሁን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ ስለነበረ፡ ራሱን እንደ መሲሕ ቆጠረ፡" ማሰሮው ይሞላባቸዋል፡ ይሄዳሉም። አንዱ... መንገዱንም ይይዛሉ። ምንድን ነው? የማያምኑ!

150 "ይህን በራስህ የፈጠርከው ነው፡" ትላላችሁ። አይደለሁም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን በትክክል እናገራለሁ።

151 የማያምኑ ነበሩ፡ ጥለውም ወጡ። ደቀ መዛሙርት ቢሆኑም፡ ነገሩ ጋር ግን የ—የሚቃረን ነበር... እንዲህም አሉ፡ "ይህን፡ እንደዚህ ያለውን ነገር ማን ሊያምን ይችላል? " አያችሁ? ከእሱ ጋር ወጥተው፡ ተባብረው አብረውት ይሄዱ የነበሩ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ነበሩ።

152 ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ መለኮታዊ የሆነ ነገር—በሚገለጥበት ጊዜ፡ ሦስት የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን ያወጣል። በግብፅም እንዲሁ አድርጓል። የማያምነውን፡ አማኙን፡ አስመሳይ-አማኙንም አምጥቷል። ሦስቱን ወገኖች አመጣ። እዚህም ተጽፏል፡ ነገሩ እንዴት እንደሆነ እያብራራን፡ ሌሊቱን ሙሉ፡ ብንቀጥል እንኳ አያልቅም። በየትኛውም ሰፍራ፡ ብትፈትሹ፡ ሦስቱንም ታዩአቸዋላችሁ። ሁልጊዜም እንዲሁ ነው፡ አያችሁ፡ ታገኟቸዋላችሁ።

153 አሁንም ተመልከቱ፡ እነዚህ ሰባዎች፡ ትክክል ነው ብለው ከሚያምኑት ጋር ስላልተስማማላቸው ጥለው ወጡ።

154 ልናመጣው የሚገባን የራሳችን አሳብ የለንም። እሱ የተናገረው ነው! የራሳችሁን አሳብ ትክዳላችሁ። እሱ የሚለውን ብቻ ትናገራላችሁ። እውነተኛ ኑዛዜ ማለት ይህ ነው። **ኑዛዜ** ማለት "የሆነውን ነገር መናገር" ማለት ነው። አንድ የተወሰነ ነገር እንደተከሰተ ብናዘዝ፡ የተከሰተውን ያንኑ ነገር እናገራለሁ። እውነተኛ ኑዛዜ ማለት ያ ነው። "እሱም የኑዛዜያችን ሊቀ ካህናት ነው።" አያችሁ? እግዚአብሔር የተናገረውን ያንኑ ነገር መናገር፡ አያችሁ፡ ይህም ትክክል ያደርገዋል፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቃል እየደገማችሁ ነውና።

155 አሁን ልብ በሉ፡ ሰባዎቹ ጥለው ወጡ። ምን አደረጉ? እነሱም በ—በመካከላቸው ባ—ባለመስማማታቸው ብቻ ወጡ። የእነሱ—የእነሱ—የእነሱ ጥበብ፡ የእነሱ—የእነሱ የቤተክርስቲያን ግንኙነት፡ በጣም—በጣም በዛባቸው። ይህን ለማሰብ ለእነሱ ከአቅማቸው በላይ ነበር፡ ይህ እዚህ የቆመው ሰው፡ ያ... ሌሎች ሰዎች ሁሉ ይህ ከጋብቻ ውጪ የተወለደ እንደሆነ

ያምናሉ። “ራሱን አምላክ ብሎ ለመጥራት ምንም መብት የለውም። ሰው ብቻ ነበረ።” እንዲህም አሉ፡ “በመልካም ሥራህ አንወግርህም፡ ነገር ግን አንተ፡ ሰው ስትሆን፡ ራስህን አምላክ ስላደረግህ እ—እንወግርሃለን።”

156 ቃሉም እሱ አምላክ እንደሆነ ተናግሯል። “ስሙም ‘መካር፡’ ‘የሰላም አለቃ፡’ ‘ኃያል አምላክ፡’ ‘የዘላለም አባት’ ተብሎ ይጠራል።” እነሱ ራሳቸው የሚያነቡት መጽሐፍ ቅዱስ!

157 መዝሙርን በዘመሩበት ቀን፡ መዝሙር 22ኛው ምዕራፍ፡ “አምላኬ፡ አምላኬ፡ ስለምን ተውኸኝ? አጥንቶቼ ሁሉ አፈጠጡ።” “ከአጥንቶቹ አንድም አይሰበርም።” በመቅደሱ ውስጥ እየደጋገሙት የነበረው ያንኑ መዝሙር፡ በዚያ በመስዋዕቱ ተሰቅሎ ዳዊት ከስምንት መቶ ዓመታት በፊት የተናገረውን ያንኑ ቃል እየጮኸ ነበር፡ ያንን ለማየትም እጅግ ታውረው ነበር።

158 ዛሬም፡ ስለዚህ ዘመን የተናገረው ያው አምላክ፡ በሰፍራው ሆኖ የተናገረውን በትክክል እያደረገ ነው፡ እነሱም ያንን ለማየት እጅግ ታውረዋል። የማያምኑት እንዲህ ናቸው። ወጥተው እንዲህ ይላሉ፡ “ኦህ፡ እንደዚህ ያለ ነገር ማመን አልችልም። በሕይወቴ እንዲህ ያለ ነገር ሰምቼ አላውቅም!” የሰማችሁት ነገር ምንም ለውጥ አያመጣም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚሆን ተናግሯልና፡ ቃሉም እሱ ነው።

159 እነሱም ቢሆኑ፡ እንዲህ ያለ ነገር ሰምተው አያውቁም ነበር፡ ነገር ግን እዚያው በተመሳሳይ ሁኔታ ነበረ። አያችሁ? ልክ ነው። የማያምኑ ነበሩ።

160 ልክ እንደ ሔዋን፡ እሷም፡ በእርግጥ፡ እጅግ ሃይማኖተኛ ነበረች፡ እውነተኛውን ቃል ግን አ—አላመነችም ነበር። ለራሷም የገዛ ሃይማኖቷ ማድረግ ፈለገች፡ ስለዚህ የበለስ ቅጠሎችን አዘጋጀች፡ አያችሁ፡ ነገር ግን አልሰራም። **ሃይማኖት** ማለት “መሸፈኛ” ማለት ነው።

161 ቃየንም እንዲሁ አደረገ። ቃየን ይህ ትክክል እንደነበረ ማመን አልቻለም። እንዲህም አለ፡ “እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡ እግዚአብሔር ንጹሕ ነው፡ እግዚአብሔር ውብ ነው። ስለዚህ አንዳንድ አበቦችን ላምጣና፡ ከአበቦቹም—ከአበቦቹም ወሰጄ፡ መልካምና ታላቅ መሠዊያም እሠራለሁ፡ ለእሱም ያለኝን አ—አክብሮት አሳያለሁ። በፊቱም እቆማለሁ በፊቱም እሰግዳለሁ፡ ያንንም አምላክ እመልካለሁ። በመሠዊያውም ላይ አበቦችን እኖራለሁ፡ ምክንያቱም፡ ታውቃላችሁ፡ እናቴ እና አባቴ በኤደን ገነት ውስጥ፡ አንዳንድ አፕሎችን፡ አንዳንድ ፍራፍሬዎችን በልተዋል፡ እኔንም ከዚያ ያሰወጣኝ ነገር ይህ ነው። ስለዚህም፡ ያ ነው፡ ተመልሼ እንድገባ፡ ውብ አደርገዋለሁ። እግዚአብሔር ታላቁን ካቴድራሌን እንዲሁ አይንቀውም። ለምን፡ የካቴድራሉ ታላቅ እሆናለሁና! የእግዚአብሔርን ትኩረት እስኪስብ ድረስ እጅግ ውብ አደርገዋለሁ።” በውበት ውስጥ የሚኖረው ሰይጣን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው ይህንን ነው።

162 አንዳንድ ጊዜ፡ አንዲት ውብ ሴት ለሰይጣን ማጥመጃ የምትሆነው፡ በዚህ ምክንያት ነው። እሷን በእጁ ማስገባት ከቻለ፡ በአገሪቱ ውስጥ ካሉት መጠጥ ቤቶች ሁሉ ይልቅ ብዙ ሰዎችን ወደ ገሃነም ሊያዞር ይችላል። ልክ ነው። አያችሁ? ወይም፡ መልከ መልካም የሆነ፡ በወንድነቱ ታማኝነት የማይጸና—የማይጸና ታላቅ መልከ መልካም ሰው፡ አያችሁ፡ እሱም እንደገና፡ እነዚያን

ሴቶች ወደ ሰይጣንነት ሊቀይራቸው፡ ወደ ገሃነምም ሊልካቸው ይችላል። አዎን፡ ጌታዬ።

163 አስተውሉ፡ ሰይጣን በውበት ያድራል። በመጀመሪያ ምን ለማድረግ ሞከረ? ከሚካኤል መንግሥት ይልቅ ይበልጥ ውብ የሆነ መንግሥት ለመሥራት ሞከረ፥ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ተንቀሳቀሰ፡ ሁለት-ሦስተኛ የሚሆኑትንም መላእክት ከእሱ ጋር ወሰደ።

164 ያን ጊዜ ያ የሰይጣን ባሕርይ በውስጡ የነበረው፡ የማን—የማን ልጅ እንደነበረ አያችሁ? የሰይጣን ልጅ። በእርግጥም፡ ነበር። ስለዚህ መሰውያውንም ሠራ፡ ተንበርክኮ ሰገደ። አቤል ባደረገው ነገር ሁሉ (ቃየን) ሁሉ አለፈ።

165 አቤል ግን ነገሩ እንደዚያ እንዳልሆነ ያውቅ ነበር። እሱ... ያሰባረራቸው ነገር ደም እንደነበረ ያውቃል። ያ እንደሆነ ያውቅ ነበር። የሩካቤ ደም፡ ነበር። ስለዚህ ትንሽ እንሰሳ ወሰዶ፡ በዓለት ላይ አቀረበውና፡ አንገቱን ይቆርጣል።

166 ቃየንን ልብ በሉ፡ እሱ... እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡ እንዲህም አለ፡ “ለምን እንደ ወንድምህ አታመልክም፡ ያን ጊዜም መልካም ይሆንልሃል። ይህን ብታደርግ መልካም ይሆንልሃል።” ነገር ግን፡ እሱ ስለ ነገሩ በጣም ብዙ ያውቅ ነበርና፡ እምቢ አለ። አያችሁ፡ እውነተኛውን፡ የጸናውን ቃል እምቢ አለ። ዛሬስ ያሉት ልጆቹ ያው አይደሉምን! አያችሁ?

167 አሁንም ተመልከቱ፡ “እግዚአብሔር መሰክሯል፡” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ወደ ዕብራውያን ምዕራፍ 4፡ ወይም ምዕራፍ 11፡ “እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር፡ ጻድቅ እንደነበረ።” እግዚአብሔር መሥዋዕቱን አጸናለት። እግዚአብሔር የተቀበለው፥ ያ የእሱ ቃል፡ የእሱ ዕቅድ እንደነበረ ማረጋገጫ አደረገለት።

168 ቃየንንም፡ “አንተም ያንኑ አድርግና፡ በሕይወት ኑር፡” አለው። ነገር ግን እሱ፡ አሳቡን የሚተው ይመስላችኋል? አይተውም፡ ጌታዬ። እሱ የማያምን ነበረ፡ ጥሎም ወጣ። በትክክል። ቃየን ተመሳሳይ ነገር አደረገ። ናምሩድ ተመሳሳይ ነገር አደረገ። እምነት አልባ! አላመነም።

ብልጣሶርም፡ ቢሆን፡ እንዲሁ አደረገ፡ ወይም...

169 ናቡከደነጾር፡ ዳንኤልን እንደ አምላኩ አድርጎ ቢይዘውም፡ በአምላኩ ስም፡ ብልጣሶር ብሎ ቢጠራውም፡ ዳንኤል ታላቁን የእግዚአብሔርን ሥራ ሲሠራ አይቷልና። ያን ጊዜም ብልጣሶር እ—እንዳመነ፡ ወይም ዳንኤል አምላክ እንደነበረ አወቀ፡ ስለዚህ ለእሱ ምስል አደረገለት፡ በዚያም አቆመው ሁሉም እንዲሰግድለት አደረገ፡ ወዘተ። አያችሁ፡ የአሕዛብ መንግሥት የቅዱስ ሰውን ምስል በግድ እንዲያመልኩ በማድረግ ገባ፡ የአሕዛብም መንግሥት የቅዱስ ሰውን ምስል በግድ እንዲያመልኩ በማድረግ ይወገዳል፡ አያችሁ፡ በተመሳሳይ ሁኔታ።

170 በአሕዛብ መንግሥት መጀመሪያ ላይም፡ በግድግዳው ላይ፡ በማይታወቅ ቋንቋ የተጻፈ ጽሕፈት ነበረ፡ ከዚያ ነቢይ በቀር ማንም ሊያነበው የማይችለው ነበር። ዛሬም በግድግዳው ላይ የእጅ ጽሕፈት አለ፡ በትክክል፡ “ኢካቦድ” የሚል፡ የእግዚአብሔር ክብር ከእነዚያ ነገሮች እንደራቀ የሚያሳይ። ጽሕፈቱም

በግድግዳው ላይ አለ ይህም በመንፈሳዊ ነገሮች በሚያምን ከእግዚአብሔር መንፈስ በተወለደ፡ መንፈሳዊ አእምሮም ባለው ሊነበብ ይችላል።

171 የቀድሞው ብልጣሶር ወጥቶ ወይን ጠጅ ሊጠጣባቸው፡ እነዚህን የጌታን ዕቃዎች ይወስዳል። ለምን? እሱ የማያምን ነበረ። እሱ አማኝ ነኝ ብሎ አስቦ ነበር፡ ነገር ግን የማያምን ነበረ። አያችሁ፡ ነገሩ ያ ነው፡ ቃሉን አላመነም ነበር።

172 አክዓብ፡ ምንም እንኳን እሱ—እንዳልሆነ አድርጎ ቢንቀሳቀስም፡ የማያምን ነበረ። በጭራሽ፡ አይደለም፡ እሱ ከአማኞች መካከል ነበረ፡ ነገር ግን እሱ የማያምን ነበረ። ምን አደረገ? ጣዖት አምላኪዋን አገባ፡ ጣዖት አምልኮንም፡ በቀጥታ፡ ወደ እስራኤል አመጣ። እሱ የማያምን ነበረ። ይህንን እናውቃለን።

173 የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እውነት መሆኑን ይክዳሉ። የማያምነው ሰው፡ አያችሁ፡ አሁንም አስታውሱ፡ እሱ ግብዝ ነው። እ—እሱም እንዲሁ ያደርጋል፡ ማመኑን ይናገራል፡ ነገር ግን ይክደዋል። እንዲህም ይላል፡ “እንግዲህ፡ ይህ በአብዛኛው መልካም ነው።” ነገር ግን ሁሉም ትክክል ካላሟላ፡ ያ እሱን የማያምን ያደርገዋል። በዚያ የተነገረውን እያንዳንዱን ነጥብ፡ እያንዳንዱን ጭረትና እያንዳንዱን ነገር ማመን አለባችሁ። እውነት መሆን አለበት። እውነት ካልሆነ፡ አሁንም፡ “ያንን አላምንም” ካላችሁ፡ እንግዲህ፡ ያኔ የማያምኑ ናችሁ።

174 አንድ ጊዜ፡ አንድ ሰው፡ አንድ—አገልጋይ እንዲህ አለኝ፡ “አቶ ብራንሀም፡ የተፈወሱ የተባሉትን ሰዎች—ምንም ያህል ብታሳየኝም፡ ምንም ግድ የለኝም፡ አላምንም።”

175 እንዲህም አልኩት፡ “በእርግጥም፡ ልታምን አትችልም። አንተ የማያምን ነህ። ይህ ለአንተ አልነበረም። ይህ ለአማኞች ብቻ ነው።”

176 ማመን አለባችሁ። አያችሁ? እነሱ ግን አያምኑበትም። ስለዚህ እንዲህ ያለውን ሰው ሲታዩ፡ ጳውሎስ (ነቢዩ) መልካም ተናገረ፡ እንዲህ ይላል “ችኩሎች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፥ የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል፡ የቃሉን ኃይል ግን ክደዋል፥ ከእንዲህ ዓይነቱ ራቅ።” ልብ በሉ፡ የቃሉን ሙሉ እውነት ይክዳሉ፡ ነገር ግን በሁሉም መልክ ሃይማኖተኞች ናቸው። ቃሉ የጸና ቢሆንም እንኳ፡ በእውነተኛው ቃል ላይ የማያምኑ ናቸው።

177 በእያንዳንዱ ዘመን ሁሉ፡ እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ስለተናገርኳቸው ሰዎች ቃሉን አጽንቷል፡ ስለ ኖኅ፡ እንዲሁም፡ እስከ ሙሴና፡ እስከ ነቢያት ሁሉ ድረስ። እግዚአብሔር ከተፈጥሮ በላይ በሆነው ነገር ተናግሮ ቃሉን አጽንቷል፡ እነዚያ ሰዎች ግን ጥለውት ወጡ።

178 እነዚህም ሰባዎቹ፡ ደቀ መዛሙርት በዚያ ቆመው ነበር፡ ኢየሱስ ያደረገውን ነገር ሲያደርግ ያዩ ነበር፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያውቁ ነበር፡ እሱም ይህ ሊፈጸም የሚገባው ዘመን እንደነበረ ይነግራቸው ነበር። ያን ጊዜም እንዲህ ሲል አንድ ነገር ተናገረ፡ “የሰው ልጅ! ማን ትሉታላችሁ?” ስለ እንጀራው መቆረስና፡ ስለመሳሰሉት ነገሮች ሊነግራቸው በጀመረበት ጊዜ፡ ስለ ታላላቅ፡ ስለ መንፈሳዊ ነገር እየነገራቸው ቀጠለ።

እነርሱም እንዲህ አሉ፡ “ኡህ፡ ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው!”

179 እሱም አለ፡ “እንግዲህ፡ የሰው ልጅ ከዚህ ቀደም ወደነበረበት፡ ወደ ሰማይ ሲወጣ ብታዩ ምን ትላላችሁ?” እንዲህም አለ፡ “ሥጋ ነውን፡ ወይስ፡ ሕያው የሚያደርግ መንፈስ ነው?” አያችሁ?

180 ያን ጊዜም ፈቀቅ አሉ፡ እንዲህም አሉ፡ “ኡህ፡ ያንን፡ አይሆንም፡ ያንን ማመን አልችልም።” አያችሁ? ቃሉን ትተው፡ ጥለው ወጡ። የሚሆነውን ለማየት እንኳ አይቆዩም። ያ ነው በቃ—የማያምን ሰው ይህ ነው።

181 እነሱ፡ ያኔ ምን አደረጉ? እንግዲህ እንደተረዳነውም፡ እነዚህ ሰዎች፡ እነዚህ አማኞች፡ እንዲሁ በሃይማኖት መልክ ያሉ፡ አማኝ-ተብዬዎች፡ ከሚያምኑት ነገር ጋር ስለሚቃረንባቸው ብቻ የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛነት ለማየት ተሰኗቸዋል። አያችሁ?

182 ስለ ምታምኑት ነገርምን ያህል ታማኝ እንደሆናችሁ፡ ምን ያህል ሃይማኖተኛ እንደሆናችሁ፡ ምንም ልዩነት አያመጣም፡ ወይም፡ ይህ ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። ቅንነትም፡ ቢሆንም፡ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እጅግ ቅኖች የሆኑ ሰዎች አይቻለሁ! አረማውያን ልጆቻቸውን ሲያቃጥሉ፡ ለአዞ ሲመግቡ፡ እናቶችም ከሕፃናቶቻቸው ጋር ሲያደርጉት አይቻለሁ። ይህ አንድ ክርስቲያን ከሚያደርገው በላይ ነው። አያችሁ? በቅንነት ያምናሉ፡ በቅንነት፡ ነገር ግን በቅንነት የሳቱ ናቸው።

183 ሰዎች፡ “እንግዲህ፡ ይህች ቤተክርስቲያን ጸንታለች” ይላሉ! ይህ፡ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ከሆነ፡ እስከነቅንነታችሁ ስታችኋል። “እንግዲህ፡ አሁን ተመልከቱ፡ በእንደዚህ ያለ ነገር አላምንም!” መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡ እንዲሁ እንደሆነ፡ ተናግሯል! አያችሁ? “**ይህን** ማድረግ አለብን ብዬ አላምንም።” ማድረግ የሌብንም ብላችሁ የምታሰቡት ነገር ምንም ግድ የለኝም። መደረግ አለበት ብሎ እግዚአብሔር ተናግሯል።

184 “እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል።” ምን ያህል ርቀት ነው? “ወደ ዓለም ሁሉ።” ለማን? “ለፍጥረት ሁሉ።” አያችሁ፡ እንዲሁ ይሆናል! አሁንም፡ እንዲሁ ይሆናል፡ ሊሆንም ነው!

185 አሁንም እያጣጣምነው ያለው ይህ የዘመኑ መልእክት፡ የእግዚአብሔር ህልውና፡ የኋለኛው ዘመን፡ ብርሃን የሚበራበት የምሽቱ ጊዜ፡ የተከፈቱትም ነገሮች፡ የጸናውና እውነት መሆኑ የተረጋገጠው ቃል፥ ትንቢት የተነገረለትም፡ የሚፈጸመው፡ በሳይንሳዊና በሁሉም ነገር የተረጋገጠው፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ እስከ ለዘላለምም ያው፡” መሆኑን አረጋግጧል። ሰውም፡ ይህንን ጥሎ ቢወጣ፡ እ—እሱ የማያምን ነው። ከተሰፋ ውጭ ሆኗል። በሰይጣን ኃይል ደንዝዟል፡ ስለዚህ ለእሱ ምንም ተሰፋ የለውም። ከተሰፋዎች ውጭ ሆኗል።

186 ስለዚህ ያ ምንድን ነው? አማኙ፥ እንግዲህ ይህ የማያምን ነው፥ ሦስተኛው ክፍል፡ አሁን የምንናገርለት፡ አስመሳይ-አማኝ ነው። አንዱ ይህ ነው፡ አስመሳይ-አማኝ! እንግዲህ፡ አስታውሱ፡ በዚያ ሦስቱም ቆመው ነበር። አሁን፡ ልክ እንደ አባታቸው፡ እንደ ይሁዳ እንደሚያደርጉ፡ አሁንም ደርሰንበታል።

ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት፡ አማኞች ነበሩ።

ሰባዎቹ ደግሞ፡ የማያምኑ ነበሩ።

187 ይሁዳም፡ አብሮ ቀጠለ፡ እሱ አስመሳይ-አማኝ ነበረ። እነዚህ ምን ያደርጋሉ? እነዚህ ዓይነት ሰዎች በውስጡ አንዳንድ ስህተቶችን እስኪያገኙ ድረስ፡ አብረው ይቆያሉ። እንዴት እንደተደረገ ለማየት፡ ተንኮል መሆኑን ለማየት፡ አያችሁ፡ ሁልጊዜም ቀዳዳ ይፈልጋሉ። አሳልፈው ለመስጠት ይጠባበቃሉ። ይህንንም ይፈልጋሉ።

188 የማያምነው ሰው ግን፡ ፈጽሞ አልቆየም። አውግዞ፡ ጥሎ ወጣ።

189 አማኙ፡ ምንም ቢፈጠር፡ በምንም መንገድ፡ ያምናል፡ ምክንያቱም ቃሉ ነው።

እንግዲህ ሦስቱ መደቦች እነዚህ ናቸው።

190 እምነት አልባው ሰው፡ አልወደድኩትም ባለው፡ በመጀመሪያው በተነገረው ነገር ላይ ጥሎ ይወጣል። ወንድሜ ሆይ፡ እሱ የማያምን ነው። ወዲያውኑ ማንነቱን ያሳያል። ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡ “እነሱ በመጀመሪያ፡ ከእኛ ወገን ስላልነበሩ፡ ከመካከላችን ወጡ። ከእኛ ጋር ጀምረው ነበር።” “ኦህ፡ በመልካም ትሮጡ ነበር፥ ማን ዓዚም አደረገባችሁ?” አያችሁ? “እነሱ ከእኛ ወገን ስላልነበሩ፡ ወጡ።” ቃሉ በትክክል ሲንቀሳቀስ ባዩ ጊዜ ወጡ፡ ለምን ቢሉ፡ ሊሠሩበት የሚችሉትን አንዳንድ ተንኮል ማግኘት ፈለጉ። አያችሁ?

191 እውነተኛዎቹ አማኞች ግን ምንም ጥያቄ አይጠይቁም። በቃሉ ውስጥ ተጽፏል፡ ያምኑታል፡ እናም ዝም ብለው ይቀጥላሉ። በቃ። ሁልጊዜም ቢሆን፡ ተጽፏል። ካልተጻፈ ግን፡ ለምን፡ ምንም ቢፈጠር፡ ከእሱ ይርቃሉ። መጻፍ አለበት። አያችሁ? የተጻፈውንም ቃል ያያሉ ያምኑበትማል። እግዚአብሔርም በቃሉ ውስጥ ሲንቀሳቀስ ያያሉ፡ ሰዓቱን፡ መልእክቱን፡ ጊዜውንም ያያሉ፡ ከእሱም ጋር ይራመዳሉ።

192 ዛሬ ጠዋት እንደተናገርኩት፡ ያለፈው ጲላጦስ በጭንቀት በተሞላ ሕሊና፡ ራሱን ለማንጻት እየሞከረ፡ በሌሊት ወለሉ ላይ፡ ተመላልሶ ሊሆን ይችላል። እሱም፡ እንዴታ፡ በሌሊት ጠርቶ እንዲህ ሊል እንደሚችል ምንም ጥርጥር፡ እንዲህ በማለት፡ “ሌሊቱን በሙሉ፡ እጄን ታጥቤ—ታጥቤ—ታ—ታጥቤያለሁ፡ አሁንም ግን ሊገባኝ አልቻለም። አያችሁ፡ ንጹሕ አይደሉም። እሱን ለመገናኘት መቼም መሄድ አልችልም፥ በእጄ ላይ ደም አለበት።” ኦህ፡ ማይ! አያችሁ፡ በጭራሽ በዚያ መንገድ ጥፋተኛ አትሁኑ። አያችሁ?

193 በእጃችሁ ላይ ነው። ከዚያ ለማምለጥ አንድ መንገድ ብቻ አለ፥ ይህም፡ መቀበል ነው፡ ልክ ነው፡ የእሱ አካል መሆን። የፈሰሰውም ለዚህ ነው።

194 አሁን፡ አስመሳይ-አማኝ የሆነው አካል በተቻለው መጠን ቀናተኛ መስሎ ይቆያል፡ በልቡ ውስጥ ግን ምን—ምን እንደሆነ፡ እንዴት እንደምታደርጉት፡ ለማወቅ ይጥራል። ኦህ፡ አገሪቱ በእንደዚህ ዓይነት ግብዞች፡ ተሞልታ የለም ወይ! አዎን። ይህ ይሁዳ ነው። በትክክል። ይከተላል፡ የቡድኑም አካል ይሆናል፥ እሱ ገንዘብ ያዥ ነበረ፡ አያችሁ። እሱም በዚያ ቆሞ፡ ሁልጊዜም እጁን ለገንዘብ ይዘረጋል። በዚህ ማወቅ ትችላላችሁ፡ አንደኛው ነገር፡ እሱ ሁልጊዜም ገንዘብ ለማግኘት ይጥራል፡ እጁንም ለዚህ ይዘረጋል። እሱም አስመሳይ-አማኝ ነው። እንደ አማኝ ይንቀሳቀሳል፡ ነገር ግን በልቡ ውስጥ...

195 እሱ ኢየሱስን አታልሎ እንዳልሆነ፡ ታስታውሳላችሁ። ሰባዎቹ ከሄዱ በኋላ፡ አማኞቹም አቋማቸውን በያዙ ጊዜ፥ እርሱ ወደ አማኞቹ ዞር ብሎ፡ እንዲህ

ብሏቸው ነበርና፡ “በእናንተ ውስጥ አሁንም የቀረ ነገር አለ፡” ምክንያቱም እንዲህ ብሏል፡ “እሥራ ሁለት መርጫለሁ፡ ከእናንተም አንዱ ሰይጣን ነው።” ኢየሱስ ከመጀመሪያው፡ ያውቅ ነበር፡ ምክንያቱም እሱ ቃል ነበረ። የልብንም ምስጢር ያውቅ ነበር።

196 ይህ ምን ያህል ከባድ ነበረ! ለአፍታ ቆም በሉ። በጥልቀት፡ አብዝታችሁ፡ በቀጥታ አሰላስሉት! ምን ያህል ከባድ ነገር ነበር ይሆን፡ በዚያ ሲመላለስ፡ ይሄኛው አንዱ “ወንድም፡” ብሎ ሲጠራው፡ እሱም እሱን ሊያሰናክለውና በሠላሳ ብር ሊሸጠው የሚሞክር፡ አታላይ እንደነበረ ሁልጊዜም ያውቅ ነበር። እንደ ወዳጁ በጉያው አቅፎ፡ አብሮት ሲሄድ ምን ያህል ከባድ ነበረ። እሱም ቢሆን “ጓደኛዬ” ብሎታል፡ ይሁዳንም ጓደኛው ብሎ ጠርቶታል፡ “ይህን ሁሉ ጊዜ፡ ከእናንተ ጋር አልነበርኩምን? ” በልቡ እያወቀ፡ መናገር ግን አልቻለም። ከመጀመሪያው፡ አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደነበረ፡ ያውቅ ነበር።

197 ያ አስመሣይ-አማኝ ዝም ብሎ ይጠባበቅ ነበር። እንዲህ እያለም፡ ይዘምራል፡ “ኦህ፡ **ይህን** አምናለሁ፡ **ይህን**ንም አምናለሁ፡ **ይህን**ንም አምናለሁ። ነገር ግን፡ ኦህ፡ ታውቃላችሁ፡ አንድ ሰው **እንዲህ-እና-እንዲህ** ያለ ጊዜ ነው ሲል ሰምቻለሁ።” ኦህ፡ አያችሁ፡ በጆሮዎቻቸው ብቻ ረዘም ያሉ ናቸው።

198 እውነተኛ አማኝ ከቃሉ በቀር ምንም አይሰማም። ይኸው ነው። እሱ ቃሉን ይጠብቃል። ምንም ቀዳዳ አይፈልግም። ምንም ተንኮል አይፈልግም። እግዚአብሔርን ያምናል፡ ያበቃል፡ ጉዞውን ይቀጥላል። አያችሁ? አማኙ ያ ነው።

199 የማያምነው ሰው በአንድ ደቂቃ ውስጥ ይሞላል፡ ከመልእክቱም አሥር ደቂቃ እንኳ ሊሰማ አይችልም። መነሳትና መውጣት ይፈልጋል። ይህ ከእሱ የሕይማኖት መግለጫ ጋር የሚቃረን ነው፡ ከእሱም ጋር ምንም ግንኙነት አይኖረውም፡ ስለዚህ ይወጣል።

200 ስለዚህ፡ አስመሣይ-አማኝ፡ ያ ይሁዳ፡ አብሮ ይንጠለጠላል። አያችሁ፡ አታላዩ ያ ነው። እንዲህ ያለውን ቃል መናገር ካለብኝ፡ እሱ—እሱ ብልጣብልጥ ነው። ይሁዳ፡ አብሮ ይንጠላጠላል። አንዳንድ ጊዜ፡ እነዚህ አስመሣይ-አማኞች በሰዎች ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሚሆኑበት፡ ይህ ጊዜ ነው። አዎን፡ እነዚህ አስመሣይ-አማኞች ናቸው፡ አያችሁ። አንዳንዶቹ ኃያላን ሰዎች ናቸው፡ የተማሩ፡ የዶክትሬት ዲግሪ፡ ከፍተኛ ተከፋዮች፡ ወዘተረፈ። አንዳንዶቹም ልክ እንደ ሰይጣን ልጆች የሆኑ ታላላቅ፡ ብልሆች፡ ሰዎች ናቸው።

201 ሰይጣን እንዴት በቀጥታ ወደዚያ መጥቶ በዚያ ቃል ሁሉ ላይ እንደተሰማማ ተመልከቱ፥ እሷን ለማታለል፡ አሳልፎ ለመስጠት ኃይሉን ማሳየት የሚችልበትን፡ ያንን በሔዋን ውስጥ ያለውን ደካማ ጎን ለማግኘት ዝም ብሎ ይጠባበቃል። ያ—ያ ሰይጣን ነበረ። በዚያ ዘመንም፡ ሰይጣን፡ በይሁዳ መልክ በዚያ ነበረ። ያ በመጀመሪያው ዘመን ሰይጣን ያ ነበረ። እሱ ምን ነበረ? አንዲት ትንሽ ነገር እስኪያገኝ ድረስ ብቻ በቃሉ ላይ ይሰማማ ነበር፥ ድካም የሚያገኝበትን ስፍራ ለማግኘት እየጣረ ነው።

202 ይሁዳም አሁንም በትክክል የሚያገኘው ይህንን ነው። በቀጥታ ወደ ስብሰባው ይመጣል፡ ዙርያውንም ይቃኛል “ኦህ፡ ይኸው! በቃ!” የሚልበትን፡

ያቺን ትንሽ ሰፍራ እስኪያገኝ ድረስ ዙሪያውን ይመለከታል። አያችሁ? “ኦህ፡ የሚደረገው በዚህ መንገድ ነው!” አያችሁ? ልክ እንደዚሁ ነው።

203 በዚያች ሌሊት ያ ሰው ወደ መድረኩ ሲወጣ በዚያ የነበራችሁት ብዙዎቻችሁ ታስታውሳላችሁ። እሱም የጸሎት ካርዶቹን በመጠቀም አእምሮን የማንበብ ድርጊት እንደሆነ ይመስለው ነበር፡ በቃ ደርሼበታለሁ ይል ነበር። ወንድሜ ሆይ፡ እሱ—እሱ እንደደረሰበት እርግጠኛ ነበረ። እናም መጣ። እሱም በዚህ—በ—በወንጌሉ፡ በሙሉ ወንጌል በማያምን፡ የሐይማኖት ተቋም ውስጥ ነበረ። ወደ መድረኩም ወጣ። ደክሞኝ ነበር። ሊወስዱኝም በዝግጅት ላይ ነበሩ።

204 ይህም በዊንዘር፡ ኦንታሪዮ ነበረ። በዚያም፡ ከዩናይትድ ስቴትስ—ከሰሜን አሜሪካ፡ በቀጥታ ማዶ፡ ከዴትሮይት ማዶ፡ በዊንዘር በታላቁ አዳራሽ ውስጥ መጣ።

205 ይህም ሰው ግራጫ ልብስ ለብሶ፡ ቀይ ክራቫት አስሮ፡ ብልህ-የሚመስልና፡ እጅግ ንቁ ሰው ሆኖ መጣ። ወደ መድረኩም መጣ። እኔም… ወደ ላይ ወጣ። እንዲህም አልኩት፡ “እንግዲህ፡ እጅህን ብቻ ስጠኝ።” አልኩት፡ “ደክሞኛል፥ ብዙ ራእዮችን አይቻለሁ። እጅህን ብቻ ስጠኝ።” እናም—እንግዲህ እኔ ሰውየውን ምንም ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። እሱም እጁን በእጄ ላይ አኖረ። እኔም፡ “ጌታዬ፡ አንተ ምንም ችግር የለብህም። ሂድ እለፍ” አልኩት።

እሱም አለ፡ “ኦህ፡ እኔ፡ አለብኝ።”

206 “እሺ፡ እዚያ ልየው፡” አልኩት። “አይ፡ ወዳጄ፡ አንድ ምልክት የለም። አይ፡ ወዳጄ፡ አንተ ጤናማ ሰው ነህ፡” አልኩት።

እሱም አለ፡ “ሂድና የጸሎት ካርዴን ተመልከት!”

207 አልኩትም፡ “በጸሎት ካርድህ ላይ የጻፍከው ምንም ግድ የለኝም።” አልኩት፡ “ከጸሎት ካርድ ጋር ምንም የምሠራው ነገር የለኝም፡” ያኔ ሳላስበው፡ አያችሁ። ደክሞኝና ዝዬ ነበር። እንደው እ… የእግዚአብሔር ጸጋ ግን፡ አያችሁ፡ አሁንም በዚያ ነበረ።

208 እሱ ከላካችሁ፡ የእናንተን ነገር መፈጸም ግዴታ፡ የእሱ እንደሆነ አስታውሱ። የኔ አይደለም፥ እሱ ነው። ላኪው እሱ ነው። የኔ ድርሻ እውነት በሆነው ላይ መቆም ብቻ ነው።

209 ሙሴ በትርን ወደ ታች በጣለ ጊዜ፡ እባብ ሆነች፡ ጠንቋዮቹም እንዲሁ አደረጉ፡ ሙሴስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ከመጠበቅ በቀር ምን ማድረግ ይቻለው ነበር? በቃ። ተመሳሳይ ነገር ነው። እሱ ትእዛዛቱን ፈጽሟል። የሆነውንም ታውቃላችሁ፡ አይደል? አያችሁ?

210 ይህ ሰው እንዲህ አለ፡ “አሁን፡” እንዲህ አለ፡ “ይኸው። የጸሎት ካርድዬን ተመልከት።”

211 እንግዲህ ሌላ ነገር ሳላስብ፡ “እንግዲህ፡ ምናልባት ብዙ እምነት ሊኖርህ ይችላል፡ ለዚያ ይሆናል፡” አልኩት፡ አያችሁ። እ… ምንም ትኩረት እንኳ ሳልሰጥ።

212 ያኔም የኮቱን ቁልፎች ፈታና ደረቱን ነፋ። ለታዳሚዎቹም፡ “ይኸውላችሁ!” አለ።

እኔም፡ “ምን እየተደረገ ነው” ብዬም አሰብኩ?

213 ዞሪያውን ተመለከተ። እንዲህ አለ፡ “ይኸውላችሁ!” “ተንኮሉን አያችሁ፡” ብሎ ጠየቀ? ያ ይሁዳችሁ ነው፡ ሃይማኖተኛ ሰው፡ የታላቅ የሐይማኖት ተቋም ሰባኪ። እንዲህም አለ፡ “ይኸውላችሁ! ‘በጣም ብዙ እምነት’ ነበረኝ። አሁን፡ እሱ በጣም ደክሟል፡ ያንን አእምሮ ማንበብ አቃተው። አያችሁ፡ ከእንግዲህ ወደ እሱ አይመጣም።” በዚያም እንዲህ አለ፡ “እምነቴ በጣም ታላቅ ስለነበረ አይደለም።” እንዲህም አለ፡ “ያንን በጸሎት ካርዱ ላይ ጽፌው ነበር፡ አሁን ግን ሊረዳው አልቻለም፡ አያችሁ።” እንዲህም አለ፡ “ተንኮሉ ያ ነው!”

214 “ምን እየሆነ ነው፡” ብዬም አሰብኩ? ያኔም የእግዚአብሔር ጸጋ ወረደ።

215 እንዲህም አልኩት፡ “ጌታዬ፡ እግዚአብሔርን ለማታለል በልብህ ውስጥ ሰይጣን ለምን አኖረብህ? ” የዘመናችን ይሁዳ! እንዲህም አልኩት፡ “አንተ የቸርች ኦፍ ክራይስት… ” ይቅርታ አድርጉልኝ። እንግዲህ፡ ተናግሬዋለሁ። “አንተ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ ነህ። ከዩናይትድ ስቴትስ የመጣህ፡ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነህ። ያም ሰማያዊ ልብስ ለብሶ እዚያ ላይ የተቀመጠው ሰው፡ ሚስትህና የእሱ ሚስት እዚያ ተቀምጠዋል፡ ትናንት ማታ አረንጓዴ ነገር በተዘረጋበት ጠረጴዛ ላይ፡ **እንደዚህ** ባለ፡ መጋረጃ በነበረበት——ላይ ተቀምጣችሁ ነበር፡ ይህም ‘አእምሮ ማንበብ’ እንደሆነና ዛሬ ማታ እንደምትመጡ ተስማምታችሁ ነበር።”

216 ያ ሰው ተነሳ። እንዲህም አለ፡ “ይህ ፍጹም እውነት ነው። አምላኬ ሆይ፡ ማረኝ!”

217 እንዲህም አልኩት፡ “ጌታዬ፡ በዚያ ካርድ ላይ ‘ሳንባ ነቀርሳና ካንሰር’ ብለህ ጽፈሃል፡ አሁን ተቀበል። የአንተ ነው።”

እሱም የሱሪዬን እግር ይዞ እየሳበኝ፡ እንዲህ አለ፡ “እኔማ አል… ”

218 እንዲህም አልኩት፡ “ልረዳህ አልችልም። አንተ ቀጥል። ይህ በአንተና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ነገር ነው። ፍርድህን በገዛ እጅህ በካርድህ ላይ ጽፈሃል።” ይህም ያዘው። ነገሩ በሙሉ ያ ነበረ።

219 አያችሁ፡ አስመሣይ-አማኞች፡ አታላዮች፡ በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ ስህተቶችን ለማግኘት ይጥራሉ። ይሁዳዎች እነዚህ ናቸው። እነዚያ ናቸው። ይሁዳ እንዴት እንደወጣ አያችሁ? ያ ሰው እንዴት እንደወጣ አያችሁ? አስመሣይ-አማኞች እንዲህ ይሆናሉ። አያችሁ፡ አስመሣይ-አማኞች፡ ኦህ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ በጣም የተማሩ ናቸው፡ በቃሉና በሃይማኖት መግለጫቸው መካከልም ታላቅ ትዕይንት ይመጣል። እና፡ ያም በሆነ ጊዜ፡ ልክ እንደ መሪያቸው፡ እንደ ይሁዳ ለየሐይማኖት ተቋሞቻቸው አሳልፈው ይሸጡታል። ይሁዳ ለራሱ የሐይማኖት ተቋም አሳልፎ ሸጠው፥ ቃሉ የሆነውን፡ ኢየሱስን፡ ለራሱ የሐይማኖት ተቋም ሸጠ፡ የእሱ አካል መሆኑን ከተናገረ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ ሰጠ።

220 አገልጋዮች አንዳንድ ጊዜ የክርስቶስ አገልጋዮች እንደሆኑ ይናገራሉ፡ ቃሉም ለዚያ ቀን የጸና ሆኖ ሙሉ በሙሉ ሲቆጠር፡ ይህም የዘመኑ መልእክት እንደሆነ ሲታወቅ፡ በዚያ ታዋቂ ለመሆን ሲሉ፡ ለራሳቸው የሐይማኖት ተቋም አሳልፈው ይሸጡታል፥ ልክ ይሁዳ እንዳደረገው፡ ኢየሱስን ለፈሪሳውያንና ለሰዱቃውያን

አሳልፎ እንደሰጠው ያደርጋሉ። ያ መንፈስ አይሞትም፡ ስለዚህ ያ በአማኞች፡ በአስመሣይ-አማኞችና፡ በማያምኑት መካከል አለ። አያችሁ፡ ይህ ልክ እውነት ነው፡ መጥቶ ኢየሱስን በሠላሳ ብር ሸጠው፥ ዛሬም ብዙ ሰዎች ለምግብ ትኬት፡ በሳምንት ለተጨማሪ መቶ ዶላር ይሸጡታል፥ ልክ ነው፡ በመካከላቸው የቆመውን፡ ሕይወታቸውን፡ በሙላት ቃል የገዛውን አምላክ ይክዳሉ።

221 እንዲህም ይላሉ፡ “ኦህ፡ የተአምራት ዘመን አልፏል!” ወይም፡ “ዛሬ እግዚአብሔር እንደዚህ ያለ ነገር አያስፈልገውም።” አያችሁ? “ኦህ፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ! ‘ሰላም ለኪ ማርያም፡ የእግዚአብሔር እናት፡ በሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡’” እነዚህንና ሌሎች ብዙ ነገሮችን ይናገራሉ! ከእነሱም አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፡ “በሐዋርያት የሐይማኖት መግለጫ አምናለሁ። ሁሉን በሚችል፡ በሰማይና በምድር ፈጣሪ፡ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ። በቅድስት የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንና፡ በእነዚህ ሁሉ ነገሮች አምናለሁ።”

222 የትኛው ሐዋርያ ነው እንደዚህ ያለ የሐይማኖት መግለጫ የነበረው እስኪ ንገሩኝ። ሐዋርያት የሐይማኖት መግለጫ ነበራቸው ከተባለ፡ በሐዋርያት ሥራ 2፡38 ላይ የተጻፈው ነው፡ “ንሰሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለኃጢአት ስርየት ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።” የሐይማኖት መግለጫ ነበራቸው ከተባለ፡ ያ ብቻ ነበረ። ምንም የሐይማኖት መግለጫ አልነበራቸውም። ቃሉ ነበረ። ይህ እውነት ነው። አሁንም ያው ሆኖ ይኖራል። ለኃጢአት በሽታ ፈውስ የሚሆን ማዘዣ ይህ ነው፡ “የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ! ለኃጢአት ስርየት ንሰሐ ግቡና ተጠመቁ፡ አያችሁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።”

223 ነገር ግን ልክ እንደ ይሁዳ፡ አሳልፈው ይሸጡታል። አስመሣይ-አማኙ ያ ነው። ከእነሱም አንዳንዶቹ ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች ናቸው። ይህንንም አስመሣይ-አማኝ፡ ያንን ሰው ተመልከቱት። ብልጣብልጡ ሰው ያ ነው። ያልወደደውን እያንዳንዱን ትንሽ ቃል በሰማ ጊዜ፡ በፍጥነት የሚቆጣ፡ ዘሎም የሚወጣው ይህ ትንሽ ሰው፡ ለእሱ ምንም ትኩረት አትስጡት፥ በመጀመሪያ ደረጃ፡ እሱ የማያምን ነው። ነገር ግን ይህ ዓይነቱ ሰው፡ አስመሣይ-አማኙ፡ ሲከተል ስታዩት፡ አያችሁ፡ ያ ይሁዳ ነው። እሱ ነው።

224 ታላላቅ ተሰጥኦዎች እንዳላቸው። እነዚህ ስሞችን እጠራለሁ። በእርግጥ፡ ማድረግ አልነበረብኝም፡ ነገር ግን እንድታውቁት ብዬ፡ እንዲሁ፡ እጠራቸዋለሁ። ልክ እንደ፡ ኤልቪስ ፕሪስሊ፡ ሬድ ፎሌ፡ ኤርኒ ፎርድ፡ ፓት ቡን። ኤልቪስ ፕሪስሊ፡ ጴንጤቆስጤ፥ ፓት ቡን፡ የቸርች ኦፍ ክራይስት አባል፥ ሬድ ፎሌ፡ በቸርች ኦፍ ክራይስት ዲያቆን፥ ኤርነስት ፎርድ ሜቶዲስት ይመስለኛል። እነዚህም ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች ሁሉ፡ ብልሆች ሆነው፡ በቴሌቪዥን ይቀርባሉ። ሰዎችም፡ “እንግዲህ፡ ሃይማኖተኞች አይደሉምን? መዝሙር ይዘምራሉኮ” ይላሉ። ይህ ምንም ትርጉም የለውም። አዎን፡ ጌታዬ። ዓለምን እያታለሉ ነው!

225 ከዚህ ምን ያገኛሉ? ይሁዳ ሠላሳ ብር አገኘ። ኤልቪስ፡ በርካታ የካዲላክ መኪኖችን፡ አንድ መቶ፡ ወይም ሁለት መቶ፡ አንድ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ዶላር፡ ወይም በቅጂዎችና በነዚህ በመሳሰሉት ነገሮች ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮችን አገኘ። ፓት ቡንና ሌሎቹም። በየትኛውም የሐይማኖት ተቋም ውስጥ

ቢሆኑ፡ ምንም ግድ የለኝም፡ ሁሉም ግብዝነት ነው። አስመሣይ-እምነት ነው። መሸፈኛ ነው። ያ፡ ሕይወታቸው የሚመሰክረው ነው፡ ትክክል አይደለም። በትክክል።

226 ያን ጊዜም ታላላቅ አደራጆች የሆኑ፡ ዓለማዊ ጥበብ ያላቸው ተሰጥኦ ያላቸው አሉ። ወንጌሉን፡ እንሰብካለን ይላሉ፥ ብልሆች፡ ምሁራን ሰዎች ናቸው። ሰሙኝ፡ በዚያ መሰክ የሠለጠነ ሰው፡ እሱ ሰባኪ አይደለም። እሱ ሌክቸረር ነው። ዛሬ ያለው ችግር ይህ ነው፡ ሌክቸረሮች በዝተውብናል።

227 ኢየሱስ መቼም ቢሆን፡ “ሂዱና ይህን ለማድረግ ሥልጠና ውሰዱ” አላለም። እርሱ ያለው፡ “ሂዱ ወንጌልን ሰበኩ፡ እነዚህም ምልክቶች ከሰብከቱ ጋር ይከተላሉ።” አያችሁ? አያችሁ?

228 ቆሞ ዝም ብሎ፡ አቤት፡ ውብ ነገሮችን በውስጡ በመጨመር በሊቀ መላእክት ፊት የተቀመጣችሁ እንዲመስላችሁ፡ የሚያደርግ ንግግር አቅራቢ መሆንን መማር አይደለም። ነገሩ ያ አይደለም። “የሃይማኖት መልክ አላቸው፡” አያችሁ፡ ያ ሌክቸረር ነው እንጂ፡ በሥራ ላይ ያለ መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

229 ሀሁ'ን እንኳን ያልቆጠረ ትንሽ ሰው፡ በቃሉ ላይ ባለው የእምነት ኃይል ሊመጣ ይችላል፥ መንፈስ ቅዱስም ያ ሰው ምንም የማያውቀውን ነገር እንዲያደርግ ያደርገዋል፡ እናም ይክዱታል። አያችሁ? ነገሩ እንዲህ ነው።

230 ታላላቅ ሰዎች! አዎን፡ ጌታዬ። ያን ጊዜም እነሱ አደራጆች ናቸው። በዓለማዊ ጥበብ የበለጸጉ፡ የተሳካላቸው፡ ብልሆች ናቸው።

231 ልክ ሰይጣን በዚያች በትንሿ፡ ረዳት አልባ በሆነችው ሴት፡ በሔዋን ላይ እንዳደረገው ነው። እሱም በቀጥታ ወደ እሷ መጣ ከነበረችበት ይልቅ ይበልጥ ጥበበኛ እንደምትሆን በሚያጓጓ አሳብ ሊያሳምናትም ፈለገ፡ እሷም ትፈልገው የነበረው ይህንኑ ነበረ። ቃሉ ከተናገረው ነገር ጋር ከመስማማት ይልቅ፡ እ— እሱ ይበልጥ ጥበበኛ እንደምትሆን በሚያጓጓ አሳብ ሊያሳምናት ፈለገ፡ እሷም የእሱን አሳብ ተቀበለች። ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ። “የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞኝነት ነው።” አዎን፡ ወዳጄ።

232 አይደለም፡ ጌታዬ! ኦህ፡ ማይ፡ ልክ ፈሪሳውያን ባወቁት ጥበብ አሳልፈው የሰጡትና፡ ያደረጉት፡ ያንኑ ነገር ነው፡ አያችሁ። የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ— ግን ይክዳሉ።

233 በትክክል ሲረጋገጥና ቃሉም ለእነሱ የጸና በሆነላቸው ጊዜ፡ አሁንም አንዳንድ ነገር ለመንቀስ ይጥራሉ፡ ይህም ተንኮል እንደሆነ ያስባሉ። በአእምሯቸው አልተረጋገጡም። ማመን አይችሉም። ማንኛውንም ነገር ልትነግራቸው ትችላለህ፡ እነሱ ግን ተመልሰው ይመጣሉ፥ ማንኛውንም ነገር ልትነግራቸው ትችላለህ፡ እነሱ ግን ተመልሰው ይመጣሉ። እነሱም እንዲሁ... ሊገባቸውም አልቻለም፡ አያችሁ። እና ተመልከቷቸው፥ ቀዳዳ ፍለጋ፡ ጊዜ ይጠባበቃሉ። የሚፈልጉት ያ ብቻ ነው።

234 የእግዚአብሔር ጸጋ ባይሆን ኖሮ፡ ምናልባት፡ አንዳንድ ቀዳዳዎቼ ቢኖሩብኝ ኖሮ፡ ሁሉም ይገለጡ ነበር። አያችሁ? የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፡ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ምንም ቀዳዳ የለም፥ ቀጥተኛው ወንጌል ብቻ ነው። ሁልጊዜም የምናገረው፡ ማንም ቢሆን፡ ሳስተምር ወይም የእግዚአብሔርን

ቃል የማይመስል ነገር ሳደርግ ካያችሁኝ፡ መጥታችሁ ንገሩኝ። እናንተ ለማግኘት የምትጥሩትን ቀዳዳዎች የሚሸፍነው ነገር ይህ ነው። ዓይኖቻችሁን በዚያ ላይ ብቻ አድርጉ፡ ምንም ቀዳዳዎችን አታዩም፡ ምክንያቱም ምንም ቀዳዳ የለምና።

235 አሁንም አስታውሱ፡ ይሁዳ ያገኘ ይመስለው ነበር። ያ ሰው ያገኘ ይመስለው ነበር። ብዙ ጊዜ፡ ያገኙት ይመስላቸዋል፡ ነገር ግን እንዳልሆነ ይረጋገጣል። አስመሣይ-አማኞች፡ ግብዞች እነዚህ ናቸው። እነሱ በቃሉ ላይ ዘጠና-አምስት በመቶ ናቸው፡ ሔዋንም እንዲሁ ነበረች፡ ሆኖም፡ ዘጠና-ዘጠኝ ነጥብ ዘጠኝ-በመቶ፥ ነገር ግን ሞትንና ሐዘንን ሁሉ ያመጣው ያ አንዱ አሰረኛ ክፍል ነበረ።

236 ይህም የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉ በሙሉ ስለማይቀበሉ፡ ድርጅትና ነገሮችን የሚኰንንበት አንዱ ነገር ያ ነው። አስመሣይ-አማኞች እነዚህ ናቸው። ሁልጊዜም እንደነበረ እናውቃለን፡ ነገር ግን እውነተኛውን፡ የጸናውን ቃል ይክዳሉ። እነዚህ ሁልጊዜ በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ አሉ። አብረውን ሲጓዙ እንደምናውቃቸው፡ እንዲሁም እጅግ ሃይማኖተኞች ናቸው።

237 አሁን፡ አሁን ለመጨረስ በዝግጅት ላይ ነኝ፡ ምክንያቱም ሌላ ግማሽ ሰዓት ወስጄያለሁና።

238 ኢየሱስ፡ ስለ እነዚህ የመጨረሻ ቀናትና ስለ እነዚህ ዓይነት ሰዎች እንዳስጠነቀቀን አይተናል፡ እነሱ እውነተኛውን ነገር በጣም ስለሚመስሉ፡ ፍጹም የተመረጡትን እንኳ ለማታለል ይጥራሉ። ይህ ምንድን ነው? ይሁዳዎች እነዚህ ናቸው፡ በጣም ከፍ ብለው የሚሄዱ ሰዎች—እነሱ ናቸው። ተመልከቱ፡ እነርሱ ማልቀስ፡ መጮኽ፡ አጋንንትን ማውጣት መቻላቸውን መናገር፡ ሁሉንም ነገር ማድረግ እንኳ ይ—ይችላሉ፡ ከዚያም ወደ ኋላ ተመልሰው ቃሉን ይክዳሉ። በትክክል። የሃይማኖት መልክ አላቸው። እ—እ—እነሱ ሊቃረቡ...

239 ይሁዳ እስከ የት እንደመጣ ተመልከቱ። የይሁዳ መንፈስ በወንጌል ውስጥ፡ እስከ ጴንጤቆስጤ ሰፍራ ድረስ ወጣ። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚጠመቅበት ጊዜ ሲደርስ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር የሚሄዱት፡ እነዚህ ሌሎች ነገሮች ሲመጡ ጥሎ ወጣ። እውነተኛ ማንነቱን አሳየ። ያም መንፈስ በእነዚያ የሐይማኖት ተቋማት ውስጥ እስከዚያ እውነት ድረስ ሊኖር ይችላል፡ ከዚያም ወዲያው ወደ ኋላ ይመለሳል፡ ልክ በእነሱ ላይ እንዳለው መንፈስ፡ መምጣታቸውን እንደ ቀደመው፥ ልክ ዮሐንስ የኢየሱስን መምጣት እንደቀደመው።

"አሁንም ትላላችሁ፡ 'ኢየሱስ በጣም ይቀራረባሉ ብሏልና።'"

240 አሁንም፡ "የተመረጡት፡" ማለት ሰማቸው፡ ሕይወት ከጀመረ ጀምሮ፡ በሕይወት መጽሐፍ ላይ የተጻፈው፡ የሚያምኑቱ፡ ማለቴ ከዓለም ምስረታ ጀምሮ፡ የሕይወትን ቃል ሁሉ የሚያምኑት ወገኖች ናቸው። የተመረጡት እነዚህ ናቸው።

241 አሁን እነዚህን ሰዎች ተመልከቱ። አሁን፡ ይህንን በአክብሮት እና በትህትና እናገራለሁ፡ በአምላካዊ ፍቅር ይህን እናገራለሁ፥ ካልሆነ ግን፡ እ—እ—እኔ—ራሴ፡ የመሠዊያ ጥሪ ያስፈልገኛል። ልብ በሉ፡ ኢየሱስ እውነተኛ የተመረጡትን እንኳ እንደሚያታልሉ ተናግሯል። አሁን፡ ይህ ሜቶዲስት አይሆንም፡ ባፕቲስትም አይሆንም፥ በመጀመሪያ ደረጃ፡ እነሱ የማያምኑ መሆናቸውን እናውቃለን። ነገር ግን፡ ወደዚያ የሐይማኖት ተቋም ውስጥ የገቡት የጴንጤቆስጤ ድርጅቶች ናቸው፡ ያለ ቃሉ፡ የራሳቸውን ወሰን

አበጁ፥ የራሳቸውንም ድርጅት በማቋቋም ወሰን አበጁ፡ ቃሉንም አገለሉ። የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ፡ እጅግ ይመሳሰላሉ! “ያለቅሳሉ። ይጮኻሉ። ወደ-ላይ-እና-ታች ይዘላሉ። የፈውስ አገልግሎቶች አሉን፡” ይላሉ። ይሁዳም እንዲሁ አደረገ፡ ሌሎቹም ሁሉ እንዲሁ አደረጉ። በወጡ ጊዜ፡ በደስታና በሁሉም ነገር ተሞልተው ተመለሱ፡ ስማቸውም በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ ነበር።

242 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ሙሽራይቱ በእንደዚህ ዓይነት ቡድን ውስጥ አ—አ—አትመጣም። በመነጠቅ ትሄዳለች።

243 በፍርዱ ጊዜ፡ ፍርዱ ተዘጋጀ፡ “መጻሕፍትም ተከፈቱ፡ የክፋዎች፥ ሌላም መጽሐፍ፡ እሱም የሕይወት መጽሐፍ፡ ተከፈተ፡” ሙሽራይቱም ፍርድ ለመስጠት በዚያ ነበረች። አያችሁ? አያችሁ? “የሕይወት መጽሐፍ የሆነው፡ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ።” በአንድ በኩል በጎች፡ በሌላውም በኩል ፍየሎች አሉ። አያችሁ፡ ያኔ የሞቱት፡ ዕድሉን ፈጽሞ ያላገኙት ሰዎች፡ የሚለዩት እነሱ ይሆናሉ።

244 ነገር ግን አሁንም ልብ በሉ፡ እውነተኛ የተመረጡትን “ማታለል”፡ ያንን ቡድን ተመልከቱት። ያ አብሮ የሚከተለው ቡድን እንዲህ ይላል፡ “አዎን፡ ወንድሜ። ሃሌ ሉያ! አዎን። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!” በልባችሁም ውስጥ ምን ለማድረግ እንደሚሠሩ ታዩታላችሁ፥ በቤተክርስቲያን ውስጥ (ለምን?) ህዝብን ለመሳብ፡ ማግኘት የሚችሉትን እያንዳንዱን ሳንቲም ለመበዝበዝ ይፈልጋሉ። ይህን የማላውቅ ይመስላችኋል? እነሱ የማውቅ ላይመስላቸው ይችላል፡ ነገር ግን አውቀዋለሁ።

245 ኢየሱስ ከመጀመሪያው፡ አታላዩ ማን እንደነበረ፡ ያውቅ ነበር። አያችሁ? አያችሁ? ነገር ግን ምን አደረገ? እስከዚያ ጊዜ ድረስ ጠበቀ። ሁልጊዜም ማድረግ ያለብን ይህንኑ ነው፡ እስከዚያ ድረስ መጠበቅ። ራሳችሁ አትንቀሳቀሱ። እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ጠብቁ።

246 የአምልኮ-... መልክ አላቸው፡ አብረውም ይሄዳሉ፡ ያ አታላይ ቡድን ነው። ያንን አታላይ፡ ያንን ቡድን ተመልከቱት፥ አ—አማኙ አይደለም፡ የማያምነው አይደለም፡ ነገር ግን ያ አስመሣይ-አማኝ ነው። ኦህ፡ ማይ! ምን እያደረጉ ነው? አንዳንድ ነገር ማግኘት የሚችሉ እስኪመስላቸው ድረስ ዝም ብለው እንደ አረም ይሄዳሉ፡ ማግኘት የሚችሉትን እያንዳንዱን ሳንቲም ከህዝቡ ውስጥ ይበዘብዛሉ፡ አያችሁ፡ ከዚያም በነዚህ ታላላቅ ድርጅት ውስጥ ያከማቹታል፥ ይህም ፍጹም የሚቃረን ነው፡ እነሱም ያውቁታል። አያችሁ፡ እነሱ ያውቁታል።

247 እናንተ የምትናገሩት ነገር ምንም ለውጥ አያመጣም። እናንተ ከመምጣታችሁ በፊት ሁልጊዜም ለህዝባቸው፡ “እንዳትሰሙት” ብለው ያስጠነቅቃሉ።

248 አንድ ሰው፡ በኦሃዮ በድፍረት ቆሞ፡ ወንድም ኪድ በተፈወሰ ጊዜ፡ ወደ መድረኩ መጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ “አሁን፡ ወንድም ብራንሃም በቅባቱ ስር በሆነ ጊዜ፡ ያለ ምንም ጥርጥር ነቢይ ነው። አሁን ግን፡” እንዲህ አለ፡ “ቅባቱ ከእርሱ ሲለቀቅ፡” “ትምህርቱን አትመኑት፡ ምክንያቱም ስህተት ነው፡” አለ።

249 በክፍሌ ውስጥ ተቀምጬ ሳለሁ፡ ጌታ ይህንን እንደገለጠልኝ፡ እሱ አያውቅም ነበር። እኔም እዚያ ጠጋ አልኩኝ። እና ብዙዎቻችሁ በዚያ ነበራችሁ።

አልኩት፡ “አንድ ሰው ለምን እንዲህ ያለ ነገር ይናገራል፡ ቃሉ ራሱ… .” አሁን፡ እያችሁ፡ ነቢይ ነኝ ብዬ መቼም አልተናገርኩም፥ እሱ ነው የተናገረው።

250 ነቢዩም፡ **ነቢይ** የሚለው ቃል፡ “ባለራእይ፡” በብሉይ ኪዳን-… አሁን፡ በእንግሊዝኛው ትርጉም **ነቢይ** ማለት “ሰባኪ” ማለት ነው። ነገር ግን የብሉይ ኪዳኑ **ባለራእይ** “መለኮታዊ የቃል ትርጓሜ” የነበረው፡ ቃሉም ወደ እሱ በመምጣቱና አስቀድሞ በማየቱ የተረጋገጠ ሰው ነበረ። ይህም…

251 አንድ ሰው ደግሞ አንድን ሰው ነቢይ ስለመሆኑ እየተናገረ፡ ትምህርቱ ስህተት ነው ይላልን? ይህ የገንዘብ-ማግኛ ዘዴ ካልሆነ፡ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ያ ነገር ገሃድ የሚወጣበት ሰዓት ቀርቧል። አዎን። ሆኖም ያ ዓይነቱ፡ አስመሣይ-አማኝ፡ ጀርባችሁን መታ መታ እያደረገ፡ ልክ እንደ ይሁዳ “ወንድም፡” ብሎ የሚጠራችሁ ነው። ዳሩ ግን፡ አስታውሱ፡ እሱ ከመጀመሪያው ያውቅ ነበር። አሁንም ያውቃል። አዎን፡ ጌታዬ።

252 አስታውሱ፡ ይህንን ቴፕ የምትሰሙት፡ እናንተም ደግሞ፡ አዎን፡ ከእነዚህ ክፍሎች በአንዱ ውስጥ ናችሁ። ይህ ፍጹም ትክክል ነው። አሁን ልንጨርስ ነው። እዚህ በአካል ያለው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ይህንን ቴፕ የሚሰማው እያንዳንዱ ሰው፥ እነሆ አንድ ቀን ከዚህ ዓለም መለየቴ የማይቀር ቢሆንም እንኳ፡ እነዚህ ቴፖች አሁንም በሕይወት ይኖራሉ። ልክ ነው። እያችሁ? እናንተም ከእነዚህ ምድቦች በአንዱ ውስጥ ናችሁ። ከእነሱ በአንዱ ውስጥ መሆን አለባችሁ። በትክክል። ማምለጥ አትችሉም። ከእነዚህ ምድቦች በአንዱ ውስጥ ናችሁ።

253 አሁንስ ምንድን ነው? ቃሉ በተረጋገጠበት ጊዜ ባመናችሁበት ሁኔታ፡ ዛሬ ማታ እኔም እንዳረጋገጥኩት፡ ሁልጊዜም በህዝብ ተቀባይነት ካለው እምነት ጋር የሚቃረን የጸና ቃል እንደነበረ፡ ራሳችሁን ካመኑ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባህሪ ጋር ቁጠሩ።

254 በኖኅ ዘመን ኖራችሁ ቢሆን ኖሮ፡ አሁንስ ልጠይቃችሁ፡ በየትኛው ወገን ትሆኑ ነበር፡ በቤተክርስቲያን ወገን፡ ወይስ በነቢዩ በኖኅ ወገን? እያችሁ?

255 በሙሴ ዘመን ኖራችሁ ቢሆን ኖሮ፡ መልእክቱ በእግዚአብሔር ከተረጋገጠና ከጸና በኋላ የሙሴን መልእክት ታምኑ ነበርን? ወይስ ከቆሬ እና ከዳታን፡ ከሌሎቹም ጋር በመሄድ፡ እንዲህ ትሉ ነበር፡ “አንተ ብቻ አይደለህም ቅዱስ ሰው። ሌሎች ሰዎችም ደግሞ፡ አንተ የምታደርጋቸው እነዚህን ነገሮች ማድረግ አይችሉምን” ትሉ ነበርን? እያችሁ? እያንዳንዳችሁም የአንዱ ወገን ትሆኑ ነበር፡ ዛሬ ማታም፡ ናችሁ።

256 ወይስ ከዳንኤል ጋር ትሆኑ ነበርን፡ ወይስ በናቡከደነጾር ግብዣ ላይ እዚያ ታች ከነበረችው ቤተክርስቲያን ጋር? እያችሁ? ወይስ እዚያ ታች በጭፈራው፡ በዚያ—በዚያ ታላቅ በነበራቸው ነገር ላይ፡ በውጭ ትገኙ ነበርን?

257 ብቻውን ቆሞ ከነበረው፡ “ጊዜ ያለፈበት ጨቅጫቃ፡ አእምሮውን የሳተ ሰው፡” ከተባለው፡ በተራራውም ራስ ላይ ቆሞ፡ ራሱም በዚያ በፀሐይ ላይ ከሚያበራው፡ በጺም የጠማማ በትር ከነበረው፡ ወፎችም ይመግቡት ከነበረው፡ ኧ-ህ፡ ከእንዲህ ዓይነቱ ጨቅጫቃ ኤልያስ ጋር፡ ትሆኑ ነበርን? ወይስ ከካህናቱና እዚያ ከኤልዛቤል ጋር ከነበሩት ሁሉ፡ ዘመናዊ-ልብስ ከለበሱት ከሌሎቹ ሴቶች ጋር? ኤልያስም እዚያ ላይ ቆሞ፡ በሙሉ ኃይሉ፡ ይገሥጻቸው ነበር!

ሚሰታችሁን ወደ የትኛው ወገን ትወስዷት ነበር? ዝም ብላችሁ አሰቡ። ዛሬ ማታ እራሳችሁን በዓይነ ሕሊናችሁ ተመልከቱ።

258 በኢየሱስ ዘመንስ፡ ምንም ዓይነት የማረጋገጫ ሰነድ ከሌለው ከዚህ ብላቴና ጋር ትሆኑ ነበርን? ምንም ዓይነት የየሐይማኖት ተቋም ግንኙነት አልነበረውም። እነሱም፡ "ከየትኛው ትምህርት ቤት ነው የመጣኸው? እዚህ በምዝገባችን ላይ የለህም። ይህን ጥበብ እንዴት አገኘኸው? እኛ ካላስተማርንህስ እንዴት ልትማር ቻልክ? በየትኛው ትምህርት ቤት አልፈህ መጣህ? ሜቶዲስት ነህ፡ ፕሪስቢቴሪያን፡ ወይስ ባፕቲስት?" ከእነዚህም የትኛውም አልነበረም። [አንድ ወንድም፡ "ቃል ነበረው" አለ።—አርታዒ።] ልክ ነው። እርሱ ቃል ነበር። ትክክል ነው፡ ወንድሜ። እ...

259 ወይስ በጣም የዋህና ደግ ከሚመስለው ከትሑቱ ያረጀ ካህን ዘመናዊ እምነት ካላቸው ከፈሪሳውያን ጋር፡ ከኒቂያ ጉባኤ ጀምሮ ወይም ሉተር ካደራጀው ጀምሮ፡ ከቆመው ድርጅት ጋር ትወግኑ ነበርን? ወይስ በየትኛው—በየትኛው ቡድን ውስጥ ትሆኑ ነበር? በዚያ በ... በየትኛው ቡድን ውስጥ ትሆኑ ነበር? ቃሉ በጸናበት ጊዜ ባያችሁትና ለእናንተም በተረጋገጠላችሁ ጊዜ፡ የሰዓቱ መልእክት እንደነበረ፡ ወይስ ቤተክርስቲያንን ትቆማላችሁን? አሁንስ ዛሬ ማታ እራሳችሁን በዓይነ ሕሊናችሁ ተመልከቱ።

260 ሐዋርያቱ ኢየሱስንና እነዚህን ድንቅ ነገሮች ሁሉ ባዩ ጊዜ፡ በእነዚያ ሰባኪያን ላይ በጮኸባቸውና፡ "እናንተ የእባብ ጎጆዎች ናችሁ፡" ባላቸው ጊዜ፡ ከእነሱ ጋር በዚያ ትሆኑ ነበርን? እነዚያ ታማኝ፡ ሰባኪያን ያንን ቃል ያጠኑ ነበር። አላቸውም፡ "እናንተ የወንበዴዎች ዋሻ እንጂ ሌላ አይደላችሁም፡ እ—እናንተ በሙታን አጥንት ተሞልታችኋል። የተለሰኑ ግድግዳዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም።" አያችሁ? "እናንተ የእፉኝት ትውልድ።" በዚያ ቆሞ ከገሠጻና፡ ካፈራረሳቸው ግልፍተኛ-ሰው ጋር ትቆሙ ነበርን? አላቸውም፡ "ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? አባቴ የተናገረውን የማላደርግ ከሆነ... "

261 እነርሱም አሉ፡ "አትሰሙት። ይህ ሰው ክፉ መንፈስ አለበት። እብድ ነው። እሱ እብድ ነው። የ—የሰይጣን መንፈስ አለበት። አያችሁ? አሁን፡ እ... ይሄን የሚያደርገው፡ እርሱ፡ የጠንቋይ መንፈስ አለበት። እ... እሱ ምንድነው? እናቱ እሷና ባሏ ከመጋባታቸው በፊት ወለደችው። አያችሁ? አያችሁ? ከየትኛው ትምህርት ቤት የመጣ ነው? ወደ ሰዋሰው ትምህርት መግባቱ የሚገልጽ አንዳች ማስረጃ የለንም።"

262 ሆኖም ገና የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለ፡ በእግዚአብሔር ቃል፡ ካህናቱን አስደንቆና ግራ አጋብቶአቸው ነበር። አያችሁ? ከየትኛው ትምህርት ቤት ነው የመጣው? ከላይኛው ትምህርት ቤት ነው። አያችሁ? "የሰው ልጅ ከነበረበት ወደላይ ሲወጣ ባያችሁ ጊዜ።" አያችሁ፡ የእሱ ትምህርት ቤት ያ ነበረ።

263 ዳሩ ግን ወሳኙ ፈተና ሲመጣ፡ እንደዚያ ካለ ሰው ጋር፡ ከሐዋርያቱ ጎን ትቆሙ ነበርን?

264 ወይስ በእርግጥ ከሰባዎቹ ጋር በመሄድ፡ እንዲህ ትላላችሁን፡ "እንግዲህ፡ 'የሰው ልጅ' ነኝ፡ እያልክ፡ የምታስተምረው በዚህ መንገድ ከሆነ፡ ወደ ቤት ክርስቲያናችን እንመለሳለን? እንዴ፡ በመሰረቱ፡ አንተ ማን ነህ? ምንድን ነህ? እንደኔው ሰው ነህ፡ አብሬህ እበላለሁ፡ ደግሞም ትልቅ ነገር እንደሆንክ ልትናገር

ትሞክራለህ። ታዝቤሃለሁ። ድካምህን አይቻለሁ። ስታለቅስ አይቼሃለሁ። **ይህን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** ስታደርግ አይቼሃለሁ። ከእኛ ጋር ወደ በረሃ ስትሄድ፡ ከዚህም ጋር የሚመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ አይቻለሁ፡ አንተ ተራ ሰው ብቻ ነህ። ከሰማይም እንደ ወረድክ ትናገራለህ። ይህ ለኔ ይከብደኛል።” ከእነርሱ ጋር ትጓዙ ነበርን? ወይስ ከሰባዎቹ ጋር ጥላችሁ ትወጡ ነበርን? ወይስ ከሐዋርያቱና ከክርስቶስ ጋር ትቀጥሉ ነበርን?

265 ቅዱስ ማርቲን፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚደረገውን ጥምቀት ለማቆየት ሲሞክር፡ አሁንም ምልክቶችን ድንቆችን ሌሎችንም ነገሮች አጥብቆ ለመያዝ ሲሞክር፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያንን ሰው ስታወግዘው ፈጽሞም እውቅና ስትነፍገው፡ ወደ ውጭም ስታባርረው፡ እናንተ ከካቶሊክ የሐይማኖት መግለጫ ጋር ትቆሙ ነበርን፡ ወይስ ከቅዱስ ማርቲን ጋር ትቆሙ ነበርን? እነዚህን የ—የሞቱ ሰዎችን ምስሎች አቁሞ፡ እነርሱን ለማምለክ፡ ምስሎቹን ለማምለክ፡ የመሳሰሉትንም ለማድረግ፡ እምቢ ያለ ጊዜ፡ የተጨመሩትን ዶግማዎች በተቃወመ ጊዜ፡ “ቃሉ እውነት ይሁን” አለ! እግዚአብሔርም በታላቅ ምልክቶችና ድንቆች አረጋግጦታል፡ እርሱ የተነበየውንም ሆነ። ያደረገውንም ሁሉ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመላለሰ አረጋገጠለትም፡ ከእነዚያ ካህናት መካከል አንዱም ሆነ ሌላ ማንም ሰው ምንም ሊያደርግበት አልቻለም። የእርሱን ወገን ይዛችሁ ከቅዱስ ማርቲን ጋር ትሄዱ ነበርን፡ ወይስ ከካቶሊክ የሐይማኖት መግለጫ ጋር ትሄዱ ነበርን?

266 አሁንም ቃሉ፡ አሁን የእግዚአብሔር ቃል ወይም የቤተ ክርስቲያን ዶግማዎች፡ በፊታችሁ ቀርበዋል። የቤተ ክርስቲያንን ዶግማዎች ትወስዳላችሁ፡ ትቀበላላችሁ፡ ወይስ ቃሉ የሚለውን ትወስዳላችሁ?

267 አስታውሱ፡ በዘመናት ሁሉ አሁን እንዳለው ሆኖ አልፏል። በሕዝቡ ዘንድ ሁልጊዜ ታዋቂ የሆነ እምነት አለ፡ ይህም ሁልጊዜ ከእውነተኛው ቃል ጥቂት ያፈነገጠ ሆኖ ቆይቷል። አስታውሱ፡ በፍጹም በግልጽ-ቃሉን መካድ ሆኖ አያውቅም። ኦህ፡ በፍጹም። የክርስቶስ ተቃዋሚ ቃሉን አይክድም። በእርግጥ አይክድም። እርሱ እንደሚያምን ይናገራል፡ ዳሩ ግን እዚህ ላይ በተጻፈው መንገድ ሙሉ በሙሉ አይደለም። አያችሁ? አያችሁ?

268 ሰይጣን ለሔዋን ነገራት፡ ሔዋንም ሁሉንም አመነች፡ እርሱ የነገራትን ግን ያቺ ጥቂት ነገር ብቻ ናት። እነርሱ ሁሉንም ይወስዳሉ ነገር ግን፡ ያቺን ጥቂቷን ብቻ፡ “ወደ ገንዳው ሂዱ” ልትሆን ትችላለች፡ ወይም ሌላ ነገርም ሊሆን ይችላል፥ እርሱን መቀበል አለባችሁ፡ እያንዳንዱን ክፍል፡ **እዚህ** ላይ እንዳለው አድርጋችሁ፡ አያችሁ፡ **እዚህ** ላይ እንደተነገረው አድርጋችሁ፡ ይህ አንዳንድ የመጀመርያ ሥራዎችን እንድትደግሙ ሊያደርጋችሁ ይችላል፡ ዳሩ ግን ቃሉ ያለው ይህንኑ ነው። ሰይጣን መጀመሪያ በሔዋን ላይ ከሠራው ጊዜ ጀምሮ የእርሱ ማታለያ ይህ ሆኖ ቆይቷል፡ ከቃሉ ጥቂቷን ብቻ ላለማመን ማድረጉ ነው።

269 ደግሞም፡ እነዚህን ሦስት የሰዎች ክፍሎች ሁልጊዜ ይለያል፡ ቃሉ እነዚህን ሰዎች ይለያቸዋል። በየዘመናቱ ሁሉ እንደዚሁ ሆኖ ቆይቷል። በነበሩት ዘመናት ሁሉ፡ እንደዚሁ ሆኖ ቆይቷል፡ እግዚአብሔር የሆነ ነገርን ወደ መድረኩ ሲልክና፡ የእርሱ ቃል ሆኖ በግልጽ ሲቆጠር።

270 ከዚያም የሚከተሉ አሉ፡ አማኞች መሆናቸውን የሚናገሩ አሉ፡ በእርግጥም ናቸው። ወደኋላ የማይመለሱ እነዚህ ናቸው። ቃሉን ያምናሉ። እናንተ በቃሉ ውስጥ እስካላችሁ ድረስ፡ እነርሱም ያምኑታል።

271 ዳሩ ግን ጥቂት ተቃራኒ ሆኖ ሲመጣ፡ እግዚአብሔር ከሚያምኑት ጋር ምን ያህል ያለ ቢመስልም፡ "እንግዲህ፡ እ—እ—እኔ **ስለዚህኛው** አላውቅም፡" ይላሉ። ያ የማያምን ነው።

272 ወይስ፡ "ኧ-ህ፡ ይኸውላችሁ" ለማለት እድል እስክታገኙ ድረስ ብቻ አብራችሁ ትከተላላችሁን! እርሱ እንዳደረገው፡ ሰውን ከጀርባው እንደሚወጋ ይሁዳ። "ውሎ አድሮ፡ መውጣቱ እንደማይቀር አውቃለሁ። ይኸውላችሁ!" ያ አስመሳይ-አማኝ ነው። እያንዳንዱ፡ እያንዳንዷ ነገሩ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይተነዋል።

273 በአንድ ወቅት እዚህ ኬንታኪ ውስጥ፡ ራቅ ብሎ፡ በተራሮች ላይ ያደገ አንድ ትንሽ ልጅ፡ እርሱ—እርሱ የሚታይ መስታወት ባለበት አካባቢ ፈጽሞ ሄዶ አያውቅም ነበር። በዛፍ ላይ የተለጠፈች ትንሽ ቁራጭ ነበረቻቸው፡ ሆኖም ራሱን ፈጽሞ አይቶ አያውቅም ነበር። ወደዚህ ወደ ሉዊስቪል እንደመጣ፡ ይነገራል፡ ከእናቱ እህት ጋርም አረፈ። እርሷም ውብ ከሆኑ ቤቶች በአንዱ ውስጥ ትኖር ነበር፡ የድሮ-ዓይነት ቤት። ወደ እንደኛው መ—መኻታ ክፍል ሲገቡ ሙሉ ለሙሉ ከላይ-እስከ-ታች በር ላይ፡ መስታወት ወ—ወዳለው መኻታ ክፍል ገቡ። አያችሁ?

274 ትንሹም ልጅ በቤቱ ውስጥ መሮጥ ሲጀምር፡ ቆመ። ትንሹ ጃኒ ህጻን ጃኒን አየው። አያችሁ? ራሱንም አከከ፡ በመስታወቱ ውስጥ ያለው ትንሹ ጃኒም ራሱን አከከ። ሳቀ፡ በመስታወቱ ውስጥ ያለው ትንሹ ጃኒም ሳቀ። ወደላይ-እና-ወደታች ዘለለ፡ እና ትንሹ ጃኒ በመስታወት ወደላይ-እና-ወደታች ዘለለ። አያችሁ? በጣም ተጠግቶ ቀረበ። አብሮት ሊጫወት የሚችል ትንሽ ልጅ እንደሆነ ሰላሰበ፡ ተጠግቶ ቀረበ። በቀጥታ፡ መስታወቱን ቆረቆረው። ዞር ሲል፡ ወላጆቹ ይመለከቱት ነበር። እርሱም፡ "እማማ፡ ያ እኔ ነኝ" አለ።

275 አሁን እናንተ **በዚህ** ውስጥ ትመለከታላችሁ፡ ታዲያ የትኛው ናችሁ? ኧ-ህ። ኧ-ህ። **ከእነዚህ** ትንንሽ ጃኒዎች መካከል የትኛውን ነው የምትወክሉት? የትኛው ናችሁ፡ አያችሁ? ከእነርሱ አንዱ ናችሁ።

276 ጉድለት ነው ብላችሁ የጠራችሁትን፡ የመጀመሪያውን ጉድለት እንዳገኛችሁ፡ ወደኋላ የሚመለሰው፡ ከእነርሱ አንዱ ያ ነው። አያችሁ?

277 ቃሉ ሁሉንም ነገር የሚያረጋግጥ ከሆነ፡ በቃሉ ፈትኑትና ትክክል መሆኑን እዩ። አያችሁ፡ ሁሉንም ነገር በቃሉ አረጋግጡ። ኢየሱስም እንዲሁ ብሏልና። አዎን፡ ወዳጄ። "መልካም የሆነውን አጥብቃችሁ ያዙ።" እርሱ ያለው ይህ ነው።

278 አሁን በሌሎች ዘመናት፡ በእግዚአብሔር ቃል መስታወት ውስጥ ተመልከቱ፡ ከእነዚህ ከሦስቱ ክፍሎች በየትኛው ውስጥ ልትቆጠሩ እንደምትችሉ እዩ። አሁን እስቲ አስቡ፡ በኖኅ ዘመን ኖራችሁ ቢሆን፡ በሙሴ ዘመን ኖራችሁ ቢሆን፡ በኢየሱስ ዘመን ኖራችሁ ቢሆን፡ ወይም ከእነርሱ በአንዱ፡ ምንም ይሁን ምን፡ በየትኛው ክፍል ውስጥ ትቆጠሩ እንደነበር እስቲ አስቡ። ዛሬ ማታ አስቡበት።

279 ከዚያም፡ የአሁኑ ጊዜያችሁ። አሁን፡ እስቲ አሁን አስቡ። ይህ አሁን ጥልቅ ነው። በላዩ ላይ ዝም ብላችሁ አትለፉት። ልክ አሁን ያላችሁበት የአሁን ሁኔታችሁ በዚያን ጊዜ ከየትኛው ክፍል ጋር ትሆኑ እንደነበር ያረጋግጥላችኋል። አሁን፡ ለራሳችሁ ፈራጆች ናችሁ፡ ምን እንደሆናችሁ ያረጋግጣል።

280 ቄስ፡ አገልጋይ፡ ኢየሱስ ያንን ለማመን የሚከብድ ንግግር በተናገረ ጊዜ ከየትኛው ክፍል ጋር ትሆኑ ነበር? ከየትኛው? ከየትኛው? እርሱ ቃሉ እንደሆነ በሚገባ ከተቆጠረ በኋላ፡ አያችሁ፡ ሆኖም፡ ያ ንግግር፡ እንደዚያ ያለ ነገር ፈጽሞ ሰምታችሁ አታውቁም፡ "የሰው ልጅ፡ ከነበረበት ወደ ሰማይ ሲወጣ ብታዩስ ምን ትላላችሁ? "

281 እናንተም፡ "እንግዲህ፡ የት እንደተወለደ አውቃለሁ። አባቱን አውቃለሁ፡ እናቱን አውቃለሁ፡ እዚህ ደግሞ ወደ ላይ እንደሚያርግ ይናገራል" አላችሁ። ያ ለእናንተ ትንሽ የሚከብድ ሆኖባችሁ ነበር፡ አይደል እንዴ፡ ጌታዬ? ኧ-ህ። ትንሽ የሚከብድ ሆኖባችሁ ነበር፥ ያንን መዋጥ አቅቷችሁ ነበር። ምናልባት ዛሬም ያው ተመሳሳይ ነገር ነው። ታዲያ በእግዚአብሔር ቃል መሰታወት ውስጥ ተመልከቱት የት እንደምትቆሙም እዩ። ኦህ፡ የሰው አሳች፡ ያንን ፈጽሞ እንዳታደርጉት።

282 ተመልከቱ፡ ከእነዚህ መደቦች ውስጥ በአንዱ ናችሁ። አሁን ባላችሁበት የአሁን ሁኔታ፡ የአሁን የአእምሮ ሁኔታ፡ ይኸውም፡ እዚህ በዚህ በሚታየው ታዳሚ ውስጥ ያላችሁ፡ በዚህ ቴፕ ክር በማይታየው ታዳሚ ውስጥ ያላችሁም፡ ይህንን ክር ካዳመጣችሁ በኋላ፡ አሁን ያላችሁበት የአእምሮ ሁኔታ በየትኛው ክፍል ውስጥ እንዳላችሁ ያረጋግጥላችኋል። በቃሉ የምታምኑና ከእርሱም ጋር የምትቆዩ መሆናችሁን፡ ወይስ ጠቅ አድርጋችሁ የምትወጡ፡ ወይም ያንን ክር የምትዘጉት መሆናችሁን፡ ትክክለኛውን ያላችሁበትን ቦታ ይነግራችኋል። እህም? ያደረጋችሁትን ይናገራል። እርሱን ማዳመጥ አትፈልጉም፡ ትዘጉታላችሁ፡ "ያንን ማዳመጥ አልፈልግም፡" ትላላችሁ፡ ያም፡ ያ የማያምነው ነው። አያችሁ፡ እርሱን ለመፈተንና እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለመመልከት አትቆሙም። አያችሁ? ወይም ዝም ብላችሁ እየተነጠለጠላችሁ በእርሱ ላይ የሆነ ስህተት ለማግኘት ትሞክራላችሁ፡ ከዚያም የት እንዳላችሁም፡ ታውቃላችሁ። ይነግራችኋል።

283 እርሱን እንድናምንና በእርሱም ላይ እንድንቆም፡ ለእርሱም ታማኝ እንድንሆን፡ ቃሉንም እንድንታዘዝ እግዚአብሔር ይርዳን፡ እርሱ ቃሉ ነውና። ይህን ታምናላችሁን?

እስቲ፡ እስቲ እንጸልይ።

284 ውድ የሰማይ አባት፡ አንዳንዴ፡ እነዚህን ነገሮች መናገር፡ ምን ያህል ከባድ ነው፡ ምናልባትም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በሀገሪቱና በዓለም ዙሪያ ሲዘዋወሩ፡ ይህንን የቴፕ ክር እንደሚሰሙት እናውቃለን። ዳሩ ነገር ግን፡ ውድ ጌታ ሆይ፡ እውነት ነው፡ ይህ እውነት ነው። እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ አስቀድመህ ልቤን ቀድሰኝ። ጌታ ሆይ፡ መርምረኝ፡ ፈትነኝ።

285 ጌታ ሆይ፡ ብቻ ወደ እኔ ተመልከት። ደካማ ነኝ። እኔ—እኔ—እኔ... እኔ—እኔ ደክሞኛል። እ—እኔ ዝዬያለሁ። ጉሮሮዬ ተዘግቷል። ከ—ከ—ከንፈሮቼ እ—እ—እ—እንደ፡ እንደመድረቅ ብለዋል። ደግሞም፡ ደግሞም

አካሌ እየደከመ ነው፡ እያረጀሁ ነው። ደግሞም ጌታ ሆይ፡ እኔ—እኔ—እስክሄድ ድ—ድረስ፡ ምናልባት፡ ፀሐይ ብዙ ጊዜ ሳትዞር፡ ብዙ ጊዜ አይቀረኝም።

286 አሁን፡ አባት ሆይ፡ አሁንም መርምረኝ። ደግሞም የተሳሳተ ነገር የማደርገው ካለ—ካለ፡ ያላወቅሁትም ከሆነ፡ አ—አቤቱ ጌታ ሆይ፡ ግለጥልኝ። አ—አቤቱ አሳየኝ። አ—አሁን ሁሉንም ነገር ለማስተካከል ዝግጁ ነኝ።

287 በዚያ በእግዚአብሔር ቃል መስታወት ውስጥ ራሴን እመለከታለሁ። የት ነው የምቆመው? ምስሌ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ሲያንጸባርቅ እመለከታለሁን? በመስታወቱ ውስጥ የማየው ሰው እርሱ ነውን? ከብሉይ ኪዳን አማኞች አንዱን፡ ወይስ ከአዲስ ኪዳን አማኞች አንዱን እመለከታለሁን? አስመሣይ-አማኝን እመለከታለሁን? ቆሞ ቃሉን ለማዳመጥ ፈቃደኛ ያልሆነውን በምትኩ ደግሞ የሐይማኖት ተቋም ሐሳብን የሚቀበል፡ የማያምን አድርጌ ራሴን አገኘዋለሁን? ትንሽ ቀዳዳ ለማግኘት እየሞከርኩ፡ ስንጠለጠል ራሴን አገኘዋለሁን?

288 ጌታ ሆይ፡ እንደዚያ ከሆነ፡ አቤቱ—አቤቱ አንጻኝ፡ ጌታ ሆይ። ልቤ ንጹሕና የጠራ ይሁን። ምክንያቱም፡ ይህ ሕይወቴ ነው፡ ጌታ ሆይ፡ እ… ይህም፡ ትክክል እንዲሆን እፈልጋለሁ። በሙላት የሚደረግበት መንገድ እያለ፡ በግማሽ መንገድ ብቻ ማድረግ አያስፈልግም። እነሆ፡ እኔ በትክክል እንዲስተካከል እፈልጋለሁ፡ አባት ሆይ። ያ ብቻ ሳይሆን፡ ወንዶችም ሴቶችም፡ እንዲሁም፡ የምወዳቸውንና፡ የሚወዱኝንም ሰዎች፥ በስህተት ከመራሁ፡ እስታለሁ።

289 እናም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ እቺ ትክክል ናት ብዬ የማስባት፡ የሆነች የሐይማኖት ተቋም ቤተ ክርስቲያን ካለ፥ ወይም የአብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ትክክል እንደሆነ፡ የአብዛኛው ህዝብ ሐሳብ ትክክል እንደሆነ ባስብ፥ ጌታ አምላክ ሆይ፡ ስህተቴን አምኜ ለመቀበል፡ እዚህም ቆሜ፡ እነዚህን ሰዎች ትክክል ነው ብዬ ወደማስበው ቦታ ለመላክ በቂ ሰው እንድሆንና በቂ ክርስቲያን እንድሆን እርዳኝ። አንጻኝ። ልመልከትና ልየው። ስለእነዚያ ነገሮች ሲነሳ ግን፡ ጌታ ሆይ፡ መመልከት እስከምችለው ድረስ፡ እነዚያ መልክ ኖሯቸው ቃሉን ይክዳሉ፥ እናንተ ብትነግሯቸውም እንኳ፡ እነርሱ ግን፡ “እንግዲህ፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። እርሱ… እግዚአብሔር አሁን ያንን አይጠብቅም” ይላሉ።

290 ጌታ ሆይ፡ አንተ ያው ኢየሱስ እንደሆንክ አምናለሁ። አንተ ከጥንት የነበርከው ያው አምላክ ነህ። አሁንም አምላክ ነህ፡ ደግሞም አትለወጥም። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ቃልህ እንደሆነ አምናለሁ፡ አንተና ቃልህ አንድ እንደሆናችሁ አምናለሁ።

291 አምላክ ሆይ፡ ቃሉን ሕያው ለማድረግ፡ ሕያው የሚያደርገውንም ኃይል እንድትሰጠን፡ ከመንፈስ ቅዱስህ እንድትሰጠን፡ እጸልያለሁ፥ ይኸውም፡ አንድ ቀን ሕይወት ሲያበቃ፡ አንተም በእኛ ላይ ያለህን ሥራ ስትፈጽም፡ ሕያዋን ሆነን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በእግዚአብሔር አሳብ ውስጥ፡ ወደነበርንበት፡ ወደ ሰማይ እንድናርግ ነው። አምላክ ሆይ፡ ይሁንልን።

292 አባት ሆይ፡ ኃጢአታችንን ይቅር በለን። እዚህ፡ በቃሉ ከሚያምኑ እውነተኛ አማኞች ውጪ፡ በዚያኛው ክፍል ውስጥ የሚቆሙ ወንዶች ወይም ሴቶች ካሉ፡ አምላክ ሆይ፡ ልባቸውን አንጻ። በክሩ የሚያዳምጡ፡ ወይም ወደፊት

የሚያዳምጡ ካሉም፡ ልባቸው እንዲነጻ እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ እንድታነጻቸው ነው። ሲጠፉ ማየት ፈ—ፈጽሞ አልፈልግም። አምላክ ሆይ፡ አንድ ስህተት ሌላን ስህተት እ—እንደማያስተካክል ማወቅ እንድንችል እ—እንድትረዳን እጸልያለሁ። ይህንን ለማድረግ አንድ መንገድ ብቻ ነው ያለው፡ እርሱም ሁለቱንም ስህተቶች ከመንገድ አስወግዶ፡ ትክክል መሆን ነው። አባት ሆይ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንድትሰጠን፡ እጸልያለሁ።

293 ራሳችንን አጎንብሰን፡ ልባችንንም ዝቅ እንዳለ፡ አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች እንድትቆሙ እፈልጋለሁ።

294 የገሃነምን ራእይ ባየሁ ጊዜ፡ ያ—ያኔ ትንሽ ልጅ እያለሁ፡ የዚያን አስቃቂነት አይቻለሁ። እንግዲህ፡ በዚህ ልሳሳት እችላለሁ። ያ ምናልባት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ብቻ ሊሆን ይችላል። ሊሆን ይችላል። አላውቅም። ያኔ የሆን ቦታ የነበርኩ ይመስላል። በጣም ተፈጥሯዊ ነበር።

ከዚያም፡ በቅርብ ጊዜ፡ ቅዱሳን ያሉበትንም አይቻለሁ።

295 በጠፉት ሰዎች ስፍራዎች ውስጥ በነበርኩ ጊዜ፡ “አምላክ ሆይ፡ ማንም ሰው ወደዚህ እንዲመጣ ፈጽሞ አትፍቀድ፡” ብዬ ጮህኩ! የዚያን አስቃቂነት ሊገልጽላችሁ የሚችል ምንም አንደበት የለም፡ አትችሉም። እኔ ልነግራችሁ የምችልበት ምንም መንገድ የለም። በእሳትና በዲን የተሞላ፡ የሚቃጠል ገሃነም እንዳለ የምታምኑ ከሆነ፡ ይህ የጠፉበት ሁኔታ ከነበረበት አስቃቂነትና ከዚያ ስፍራ ጋር ከተያያዘው—ከተያያዘው መከራ አንጻር ሲታይ፡ ያ—ያ ቀዝቃዛ ጥላ ያለው አረንጓዴ መስክ ይሆን ነበር።

296 ከሰው ልጅ ማስተዋል በላይ ስለሆኑ ነገሮች ልነግራችሁ ብሞክርም፡ አሁንም ቢሆን የቅዱሳን ስፍራ መግለጽ አልችልም፡ ምን ያህል ሰላማዊ ነው! ፈጽሞ አለመሞት፡ ፈጽሞ አለማርጀት፡ ፈጽሞ አለመታመም፥ ሁልጊዜ ወጣት መሆን፡ ሁልጊዜ ጤናማ መሆን፡ ፈጽሞም አለመሞት፥ የዘላለም ሕይወት፡ በወጣትነት በረከት ውስጥ፡ ምንም ኃጢአት ወይም ሌላ ምንም ነገር የሌለበት! ኦህ፡ ያንን ለማብራ-... ለመግለጽ፡ እርሱን ለመግለጽ ምንም መንገድ የለም።

297 ቅዱስ ጳውሎስም፡ እንዲህ አለ፡ “ዓይን ያላየችው፡ ጆሮም ያልሰማው፡ በሰውም ልብ ያልታሰበ” ብሏል፡ ልትረዱት እንኳን አትችሉም፥ “እግዚአብሔር፡ ለሚወዱት፡ ያዘጋጀላቸውን፡” ለማብራራት ምንም መንገድ የለም።

298 አሁንም፡ ይህ በእርግጥ እውነት እንደመሆኑ መጠን፡ እዚህ ያላችሁትም ሆነ የማትታዩ ታዳሚዎች፡ ዛሬ ማታ፡ ከእነዚህ ክፍሎች በአንዱ ውስጥ፡ ተሰለናል። ወይ እውነተኛ አማኞች ነን... በቃሉ ፈትኑት። ቃሉ የሆነ ነገር ቢናገር፡ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የተለየ ነገር ብትናገር፡ የትኛውን ትወስዳላችሁ? በእግዚአብሔር ቃል መስታወት ውስጥ ተመልከቱና በየትኛው ክፍል ውስጥ እንደምትቆሙ እዩ። ዛሬ ማታ፡ እዚህ ካሉትም ሆነ በማይታየው ታዳሚ ውስጥ ካሉ መካከል፡ ካልሆናችሁ፡ ከዚያ ከሚያምነው ወገን ጋር፡ ካልሆናችሁ፡ ወደዚያኛው ወደሚያምነው ወገን እንድትመጡ፡ አሁን ለእናንተ አጭር የጸሎት ቃል ላቀርብ እችላለሁን?

299 በእግዚአብሔር ፊት፡ ራሳችሁን አጎንብሳችሁ፥ ልባችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ ዓይኖቻችሁ ተዘግተው፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ይህንኑ ታሳያላችሁን? አንዳንድ

ጊዜ ሰዎች፡ ታውቃላችሁ፡ አጠገባቸው ያለውን ሰው በመፍራት፡ እጃቸውን ከፍ ለማድረግ ትንሽ ይፈራሉ... ይህም፡ እንደዚያ መሆን አይገባቸውም፡ ነገር ግን ቆ—ቆመው፡ "እኔ፡ ተሳስቻለሁ። ተሳስቻለሁ፡" ለማለት ፈቃደኛ መሆን ነበረባቸው።

300 "ኃጢአቱን የሚሰውር አ—አይለማም፡ ኃጢአቱን የሚናዘዝ ግን ምሕረትን ያገኛል።" አያችሁ? **ኃጢአት** ምንድን ነው? "አለማመን" ነው፡ (በምን? ) በቃሉ ላይ አለማመን።

301 አሁን፡ በዚያ ክፍል ውስጥ ካልሆናችሁ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምታዩአቸው ነገሮች—ነገሮች ኖረው ዝም ብላችሁ... በ—በእናንተ... በ—በእናንተ—በአእምሯችሁ፡ ልታዩት አ—አትችሉም። እናንተ ዝም ብላችሁ... መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እንደሚል ታውቃላችሁ፡ ነገር ግን ዝም ብላችሁ... ልትረዱት አትችሉም፡ ዳሩ ግን ትፈልጋላችሁ። "አምላክ ሆይ፡ ማስተዋሉን ስጠኝ። እታዘዝሃለሁ፡" በሉት።

302 እጃችሁን ከፍ አድርጋችሁ፡ "ስንጸልይ አስበኝ፡" ትላላችሁን? እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። መልካም ነው። አያችሁ?

303 በእርግጠኝነት አስቡት እስቲ፡ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ነገር አለ እኔ—እኔ እንጃ ብቻ—እኔ አላውቅም? እኔ—እኔ—በሌሎቹ ምድቦች ውስጥ ራሴን አገኘዋለሁ ብዬ እ—እፈራለሁ። ምናልባት ራሴን ከሰባዎቹ ጋር አገኘው ይሆን፡ ያም እኔ... እንደዚህ ያሉ አንዳንድ ነገሮች እ... እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች—እንዴት ሊያደርግ እንደሚችል፡ እንዴት ሊሆን እንደሚችል፡ ኢየሱስ እንዴት ያው ሊሆን እንደሚችል፡ እንዴት—እነዚህ ነገሮች እንዴት እንደሆኑ ለመረዳት በጣም ይከብደኛል። እ—እኔ አልረዳውም። ልረዳው እፈልጋለሁ። እ—እኔ ላምነው እፈልጋለሁ። አቤቱ፡ አምላክ ሆይ፡ አለማመኔን እርዳው። የ—የዚህ አካል መሆን እፈልጋለሁ። የቃሉ ተካፋይ መሆን እፈልጋለሁ። በእኔ ውስጥ እፈልገዋለሁ።"

304 "በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፡ የፈለጋችሁትን ጠይቁ።" ቅዱስ ዮሐንስ 15። እውነት መሆኑን እናውቃለን። ተመልከቱ፡ "ብትኖሩ"፡ እየገባችሁና እየወጣችሁ፡ እየገባችሁና እየወጣችሁ ሳይሆን፡ ነገር ግን፡ "በእኔ ብትኖሩ፡" እርሱም ቃሉ፡ "በእናንተም ቢኖር፡ የፈለጋችሁትን ሁሉ ጠይቁ እና ይሰጥላችኋል። ትወርሳላችሁ።"

305 "ቃሌን የሚቀበል፡ በላከኝም የሚያምን፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል።" ነገር ግን በመጀመሪያ፡ ቃሉን መቀበል ትችላላችሁን? ቃሉን፡ ክርስቶስን በሙሉ፡ መቀበል ትችላላችሁን? ክርስቶስ የተቀባ ቃል ነው። እርሱ፡ የተቀባ ቃል ነው።

306 **ክርስቶስ** ማለት "የተቀባ" ማለት ነው፡ ለዘመኑ የተቀባ ቃል፡ የተገለጠው፡ አዳኝ፡ ቤዛ ማለት ነው። ሊመጣ የነበረበት ጊዜ ያ ነበር፡ እርሱም ያንን ስፍራ ለመውሰድ የተቀባው አካል ነበር።

307 አሁን የምሽቱን ብርሃን እንዲያበራ፡ በመጨረሻዎቹ ቀኖች ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ያንን በሐይማኖት ተቋማት በኩል፡ የተረገጠውን እምነት [በክሩ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ወደ ነበረበት ለመመለስ፥ የሐይማኖት

ተቋማትን በማውገዝና ወደ መጀመሪያው እምነት፡ ወደ መጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት በመመለስ፥ የመጀመሪያውን መጽሐፍ ቅዱስ፡ እያንዳንዱን ቃል በማመን፡ በእርሱ ላይ ሳይጨምርበትና **ይህንን** እንዲል ወይም **ያንን** እንዲል ሳያደርግ ያቃናል። ልክ በተነገረበት መንገድ ተናገሩት፡ በዚያም መንገድ ልታምኑት ይገባል።

308 እጃቸውን ፈጽሞ ያላነሱ አሉን፡ እጃቸውን ከፍ አድርገው፡ "አምላክ ሆይ፡ አስበኝ፡" ለማለት የሚፈልግ አለ?

309 ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክሽ፡ ወጣት እመቤት። ጌታ ይባርክህ፡ አንተም። በጣም ጥሩ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ አንተ ወጣት። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። "እሱን እፈልጋለሁ። እ... " እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህት፡ እዚያ በስተቀኜ ያለሽው። ወደኋላም ያላችሁትን፡ ይባርካችሁ። "እንዲህ እፈልጋለሁ... " አንተም ወጣቱ ሰው፡ እግዚአብሔር ይባርክህ። አንቺም፡ እዚህ ያለሽው፡ እህት። አንተ፡ ወንድሜ፡ በዚህ በኩል፡ ጌታ ይባርክህ። ከኋላ ያለኸው፡ እግዚአብሔር ይባርክህ። "አስበኝ፡ ጌታ ሆይ።"

310 አሁን አስታውሱ፡ እጃችሁን የምታነሱት ለእኔ አይደለም፥ ለእርሱ ነው። በቀጥታ ከበስተጀርባዬ ሆኖ፡ አሁን፡ ጌታ እጃችሁን ያየዋል። እኔ ባላየውም እንኳን፡ እርሱ ያየዋል። እርሱ ልባችሁን ያውቀዋል። ምታችሁን የሚመታውን ያውቀዋል። ዓላማህን ያውቃል። ለዚያ ያለህን ዓላማ ምን እንደሆነ ያውቃል። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ።

311 ሌላ አለ፡ "ቃሉን ሁሉ ማመን እፈልጋለሁ።" እግዚአብሔር ይባርካችሁ። በጣም ጥሩ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። "አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ እርዳኝ።" ጌታ እጃችሁን ያያል። አዎን፡ ወዳጄ። በቃ። "ሊገቡኝ ያ—ያልቻሉ ነገሮች አሉ። እ—የማያምን ሰው መሆን አልፈልግም። ምንም እንኳን ባልረዳቸውም፡ ለማንኛውም፡ ላምነው እፈልጋለሁ። 'ጌታ አምላክ ሆይ፡ እነሆኝ። ላምን እፈልጋለሁ። ጌታ ሆይ፡ አለማመኔን እርዳው፡' ለማለት ዝግጁ ነኝ።" እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ብዙ፡ ብዙ እጆች ተነስተው፡ አሁንም ይወጣሉ።

312 እናንተ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ያ ይረዳልን" ትላላችሁ? ትክክለኛና፡ እውነተኛ ዓላማ ኖሯችሁ፡ እንዴ እጃችሁን ወደ ላይ አንሱና፡ ስለዚያ ምን እንደሚሰማችሁ እወቁ።

313 በሕይወታችሁ ውስጥ የሆነ ትንሽ ነገር እንዳለ መስክራችኋል፡ ታውቃላችሁ። የሆነች ትንሽ ነገር አለች፡ እዚያ እንድትሆን አትፈልጉም፡ ዳሩ ግን ለማንኛውም፡ እዚያ አለች። እንዴት ሊደረግ እንደሚችል ትደነቃላችሁ። "ደግሞም፡ ጌታ ሆይ፡ እኔ ይሁዳ እንዳልሆን ከልክል። አንድ ቀን የሆነ ትንሽ ጉድለት ይታያል ብዬ ለማሰብ እየሞከርኩ፡ ዝም ብዬ በ—በመልእክት ውስጥ እንዳልከተል ከልክል። አምላክ ሆይ፡ እኔን አይደለም። ልክ ከቃልህ ጋር እንድቆይ ፍቀድልኝ። አያችሁ? ወይም ምናልባት ዝም ብዬ 'እንግዲህ፡ እ—እ... እንግዲህ፡ ለምን ሌሎቹ እንደዚያ አይሉም? ' ብዬ የማስብ የማላምን እሆን ይሆናል፡ አያችሁ? እኔም—እንዲህ መሆን አልፈልግም። አማኝ መሆን እፈልጋለሁ። የዘመኑ የእግዚአብሔር ቃል ማየት እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር

በእርሱ ውስጥ እያለሁ። እናም፡ ጌታ ሆይ፡ የዚያ ቃል አካል አድርገኝ። የዚያ አካል መሆን እፈልጋለሁ።" ጌታ ይባርካችሁ።

314 አሁን እንጸልይ። እያንዳንዱ ሰውም እንዲሁ፡ እናንተ ስለ—ስለ ራሳችሁ ጸልዩ፡ እኔም ስለ እናንተ እጸልያለሁ። ታውቃላችሁን፡ አንድ ቀን እኛ... ሁሌ አብረን አንሆንም፡ ምናልባት፡ ለጥቂት ጊዜ ካልሆነ በቀር። አንዳንዶቻችን እንወሰዳለን፡ ደግሞም አብረን አንሆንም። አንዳንዶቻችን፡ እያረጀን ያለን፡ ብዙዎቻችን እዚህ አለን። አንዳንዶቻችን፡ አናውቅም። ወጣቶችም እንኳን ይሞታሉ። በማንኛውም ዕድሜ እንሞታለን። መለያየታችን አይቀርም፡ ደግሞም ይህ ነገር እልባት ማግኘት አለበት። ደግሞም ዝም ብላችሁ በዘፈቀደ ወደዚያ ልትደርሱ አትችሉም፡ በትክክለኛ አእምሯችሁ ውስጥ ሳላችሁ መምጣት አለባችሁ።

315 እናንተ፡ "እንግዲህ፡ ከመሞቴ በፊት ብቻ፡ ያንን ማየት በቻልኩ" ትላላችሁ። አይ፡ ያንን አታድርጉ። ያን ጊዜ በትክክለኛ አእምሯችሁ ውስጥ እንኳን ላትሆኑ ትችላላችሁ። ወደ ቤታችሁ ከመድረሳችሁ በፊት፡ በአደጋ ልትገደሉ ትችላላችሁ። በልብ ድካም ልትሞቱ ትችላላችሁ። ምን ሊከሰት እንደሚችል አናውቅም፥ ያንን እግዚአብሔር ብቻ ነው የያዘው። እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

316 ከውጭ ያሉ ሰዎች፡ ሳይቀር፡ በመስኮት በኩል እጆቻቸውን ወደ ውስጥ ሲያነሱ እየተመለከትኩ ነው። አያችሁ? አዎ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

317 "እ—እ—እኔ ትክክል መሆን እፈልጋለሁ። እ—እ—እ—እኔ ትክክል መሆን እፈልጋለሁ።" አሁንም ትክክል እንሁን፡ አሁን፡ አሁኑኑ። ዝም ብላችሁ፡ ለአንድ ጊዜ እልባት ልታሰገኙለት ትችላላችሁ፥ ከልባችሁ ጥልቅ ሆናችሁ፡ ከልብ እንዲህ በሉ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ምንም ቢሆን፡ ወይም ሌላ ማንም ምንም ቢል፡ ቃልህ በሕይወቴ ውስጥ ቀዳሚ ይሆናል። በሕይወቴ ውስጥ እርሱን እፈልገዋለሁ። አንተ ቃሉ ነህ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ብሏል፡ ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አምናለሁ። ደግሞም ወደ ውስጡ የገቡት፡ የሐይማኖት መግለጫዎችና ዶግማዎች፡ የግብዝነት ስብስብ እንዳደረጉት አውቃለሁ። ጌታ ሆይ፡ እንደዚያ ካለ ነገር አንጻኝ፡ ሙሉ በሙሉ ያንተም ልሁን። እጆቼን ወደ አንተ አነሳለሁ። ልቤን ወደ አንተ፡ ድምፄን ወደ አንተ፡ ጸሎቴን ወደ አንተ አነሳለሁ። አምላክ ሆይ፡ ማረኝ።"

318 ደግሞም፡ የኔም እጆች ወደ ላይ ተነስተዋል፡ ጌታ ሆይ። ኦ ጌታ፡ ከአለማመን ሁሉ፡ አንጻኝ።

319 ምንም እንኳን እንደ ሄኖክ እንድሄድና እንዳልሞት ኃይሉን ባ—ባይሰጠኝም፡ ነገር ግን ከከሰዓት በኋላ አብሬው ወደ ቤት ልራመድ፥ ግን፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እኔ ይህ እንደሚሆን አምናለሁ፡ ምክንያቱም በመጨረሻው ቀን ንጥቀት እንደሚኖር፡ ደግሞም ሥራው በአጭሩ እንደሚቋጭ አውቃለሁና።

320 ደግሞም፡ አባት ሆይ፡ የቀን መቁጠሪያችን እንደሚለው፡ ሠላሳ-ስድስት ተጨማሪ ዓመታት ሲያልፍ ሥራው ያበቃል፡ አንተም በዚያ ጊዜ ውስጥ መምጣት አለብህ ያለበለዚያ የሚድን ሥጋ አይኖርም። ደግሞም በዘመን ቆጣሪዎችና እ—እንደዚህ ያሉ ነገሮችን፡ በሚመረምሩ ሰዎች በኩል፡ ከእርሱ ብዙ፡ ብዙ ዓመታት ፈጽሞ ወደፊት እንደቀደምን፡ በቀን መቁጠሪያዎች

በኩል ወደዚያ ብዙ ዓመታት እንዳለፍን ተነግሮናል፥ ከዚያም በላይ እጅግ እንደቀደምን፡ ይነግሩናል፡ ምናልባትም ዐሥራ አምስት ወይም ሃያ ዓመታት፥ ብቻ ቀርተው ይሆናል። እኔ አላውቅም፡ አባት ሆይ። ሆኖም፡ በእኛ የቀን መቁጠሪያ መሠረት እንኳን፡ ለማለት ይቻላል እዚያው እንደደረስን አውቃለሁ።

321 ጌታ ሆይ፡ ምንም ተስፋ ሊቀር የማይችልበት ደረጃ ላይ እንደደረስን እያለሁ። እየመጣ ያለ... ቦምቦችን እርስ በርሳቸው ላይ መወርወር ከጀመሩ፡ ጌታ ሆይ፡ እዚያ—እዚያ—እዚያ የጦር ግንባር የሚባል ነገር አይኖርም። እነርሱ፡ እርስ በርሳቸው ይጠፋፋሉ። ደግሞም፡ ጌታ ሆይ፡ እያንዣበበ ነው፡ ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ሰማያትና ምድር ሁሉ በእሳት እንደሚቃጠሉ ይናገራል። አምላክ ሆይ፡ ሰዓቲቱ ስትደርስ እያለሁ።

322 ስለ ፕሬዚዳንቱ ግድያ ትዝ ይለኛል፡ ከዚያም ሌላኛው ክፉ ሰው መጥቶ፡ ለሰውየው ምንም ፍርድ ሳይሰጠው፡ በጭካኔ-ግድያ፡ በጥይት ሲረሸነው። አምላክ ሆይ፡ አንዱ እንደ ሌላው በደለኛ ነው። ያንን ለማድረግ ምንም መብት የላቸውም። በገዛ አገራችን ውስጥ ያለው ክፋት፡ የክርስቲያን አገር መሆን ሲገባት፡ ጌታ ሆይ፡ ምን አይነት፡ ደካማ የክርስቲያን ምሳሌ ነን። ጌታ ሆይ፡ ኃጢአታችንን፡ ይቅር በለን።

323 አምላክ ሆይ፡ በተለይም ያንተን ቤተ ክርስቲያን፡ ወደዚያ ሚስጥራዊ የክርስቶስ አካል የተጠመቁትን፡ እርዳን። አንተም፡ እንዳልከው፡ "ሕያው የሚያደርገው መንፈስ ነው።" የሰው ልጅም ወደ ላይ እንዳረገ፡ እንዲሁ አካሉ ወደ ላይ ያርጋል። እርሱም ራስ ነው፥ ቤተ ክርስቲያኑም አካሉ ነች። አምላክ ሆይ፡ አካልን የሚመራው ራስ ነው። የቃሉ ራስነት የክርስቶስን አካል ይመራው። ጌታ ሆይ፡ እኔም የዚያ አካል ክፍል ልሁን።

324 እጆቻቸውን ላነሱት፡ እዚህ ለተገኙት ሁሉ እንዲሁም በቴፕ ላይ ለሚያዳምጡት ሁሉ እጸልያለሁ። ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ በቅንነት እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ አውጣቸው። ልባቸውን ተመልከት። ምን እንደሆኑ አንተ ታውቃለህ። ነገር ግን፡ እንደ አገልጋይህ፡ ጌታ ሆይ፡ እ—እኔ ሰዎችን እወዳለሁ። እ—እወዳቸዋለሁ። እወዳቸዋለሁ።

325 ይህን ለ—ለ—ለማድረግ የምሞክረው ይህ አንተ የሰጠኸኝ ተልእኮ እንደሆነ ስለተሰማኝ ነው። ስለዚህ፡ አባት ሆይ፡ በምችለው መጠን፡ እነሆኝ... ጌታ ሆይ፡ ደካማ ስህተቶቼን ይቅር በለኝ። ለሕዝቡ ይበልጥ ግልጽ ላደርግላቸው እንድችል፡ ብርታትን እንድትሰጠኝ—እንድትሰጠኝ እጸልያለሁ።

326 አሁን ዛሬ ማታ፡ በጉባኤው ከእኛ ጋር ሁን። ጌታ ሆይ፡ በተበርናክሉ ውስጥ፡ እጃቸውን ያነሱትን እነዚህን ተመልከት። ጌታ ሆይ፡ መርምረኝ፡ ፈትነኝም። በእኔም ውስጥ አንዳች ስህተት ቢኖር፡ አባት ሆይ፡ አንጻኝ። ይሁንልን። ይህችን ቤተ ክርስቲያን አንጻት።

327 ሁላችንን አንጻን፡ ጌታ ሆይ፡ ቃሉ በእኛ መካከል ሥጋ እንዲለብስና በዚህ ቀን ለዓለም ይታወቅ። አባት ሆይ፡ ይሁንልን። ምክንያቱም፡ ለነፍሳችን መዳን፡ ይህንን፡ ራሴንም፡ ይህንንም ጽሑፍ፡ ከዚህም ታዳሚ ጋር፡ ከቃልህና ከተስፋህም ጋር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አደራ እሰጣለሁና። ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን።

328 የእግዚአብሔር ኃይል በእኛ ላይ ይምጣ ይቅባንም፡ ከፓስተሩ ጀምሮ እስከ ጽዳት ሠራተኛው፡ እዚህ ወዳለውም እያንዳንዱ ሰው ሁሉ። መንፈስ ቅዱስ መጥቶ በልባችን ውስጥ ስፍራውን ይያዝ፡ የእግዚአብሔርንም ተስፋ ሁሉ ወስዶ ቃልህ እውነት እንደሆነ ይግለጥልን። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ።

329 ራሳችንን አጎንብሰን ሳለን። "እስ... " የኦርጋን ተጫዋቿ፡ ከቻለች፡ በዚህ መዝሙር ላይ ቃና እንድትሰጠን ብቻ እፈልጋለሁ፡ "አዳኜ ሲጠራኝ እሰማለሁ። ወደሚመራኝ ሁሉ እከተላለሁ።" **ወደሚመራኝ ሁሉ እከተላለሁ።**

> ... አዳኜ እየጠራኝ ነው፡ (እርሱ ማነው? ቃሉ።)
> አዳኜ ሲጠራኝ እሰማለሁ፡
> አዳኘን መስማት እችላለሁ...

አሁን ዶግማዎቻችሁንና ነገሮችን ትክዳላችሁ።

> መስቀልህን ተሸከምና ተከተል...

330 "መስቀሉን ተሸክሞ እኔን፡ ቃሉን፡ የማይከተል ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይገባውም።"

> ወደሚመራኝ... (ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለሱ፡ ወደሚመራችሁ።)... እከተለዋለሁ፡
> ወደሚመራኝ እከተለዋለሁ፡
> ወደሚመራኝ እከተለዋለሁ፡
> እኔ... (በሰሙ ወደ ገንዳው ቢሆን፡ ኃፍረቴን ለማስወገድ፡ ወደ መሠዊያው ቢሆን!)... እስከመጨረሻው።

331 [ወንድም ብራንሃም **ወደሚመራኝ ሁሉ እከተለዋለሁ እያለ** አንጎራጎረ።—አርታዒ።]

> ... በፍርዶች ውስጥ ከእርሱ ጋር፡ (ይኸው ነው፡ ልክ አሁን።)
> እ...

332 ከየትኛው ወገን ነህ? አሁን በቃሉ እየተፈረደብኝ ከሆነ፡ በእግዚአብሔር መስታወት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ በሚያንጸባርቀው ምስልህ ላይ ምን ታያለህ?

> አብሬ እሄዳለሁ...

333 "ምንም ዋጋ ቢያስከፍልም፡ ከቃሉ ጋር እሄዳለሁ። በእግዚአብሔር ፍርዶች ውስጥ እያለፍኩ ነው። ከክፍሎቹ አንዱን መቀበል ካለብኝ፡ ልክ በቃሉ መሠረት፡ አማኝ ያድርገኝ።"

> ... ከእርሱ ጋር፡ በመንገድ ሁሉ።
>
> እሱ ወደሚመራኝ ሁሉ...

334 አሁን በደንብ፡ አስቡበት።

> ... ወደሚመራኝ...

63-1124E ሦስት አይነት አማኞች
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org